# የምሥራች ለምእመናን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ በማዕከል ደረጃ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መሪነት፣ በወጣት ዘማር ያን ዘማሪነት የተዘጋጁ ያሬዳዊ መዝሙሮችን ቁጥር 1ና ቁጥር2 በሚል በሁለት ካሴቶች አዘጋጅቶ አቅርቦላችኋል።







በቅርቡም ከ800 በላይ መዝሙረ ማህሌት ግጥሞችን የያዘ መጽሐፍ ለማሳተም በዝግጅት ላይ ነው።

ካሴቶችን በየአጥቢያችሁ አብያተክርስቲያናት ሰንበት ት/ቤቶች ጽ/ቤት ወይም ደግሞ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ዋና በር አጠገብ ካለው የመምሪያው የመጽሔት፣ የመጻሕፍትና የካሴት መሸጫ ሱቅ ማግኘት ትችላላችሁ።

**ለተጨማሪ ማብራሪያ**
☎ 56 72 79 በመደወል
✉ 81286 በመጻፍ መጠየቅ ትችላላችሁ

ዋጋ ብር 3.50

# ፈለገ ጥበብ


፫ኛ ዓመት ቁጥር ፩ ሐምሌ ፲፱፻፺፩ ዓ.ም




- ከማስተማር የሚለየኝ ሞት ብቻ ነው
- ከጨለማ ያመለጡ የብርሃን ፍሬዎች
- ሳታቋርጡ ጸልዩ
- አስደናቂው የዘመናችን ፍቅር
- በሕግ አምላክ!


www.ethiopianorthodox.org

# ፈለገ ጥበብ

፳ኛ ዓመት ቍጥር ፩

ሐምሌ ፲፱፻፺፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች
ማደራጃ መምሪያ

በየ፫ ወሩ የሚዘጋጅ መንፈሳዊ መጽሔት

## ከአዘጋጁ ብዕር

ፈለገ ጥበብ መጽሔት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ላለፈው አንድ ዓመት ያህል ከእናንተ አንባብያን ተለይታ ቆይታለች። ለዚህም ይቅርታ እንጠይቃለን። ፈለገ ጥበብ ከሃያ አንድ ዓመታት በኋላ ዳግም ሕልውናዋን ያበሰረችው በወርሐ ሐምሌ ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ነበር። እንደ አጋጣሚ ሆኖ አሁንም ከተወሰነ ጊዜ መቋረጥ በኋላ በወርሐ ሐምሌ ራስዋን በአዲስ መልክ አጠናክራ ብቅ ብላለች።

እኔም ወጣት ነበርኩ፣ ትምህርተ ሃይማኖት፣ ከወጣቱ ለወጣቱ፣ እስትጉቡእ፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን የመሳሰሉ ቋሚ የመጽሔቷ አምዶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተዘጋጁ የሕይወት ምግብ የሆኑ ትምህርቶች ተካተዋል። በተለይ በወጣቱ ላይ ያተኮሩ ትምህርታዊ ጽሑፎችም የጐላ ሥፍራ ተሰጥቶአቸዋል።

ዐብይ ትኩረታችን በወጣቱ ትውልድ ላይ ያረፈ ቢሆንም ፈለገ ጥበብ ወላጆችንና ልጆችን፣ አበው ሊቃውንትና ወጣቶችን እንደ ድልድይ በመሆን ታገለግላለች የሚል እምነት አለን። ፈለገ ጥበብ የቤተሰብ መጽሔት ናት የምንለውም ለዚሁ ነው። እናንተም እንደ ቤተሰብ አባልነታችሁ ከጎናችን በመሆን ድክመቶቻችንን ጠቁሙን፣ አስተያየታችሁን ላኩልን።

ዋና አዘጋጅ ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር

ምክትል አዘጋጅ መልአከ ሰላም ኃይለኢየሱስ ከበደ
ስልክ 56-26-52
ፖ.ሣ.ቁ. 81286

## ማውጫ

❖ ቃለ በረከት
ከመታመምህ በፊት ጸን . . . . . . . ፫

❖ ትኩረት ለሰንበት
ት/ቤት ወጣቶች . . . . . . . . ፬

❖ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን
ዕይታ የነባር ት/ቤቶች ገጽታ . . . ፯

❖ ትምህርተ ሃይማኖት
ሳታቋርጡ ጸልዩ . . . . . . . . ፲

❖ እኔም ወጣት ነበርኩ
ከማስተማር የሚለየኝ
ሞት ብቻ ነው . . . . . . . . . . ፲፪

❖ ሞትና ትንሣኤ . . . . . . . . . . ፲፯

❖ እስትጉቡእ . . . . . . . . . . . ፲፰

❖ ከወጣቱ ለወጣቱ
የደብረ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ
ሰንበት ት/ቤት . . . . . . . . . . ፲፱

❖ ልትድን ትወዳለህን?
ሰዎች እንዲሠቃዩ እግዚአብሔር
ይፈቅዳልን? . . . . . . . . . . ፳፩

❖ ከምኞት በስተጀርባ . . . . . . . ፳፬

❖ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን
በሕግ አምላክ! . . . . . . . . . . ፳፯

❖ ከጨለማ ያመለጡ
የብርሃን ፍሬዎች . . . . . . . ፳፱

❖ የቅዱስ ገብርኤል
ተራዳኢነት . . . . . . . . . . ፴፩

www.ethiopianorthodox.org

# ከመታመምህ በፊት ዳን

**ኤች አይ ቪ ኤድስን በተመለከተ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ፣ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በተለያዩ ጊዜያት ካስተላለፉዋቸው ቃለ በረከቶች የተወሰዱ ምርጥ ጥቅሶች**



«የመጣብን ችግር ቀላል አይደለም፤ ሰውና በሽታ ተለያይተው ባያውቁም ኤድስ ግን ከበሽታዎች ሁሉ የከፋ ነው፤ «ሕልፈት አለ ኤድስ ቢኖር ባይኖርም የማይሞት የለም» የሚሉ አሉ። ይህ አባባል ስህተት ነው፤ እግዚአብሔር እንደ ተፈጠርን እንድንሞት አልፈጠረንም፤ ከአገልግሎት በኋላ እንጂ፤ ለበጎ ዋጋ፣ ለክፉ ቅጣት በመስጠት አገልግለን እንድናልፍ ፈጥሮናል።»

ከሐምሌ ፩–፫ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ለእህጉረ ስብከት ሥራ አስኪያጆች በኤድስ ላይ ተዘጋጅቶ ከነበረው ሀገር አቀፍ ሴሚናር ከተናገሩት

«ጥንታውያን አባቶቻችን በመንፈሳዊ ሀብታቸው የበለጸጉ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ ያደረባቸው ነበሩ። ለዚህ ዋና ምክንያቱ ገና ከሕፃንነታቸው ጀምረው በቤተ ክርስቲያን ሥር ያድጉ ስለ ነበር ነው። እኛም ብንሆን ልጆቻችንን ከመጀመርያው ጀምረን አዝለንም ተሸክመንም ቤተ ክርስቲያን ይዘናቸው መምጣት አለብን። እነዚህ ሕፃናት ናቸው፤ ምንም አያውቁም ማለት የለብንም፤ እኛ በማናውቀው እግዚአብሔር በሚያውቀው መንገድ እነዚህ ሕፃናት የሚማሩት ነገር አላቸው። አንድ ልጅ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ወደ እግዚአብሔር ቤት እየተመላለሰ፣ ቃለ እግዚአብሔርን እያዳመጠ ካደገ የወደፊት ዘላቂ ሕይወቱ የተስተካከለ ይሆናል።

እግዚአብሔር ለሕፃናት ሁለት ነገሮችን ሰጥቶአቸዋል፤ የመላእክት ጥበቃና የወላጆች ጥበቃ። በመሆኑም ሕፃናት ለወደፊቱ የእግዚአብሔር መካሪያ ሆነው እንዲያድጉ በማድረግ በኩል የወላጆች ኃላፊነትና ድርሻ የላቀ ነው። ከሕፃን ቂርቆስ የምንማረውም ይህንኑ ነው። ቅዱስ ቂርቆስ በሃይማኖቱ ምክንያት ለትውልድ ማስተማርያ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ኃይል የተገለጸበት ነው፤ ይህ የሚያሳየን ሕፃናት ከመጀመሪያው ጀምረው በቤተ እግዚአብሔር ማደግ እንዳለባቸው ነው።»

✧ ✧ ✧

«ሀገራችን ሀገረ እግዚአብሔር ወይም የሃይማኖት ሀገር ናት። እግዚአብሔር በዜጎቿ አድሮ በግልጽ የሚታይባት ሀገር ናት። ሕዝባችንም የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጽበት ሕዝብ ነው። ይህ ከሆነ ዘንድ ሕዝቡ ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅ አለበት። ሕገ እግዚአብሔርን የሚጠብቅ ሕዝብ ደግሞ ሕመምና ችነፈር አያጋጥመውም።

አሁን የሚታየው ሁኔታ ግን የሚያመለክተው ራሳችንን ከሕገ እግዚአብሔር እየራቅን መምጣታችንን ነው። ሕገ እግዚአብሔር ባይፈርስ ኖሮ ዜጎቻችን በየቀኑ በቀሳፊው በሽታ እንደ ቅጠል ባልረገፉ ነበር። ተደጋግሞ እንደሚነገረው ለዚህ ቀሳፊ በሽታ ብቸኛ መፍትሔ ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቆ በሥነ ሥርዓትና በኢትዮጵያዊ ባህል መኖር ነው። ኤድስ አሁን እንደምናየው በአስቂኝ ትያትሮችና በቀልዳ ቀልድ ጭውውቶች የሚገታ አይደለም። የዚህ ዓይነት አቀራረብ በሽታውን እንደ ቀላል አስመስሎ ስለሚያሳይ ወጣቱ ትውልድ በሽታውን እንዳይፈራው ያደርጋል። በመሆኑም ሕዝቡን ስለ ኤድስ በምናስተምርበት ጊዜ እውነታውን በትክክል መልኩ በሚያሳይ መንገድ መሆን አለበት።»

✧ ✧ ✧

«ስለ ኤድስ በየጊዜው ተደጋግሞ ይነገራል፤ እንደ ዛም ሆኖ ጥፋቱ እየተፈጸመ፤ ቅስፈቱ እንደ ቀጠለ ነው። ከእንግዲህ ወዲህ ግን ይህ ሁኔታ ሊቀየር ይገባል። እስከ አሁን ያለቁት ይበቃናል፤ ከአሁን በኋላ በኤድስ መማርያ የሚሆኑ ዜጎች ሊኖሩን አያስፈልግም። ግንዛቤአችንን እናዳብር፤ ሁላችንም ፊታችንን ወደ እግዚአብሔር እንመለስ፤ ብቸኛ መፍትሔ ያለው ከእርሱ ዘንድ ነውና።»

ሐምሌ ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም በቁልቢ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ካስተላለፉት ቃለ በረከት



www.ethiopianorthodox.org

# ትኩረት ለሰንበት ት/ቤት ወጣቶች

## «ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም» (ምሳሌ ፳፪፥፮)

የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደረጃ መምሪያ ኃላፊና የደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ቆሞስ አባ ቃለ ጽድቅ እውነቱ ለሁሉም አህጉረ ስብከት፤ ለወላጆችና ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ጋር የተያያዘ ተግባር ለሚያከናውኑ አካላት በሙሉ ያስተላለፉት መልእክት፤



ልጆች በሃይማኖት መንገድ እንዲሄዱ፣ በምክረ ካህን እንዲመሩ፣ ልጆችን በሚወድ ትጉህ ኖላዊ እንዲጠበቁ፣ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሊቀ ሐዋርያት ለቅዱስ ጴጥሮስ የሰጠው አደራ «ስምዖን ወልደ ዮና ታፈቅረኒ ፈድፋደ እም እሉ» የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?

«እወ እግዚኦ ለሊከ ተአምር ከመ እነ አፈቅረከ»

«አዎን ጌታ ሆይ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ» ከሚለው ጥያቄና መልስ ጋራ በማያያዝ:-

- በጎቼን ጠብቅ
- ጠቦቶቼን ጠብቅ
- ግልገሎቼን አሰማራ

ሲል የጾታ ልዩነት ሳይኖር ልጅ አዋቂውን፣ ወጣት ሽማግሌውን፣ እንደ ዕድሜ ደረጃቸው በፍጹም ትጋትና ፍቅር እንዲራራላቸውና እንዲጠብቃቸው «ትወደኛለህን?» ዮሐ. ፳፩፥፲፭ በሚለው ጥያቄ ትክክለኛ ወዳጅነቱን ከአንድም ፫ ጊዜ በማረጋገጥ ከማንኛውም በላይ ለመንጋው ከማይራሩ ነጣቂ ተኩላዎች ወይም ከሃድያን መናፍቃን የመጠበቅ፣ የማስተማር፣ የመገሰጽ ልዩ ስልጣን እንደ ሰጠው ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል።

ከዚህም በመነሳት በሐዋርያት እግር የተተኩ አባቶቻችን ማለት ቅዱስ ሲኖዶሱ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን አንድነትና አስተዳደር ለማጠናከር በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ለሦስተኛ ጊዜ ተሻሽሎ በወጣው የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ደንብ በአንቀጽ ፳፩ በገጽ ፳፮ ለሕፃናትና ለወጣቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት የዕድሜያቸው መጠን ከ፬ እስከ ፴ ዓመት የደረሱትን በሰንበት ትምህርት ቤት አባላት ሆነው እንዲማሩ፣ ከ፩ ተራ ቁጥር እስከ ፲፪ ተራ ቁጥር ድረስ ሕግና መመሪያ አውጥቶ በየደረጃው ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች አደራ ከመስጠቱም በላይ ለሰንበት ትምህርት ቤቶች መመሪያ ይሆን ዘንድ በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም የሰንበት ትምህርት ቤቶች ውስጠ ደንብ አጽድቆ ለአብያተ ክርስቲያናት አስተላልፎአል።

ሕግ ደንብ መመሪያ መውጣቱ ሁሉም ኃላፊነቱን ተወጥቶ ሕፃናትንና ወጣቶችን በማቅረብና በማስተማር የነገዋ ቤተ ክርስቲያን ተተኪ እንዲሆኑ ለማዘጋጀትና በእናት ቤተ ክርስቲያናቸው በእምነትና በሥርዓት እንዲያድጉ ለማድረግ ወሳኝ በመሆኑ ነው።

ለዚህም ነው ጠቢቡ:-

«ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም» ያለው።

በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረው የሰው ልጅ ይቅርና በዘመናችን እንስሳቱንና አራዊቱ በሰው ልጅ ሠልጥነው ሲታዘዙና ልዩ ልዩ አስደናቂ ትርኢቶችን ሲአሳዩ ስናይ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? እስከ ማለት ደረጃ የምንደርስ ጥቂቶች አይደለንም።

ይሁን እንጂ በፍቅር ከአቀረቡት የማይቀርብ፣ የማይለምድና የማይታዘዝ የለም፤ ለዚህም ነው አራዊቱና እንሰሳቱ በሰው ልጆች ሰልጥነው ከእነሱ የማይጠበቅ ሥራ ሲሠሩ የምናየው። ይህም ሊሆን የቻለው ገና ከሕፃንነት ጀምሮ የሰዎችን ጠረን (ወዝ) ከመልመድ አልፈው የሚታዘዙበትንም ቋንቋ እንዲለማመዱ በመደረጉ ነው። ዕፅዋትንም ብንመለከት ቀጥተኛ ማድረግ የሚቻለው ገና በለጋነታቸው እንጂ ከአደጉ በኋላ እናቅናቸው ብንል ለመስበር ካልሆነ በቀር ማቅናት የማንችል መሆናችን ለሁላችንም ግልፅ ነው። በጣታችን ነቅለን የምንጥለው ችግኝ ከአደገ በኋላ እንቁረጠው ብንል ብዙ ጊዜና ጉልበት፣ ስል መጥረቢያና መጋዝ እንደሚያስፈልገን አንጠራጠርም።

በመሆኑም እንስሳቱ እና አራዊቱ እንዲሁም ዕፅዋቱ በለጋ ሕይወታቸው ቀጥተኛውን መንገድ እንደሚይዙና ለሰው ልጅ እንደሚታዘዙ ከተረዳን፤ ከዚህ በበለጠ ሕፃናቱና ወጣቶች ሊሄዱበት የሚገባውን መንገድ በሕፃንነታቸው ብናሳያቸው ከዚያ ፈቀ እንደማይሉ የተረጋገጠ ነው። ይህን ሳናደርግ አድገው የእሳትነትን ባሕርይ ወይም ጠባይ ከያዙ በኋላ መንገዱ ይህ ነው ብንላቸው ግን ድካማችን ከንቱ ድካም ይሆናል።

ስለዚህ መድኃኒታችን በቅዱስ ቃሉ እንደ አስተማረን:-

«ሕድግዎሙ ለእሉ ሕፃናት ኢትከልእዎሙ ይምጽኡ ኀቤየ»

«ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ሕፃናትን ተውአቸው አትከልክሉአቸው»

«እስመ ለዘከመ እሉ ይእቲ መንግሥተ ሰማያት»

«መንግሥተ ሰማያት ወንጌል የምትነገር እንደነዚህ ላሉ ነውና»

«እንድም መንግሥተ ሰማያት የምትሰጥ እንደነዚህ ላሉ ነውና»

በማለት ሕፃናት ባርኮአቸ ዋል። (ማቴ.፲፱፡፲፬)

ዛሬም በዚሁ አምላካዊ መመሪያ ሕፃናቱና ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ተገኝተው በረከትን እንዲቀበሉ፣ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተመገቡ፣ እንዲያድጉ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት መሆኑን አውቀው በትክክለኛዋ አርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ መንገድ እንዲማሩ፣ ማድረግ ሲገባን ነገሩን አርቆ ባለማየት ባለማሰብ እንደ ደቀ መዛሙርቱ ስናርቃቸው የምንታይ ጥቂቶች አይደለንም። የሕፃንነትና የወጣትነት ጠባያቸውን ረስተን ነውርና ነቀፋ የምንቀጽላቸውም እንደዚሁ። እንግዲህ ነገሩን በማስተዋል ፈጣሪያችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያቀረባቸውን ሕፃናት እኛ ልናርቃቸው ስለማይገባን የየበኩላችን ኃላፊነት እንድንወጣ «ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ሕፃናትን አትከልክሏቸው» የሚለውን አምላካዊ ቃል መመሪያ ልናደርገው ይገባል።

በሌላ መልኩም ሕፃናትና ወጣቶች ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ማስተማር በዘመኑ የበጎች እረኞች ተብለን እንደ የስጦታችንና ደረጃችን ኃላፊነት የተሰጠን ሁላችን እንደ ገብር ሃካይ ተወቃሽ እንዳንሆን ልናስብበት ይገባል። ገብር ሃካይ ተወቃሽ የሆነው ሁላችን እንደምናውቀው የተሰጠውን መክሊት ትርፍ ባለማትረፉ እንጂ አይነቱን በማጥፋቱ አይደለም። ብዙዎቻችን ግን ራሳችንን ከእርሱ ጋር ስናነፃጽር ትርፉ ይቅርና የተሰጠንን መክሊት ዋናውን ይዘን መገኘታችን ያጠራጥራል። እግዚአብሔር ከመረጣቸውና የተሰጣቸውን አደራ ለመጠበቅ ደፋ ቀና ከሚሉት ከጥቂቶች በስተቀር ማለት ነው።

ስለሆነም ከቂምና ከበቀል ነፃ የሆኑ ሕፃናትና ታዳጊ ወጣቶች በሽምግልናቸው ጊዜ ፈቀቅ እንዳይሉ፣ እግዚአብሔርን በመፍራትና በማምለክ እንዲሁም በማመስገን እንዲያድጉ፣ ከመንገዱም እንዳይወጡ ከሽንገላ፣ ከቂም በቀል ነፃ በሆነው ሕይወታቸው ፈጣሪያቸውን ማመስገንን እናስተምራቸው። ነቢዩ ዳዊት

«እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብሐተ» (መዝ.፰፥፪)

«ከሕፃናትና ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ»

ሲል እንዳስተማረን ጠላት ያፍር ዘንድ ልጆችና ወጣቶች በጠዋት በማታ ከቀሳውስትና ዲያቆናት ጎን ተሰልፈው ማመስገን እንዲችሉ፣ ሃይማኖት ከምግባር፣ ሥርዓት ከታሪክ አጣምረን እናውርሳቸው፣ እናስረክባቸው። ይህ ከሆነ ነው እስከ መጨረሻው ድረስ ቤተ ክርስቲያኗ ታማኝ ልጆች አሉአት ብለን ልንመሰክር የምንችለው። ያላስተማርነውንና በተዋሕዶ መንገድ ያልመራነውን በልዩ ልዩ በግልጽ ብቻ በብዙ ቁጥር የምናየውን ወጣት የእኛ ነው ማለቱ ራስን ማታለል ነው። ምክንያቱም ለበዓል ጊዜ የበዓሉ ድምቀት የሚጠራቸው፣ በጓደኞቻቸው ተስበው የበዓሉን ሥርዓት ብናይ ምን አለበት የሚሉ ሌሎችም ኢአማንያን አሉና።

ሌላው ልጆች ለወላጆቻቸው ታዛዥ እንዲሆኑ ማስተማር የእኛ ኃላፊነት ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን መልእክቱ ም.፮ ከቁ. ፩፥፬ «ልጆች ሆይ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ ይህ የሚገባ ነውና፤ መልካም እንዲሆንልህ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አክብር»

በዘመናችን ለወላጆቻቸው መታዘዝ ይቅርና ለራሳቸው በጎ ነገርን ማድረግ የተሳናቸው በማይጠቅም መንገድ የሚጓዙ ወጣቶች እየበዙ በመሄዳቸው ወላጆች፣ ወገን፣ ሀገር፣ ተስፋ የሚያደርጉአቸው ወጣቶች መንምነዋል፤ ተስፋ ቢሶችም በመሆን ላይ ይገኛሉ። የእየለቱን የሕይወት እንቅስቃሴ ስንመለከትም ወጣቶች እንደ ቅጠል እየረገፉ ይታያሉ። የወ ጣቶችም ሆነ የሕፃናቱ መጥፋት ወይም ታዛዥ አለመሆን በትክክለኛው መንገድ እስካልመራናቸው ድረስ ተጠያቂዎች እኛ የጊዜው ኃላፊዎች በመሆናችን ከወዲሁ ልናስብበት ይገባል።

ቅዱስ ጳውሎስ ከላይ በተጠቀሰው መልእክቱ በምዕራፍ ፮ ቁጥር ፩–፬

«እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ»

በማለት እንዳስተማረን እግዚአብሔርን የሚከተሉ ልጆች ለሃይማኖታቸው ቀናዕያን የሆኑ የቤተ ክርስቲያናቸውን ድምፅ የሚሰሙ፣ ሰምተውም «ምንተ ንግበር» ምን እንሥራ የሚሉ ከልዩ ልዩ መቅሰፍት ደዌ በሽታ በምክረ ካህን ራሳቸውን የሚጠብቁ፣ ከቀሳፊው በሽታ አምልጠው ረጅም ዕድሜ የሚኖሩ ሕፃናትንና ወጣቶች ለቤተ ክርስቲያናችን እንዲኖሩአት ጊዜው ዛሬ ነውና እንትጋ፣ እንንቃ፤ ድምጻችንን ከፍ አድርገን እናስተምራቸው፤ ከተለያዩ መንገዶችም ጠርተን በትክክለኛዋ የተዋሕዶ መንገድ እንዲጓዙ መንገዱን እናሳያቸው።

አንዳንዶቻችን ሕፃናትና ወጣቶችን ማስተማር፣ ከእነርሱ ጋር አብሮ መዘመር፣ መጸለይ ይቅርና ከእነርሱ ጋር ብንታይ ክብራችን የተነካ የሚመስለን አለን። አልፎ ተርፎም የሚአስተምሯቸውን መምህራን ከሕፃናትና ከወጣቶች ጋር ምን አለህ በማለት የሚ



www.ethiopianorthodox.org

ያዳክሙ አንዳንድ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት መኖራቸው አያነጋግርም።

ይሁን እንጂ ሕፃናት ክብር ያላቸው መሆናቸውን መድኃኒታችን እና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተደጋጋሚ አስተምሮናል። ደቀ መዛሙርቱ ሲከለክሉአቸው ተውአቸው አትከልክሉአቸው በማለት። በሌላ መልኩም:-

«ወበይእቲ ሰዓት ቀርቡ ኀቤሁ አርዳኢሁ ለእግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይብሉ መኑ እንጋ የዓቢ በመንግሥተ ሰማያት»፤

በዚያች ሰዓት ደቀ መዛሙርቱ ወደ ጌታ ኢየሱስ ቀርበው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን? አሉት።

«ወጸውዓ ሕፃነ ወዓቀመ ማዕከሎሙ» ሕፃንም ጠርቶ በመካከላቸው አቆመ «ወይቤ አማን እብለክሙ እመ ኢተመየጥክሙ ከመዝንቱ ሕፃን ኢትበውኡ ውስተ መንግሥተ ሰማያት» እንዲህም አለ «እውነት እላችኋለሁ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃንም ካልሆናችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም» ይላል።

ከዚህ ቃል እንደምንረዳው ሕፃናት በእግዚአብሔር ዘንድ ክብር ያላቸው ከመሆናቸውም በላይ ራሳቸውን ከፍ ከፍ አድርገው እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ የሚሉ ሁሉ ራሳቸውን እንደ ሕፃናት ዝቅ ማድረግና በየዋሃት ወደ ሕፃንነት መመለስ እንዳለባቸው ያስተምረናል። እንግዲያስ ሌሎችን መምህራን ማዳከሙን ትተን ተባባሪዎች እና ተሳታፊም በመሆን ከጎናቸው በመሰለፍ ሕፃናቱን እና ወጣቶችን እናስተምራቸው። በብሩህ ገጽም እንቀበላቸው። ሌላው ሁላችንም በስፋትና በጥልቀት ለነገሮች ክብደት በመስጠት ልንመለከታቸው የሚገባን ነጥቦች በወጣቶችና በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች (ኃላፊዎች) መካከል ጎላ ብለው የሚታዩትን ችግሮች በቅደም ተከተላቸው አይቶ መፍትሄ መፈለግ፣ መስጠት ከሁላችን ይጠበቃል።

ችግሮቹም:-

፩. በብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ያሉ አስተዳዳሪዎች፣ የሰበካ ጉባኤ አባላት ሕፃናትና ወጣቶችን በቅርብ አለማየት፣ ክትትል አለማድረግና ተገቢውን ትኩረት አለመስጠት፣

፪. ለሰንበት ትምህርት ቤቱ ዕድገት በጀት አለመመደብ፣ ድጋፍ አለመስጠት በልዩ ጥረታቸው በተለያየ መንገድ አሰባስበው ገቢ ያደረጉትን ገንዘብ ለበጎ ሥራ ዓላማቸው ወጭ አድርጎ አለመስጠትና አለመፍቀድ፤ በአንፃሩም ገቢ እንዲያደርጉ አለመቆጣጠር፣ በማን አለብኝነት እንዲራመዱ ክፍተት መፍጠር፣

፫. የሕፃናቱን እና የወጣቶችን ጥቅምና ጉዳት ለይተው ባላወቁ አንዳንድ ቀሳውስትና ዲያቆናት ከዚያም በላይ ኃላፊዎች ሆነው በተሰየሙ መምሕራን ልጆቹ እንደ ሥራ ፈት መቆጠራቸው፣

፬. የመምህራን፣ የቀሳውስትና የዲያቆናት የዕለት ከዕለት ክትትልና ንቁ ተሳትፎ አለመኖር፣

፭. ለሰንበት ትምህርት ቤቶች አስተማሪ በአብዛኞች አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ብቃት ያላቸው መምሕራን አለመመደብ፣ ከእነርሱው ውስጥ የተማሪ አስተማሪ እንደ ፈለገ ያለ ታዛቢ አገኝ አጣውን የማስተማር ችግር፣

፮. ወጥና ተከታታይ የሆነ እንደየ ዕድሜ ደረጃቸው የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት አለመኖር፣

፯. የእርስ በእርስ አለመግባባት ችግር፣

፰. ሕፃናትና ወጣቶች በንጽሕና አጊጠው የቤተ ክርስቲያን አለኝታ እንዳይሆኑ ለአድማ መሣሪያነት እየተቀሰቀሱ መታየታቸው፣

፱. በሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚዘመሩ መዝሙራት፣ የሚታዩ ድራማዎች፣ የሚዘጋጁ ሥነ-ጽሑፎች ያለ አራሚ ለሕፃናትና ለወጣቶች መተላለፋቸው፣

፲. ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚመደቡ የሰንበት ትምህርት ቤት ኃላፊዎች ስለ ወጣቶችና ሕፃናት ግድየለሽ መሆናቸው ሥራውን እንደ ጊዜ ማሳለፊያ እንጂ እንደ መደበኛ ሥራ አለመቁጠራቸው፣

፲፩. በአጠቃላይ በሰንበት ትምህርት ቤቶች በቤተ ክርስቲያን መካከል የአዛዥና የታዛዥነት ሥርዓት እየቀነሰ መሄዱ የመናናቅና የመተቻቸት ልማድ እየተስፋፋ እየጨመረ መሄዱ ናቸው።

ስለዚህ እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው የሚያወጣቸውን ውሳኔዎች መሠረት በማድረግ ሁላችንም ለዚሁ የተቀደሰ ዓላማ በአንድነት ተሰልፈን ወጣቶችንና ሕፃናቱን እንጠብቅ። ኃላፊነታችንን እንወጣ፤ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ደግመን ደጋግመን እናስገንዝብ።

በመጨረሻ ለመግለጽ የምፈልገው የችግሩን አሳሳቢነት በመመልከት መምሪያው የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ መሆኑን ነው። ይኸውም በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ በኩል ቀርቦ በሊቃውንት ጉባኤ የተመረመረው የመዝሙር መጽሐፍ በልዩ ልዩ ምክንያት በመጽሐፍ ደረጃ ታትሞ ገበያ ላይ ባይውልም በማዕከላውያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ወጣት መዘምራን ተዘምሮ በመቅረጸ ድምፅ ተቀርጾ ቁጥር አንድና ቁጥር ሁለት መዝሙራት በመጠነኛ ዋጋ መምሪያው ለአብያተ ክርስቲያናት አሰራጭቶአል። ለወደፊትም በተከታታይ የአማርኛ መዝሙራት በያሬዳዊ ዜማ እያስቀረጸ ከከተማ እስከ ገጠር ከዚያም አልፎ እስከ ባሕር ማዶ ማሰራጨቱን ይቀጥላል።

ለሁሉም ነገር ፈቃደ እግዚአብሔር ይሁን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ✣



# በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ዕይታ የነባር ትምህርት ቤቶች ገጽታ

ከአባ ገሪማ
የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት፣ የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊና የድሬዳዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

## ክፍል ፩



ወደ ነባር ትምህርት ቤቶች ገለፃ ከመግባታችን በፊት የኢትዮጵያውያንን አመጣጥና የመልክአ ምድሩን አቀማመጥ በአጭሩ ለመግለፅ እንሞክራለን።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በምሥራቅ አፍሪካ በዓባይ ሸለቆ ዙሪያ በቀይ ባሕር አካባቢ ጥንታዊ ሥልጣኔ ካላቸው አህጉርና ሕዝብ ጋር ኩታ ገጠም መሆናቸው በቅዱሳት መጻሕፍት፣ በጥንታውያን የታሪክ ሠነዶችና በመልክአ ምድር አቀማመጥም የተረጋገጠ ነው። ኢትዮጵያ ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆለማ የአየር ጠባይ ያላት ሀገር ስትሆን በተፈጥሮ አቀማመጧም ቀርነ አፍሪካ እየተባለች ትጠራለች።

የአፍሪካ ቀንድ ተብሎ የሚጠራው ይህ ክፍል በአየር ጠባይ መለያየት፣ በዕፀዋቱና በእንስሳቱ፣ በሕዝቡ ባህል፣ ቋንቋ ብዛትና ዓይነት በከፍተኛ ደረጃ ሊታይ የሚችል የጂኦግራፊ ክልል ነው።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹ ነዋሪዎች የካም ነገዶች ሲሆኑ ከጊዜ በኋላም የሴም ወገኖች የሆኑ በተለያየ ጊዜና ምክንያት እየፈለሱ ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸው ይነገራል።

ኢትዮጵያ የሚለው ስመ ተጸውዖ በቅዱሳት መጻሕፍትና በጥንታውያን የታሪክ ሠነዶች በብዙ ቦታ ተጽፎ የሚገኝ ቢሆንም ብዙዎቹ ነቢያተ እግዚአብሔር ወደ ዝርዝር ጉዳይ ሳይገቡ ኢትዮጵያና ኩሽ በማለት ኢትዮጵያን በየትንቢታቸው ይዘክራሉ። ቅዱሳን ነቢያተ እግዚአብሔር ኩሽና ኢትዮጵያ እያሉ የጠሩት አሁን ያለንበትን ሀገር ብቻ የሚመለከት ሳይሆን እስከ ግብፅና ሕንድ ውቅያኖስ ድረስ የነበረውን ጭምር የሚያመለክት መሆኑ ግልፅ ነው።

ኦሪት ዘፍጥረት የሁሉንም ነገር አጀማመር የሚነግረን ልዩ መጽሐፍ መሆኑን እንረዳለን። በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፪ በቁጥር ፲፫ ላይ «የሁለተኛው ወንዝ ስም ግዮን ነው፤ እሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከባል» ይላል። በዕብራይስጥ «ኩሽ» በግሪክኛ ትርጉሙ «ኢትዮጵያ» የሚለው የግዛት ክልል በየጊዜው የመስፋትና የመጥበብ ታሪክ ቢያጋጥመውም ማዕከሉ አሁን ያለንበት ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላማው ክፍል መሆኑ ግልፅ ነው።

ኦሪት ዘፍጥረት ስለ ስነ ፍጥረት የቅደም ተከተል ታሪክ በበለጠ የሚናገር ቢሆንም በዚህ የስነ ፍጥረት ታሪክ የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱ የሆነ ድርሻ አለው። ከላይ በታሪኩ ክፍል እንደ ተገለፀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከካምና ከሴም ነገዶች የተዳቀለ መሆኑን ተረድተናል። ይህ ሕዝብ በሐረገ ትውልድ አማካይነት ከሕገ አበውየእነ አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብን እምነት ተቀብሎ ሕገ ኦሪት ከመሠራቷ ፊትና ኋላ አንድ እግዚአብሔርን ብቻ ሲያምለክ የኖረ ሕዝብ ነው። በዚህም ምክንያት ሀገራችን ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር፣ ሕዝቧም ሕዝበ እግዚአብሔር እየተባለ ሲጠራ እንደ ኖረ የሃይማኖት ታሪክ ያስረዳናል።

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» (መዝ.፷፯፥፴፩) በማለት የተነበየው ትንቢት በዘመነ ዳዊት ለነበረው ና ወደ ፊትም እስከ ዓለም ፍጻሜ ለሚሆነው ብቻ ሳይሆን በሕገ አበውም ለነበረው ለኢትዮጵያ ሕዝብ እምነት የተነገረ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ፣

- ሕገ ኦሪትን ከነ ትምህርቱ
- ክህነተ ኦሪትን ከነ ሥርዓቱ
- ጽሌ ኦሪትን ከነ መሥዋዕቱ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፱ኛው ዓመተ ዓለም ማለት በዘመነ ነገሥት በተለይም በንጉሥ ሰሎሞን ዘመነ መንግሥት በኢትዮጵያዊቱ ንግሥት በንግሥተ ሳባ ልጅ በቀዳማዊ ምኒልክ አማካይነት ተቀብሎ እስከ ልደተ ክርስቶስ ድረስ በሕገ ኦሪት ሲመራና ሲተዳደር ኖሯል። ከዘመነ ነገሥት ጀምሮ የአምላካችን እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ጽሌ፣ ታቦተ ጽዮን ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደገባች በታሪክ የታወቀ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖታዊ ባህል በግልፅ እንደሚታየው የእግዚአ



www.ethiopianorthodox.org

ብሔር ቃል ኪዳን መግለጫ የሆነውን ታቦተ ሕጉን ማክበር፣ በበዓላት ቀናት ታቦተ ሕጉን ማውጣት፣ ዑደት ማድረግና የመሳሰለው ሥርዓት የሚፈጸመው ከዚህ ከአሪቱ በወረስነው ሃይማኖታዊ ትውፊት መሠረት ነው።

ኩሽ ወይንም ኢትዮጵያ የሚለው ቃል አሁን ያለንበት የኢትዮጵያ ግዛት መሆኑ በብሉይ ኪዳን የሥልጣኔና የትውፊት አወራረስ ይታወቃል።

ይኸውም:-

ሀ. በአንድ አምላክ ማመን፣

ለ. የሃይማኖት ሕጎችን ማክበር፣

ሐ. በመጽሐፍ ቅዱስ መታወቅ፣

መ. የንዋየ ቅድሳቱ መልክና ዓይነት፣

ሠ. የሕዝቡ ልማድና ትውፊት፣

ረ. የስነ ጽሑፍ ቅርፅና ጠባይ ናቸው።

ይህ ሁሉ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ዛሬ ወደፊት እንዳሉ የሚያሳይ ጉልህ ምልክት ነው።

ከዚህም ሌላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግዝረትን፣ የበዓላት አከባበርን፣ ሥርዓተ ምግብን፣ ሴቶች ከወለዱ በኋላ የሚጠብቁት የመንፃት ሥርዓትንና የመሳሰሉትን ትውፊቶች ከሕገ ኦሪት በመውረስ እስከ አሁን ድረስ በተግባር ሲያውሏቸው ይታያል።

በአጠቃላይ ስለ ጥንታዊት ኢትዮጵያ የተነገረው ቅሪት ሁሉ በመገኘት የሚታየውና ለማስታወስም የሚቻለው በሀገራችን ካለው የባህል፣ የቋንቋና የሃይማኖት ሁኔታዎችና ይዞታዎች ጋር የተገናዘበ በመሆኑ ነው።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በዓለም ስነ ጽሑፍ የታወቁ ቢሆንም በበለጠ የሚታወቁትና በሁሉም ዓይን ጎልተው የሚታዩት «ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር» «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» ከሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር ተያይዞ በተመሠረተው የአምልኮተ እግዚአብሔር ትውፊታቸውና ታሪካቸው ነው።(መዝ.፩፻፲፤፲፤ መጽምሳ.፩፥፯)።

የኢትዮጵያውያን አስተዳደር፣ አስተዳዳግ፣ ትምህርትና ስነ ጥበብ፣ ኪነ ጥበብ በአጠቃላይ የዛሬውን አያድርግውና የኢትዮጵያውያን ሕይወት ይምራ የነበረው ከላይ በተነገረው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነበር።

እንግዲህ ከዚህ ዕይታና ገጽታ በመነሣት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በአፍሪካ ክፍለ ዓለም በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ የረጅም ዘመን ታሪክ ያላቸው ሲሆን ከክርስትናው ታሪክ በፊት በኢትዮጵያ ስለ ነበረው የእምነት አመጣጥና የሥርዓተ አምልኮት አፈጻጸም በብዙዎች ብዙ የተነገረና የተጻፈ ታሪክ ቢኖርም በብዙዎቹ የታሪክ አጻጻፍም ጎልቶ የሚታየው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በሙሴ ሕግና በነቢያት መጻሕፍት ይመሩ የነበረ መሆኑ ነው።

ይህ እስከ አሁን የተነገረው በዚህ እንዳለ ሁኖ የክርስትናው ታሪክ ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ የገባው በአንደኛው መቶ ዓመት በሐዋርያት ዘመን (የሐዋ.ሥራ ፰፥፳፯–፴) ሲሆን የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕልውና በኤጲስ ቆጶስ ተባርኮና ተቀድሶ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም የተጀመረውም በ፬ኛው መቶ ዓመት መሆኑ ግልፅ ነው።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባሏት የታሪክ ዘመናት ሁሉ ኅብረተሰቡን በሁሉም አቅጣጫ በእኩልንት ደረጃ ስታገለግል የነበረች፣ ያለችና የምትኖርም ናት።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ከልደተ ክርስቶስ በፊት በሕገ ኦሪት ከጊዜ በኋላም ሐዲስ ኪዳኑን በመማርና በማስተማር በእነዚህ ዓበይት ሕግጋት በቅደም ተከተል ስመ እግዚአብሔርን በመጥራት፣ ሕገ እግዚአብሔርን በመጠበቅ፣ አምልኮቱንም በመፈጸም ሲመሩ የቆዩ ሀገረ እግዚአብሔርና ሕዝበ እግዚአብሔር ሲሆኑ የዕደገታቸውም አላማና አቋም በዚሁ ዓይነትና መጠን የተገነባ ሆኖ ከአንድ ትውልድ ወደ ተከታዩ ሲወርድና ሲወራረድ መጥቶ አሁን ከአለበት ደረጃ ላይ ደርሶ ይታያል።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በእነ አፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት በዚያን ጊዜ በዓለም ኃያላን ከሚባሉት ከቢዛንታይን፣ ከፋርስ ባቢሎንና ከመሳሰሉት በኃይል፣ በጥበብ፣ በብልፅግና፣ በስፋት ይወዳደሩ የነበረ መሆኑን ከታሪክ እንረዳለን።

ቤተ ክርስቲያን ከማዕከለ ምድር ቀራንዮ ተነሥታ እስከ ዓለም ዳርቻ የደረሰችው በትምህርት ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር ውሎና አድሮ እንደ ተነሣ ሐዋርያቱን «ሑሩ ወመሐሩ...» «ሂዱና አስተምሩ» ነው ያላቸው (ማቴ.፳፰፥፲፱)።

ነባር ትምህርት ቤቶችን የመሠረቶች ቤተ ክርስቲያን እንደ ሆነች የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይነግረናል።

በዓለም ታዋቂነትን ያተረፉ፣ የዓለም ሊቃውንትን ያስገኙ ጥንታውያን፣ መንፈሳውያን ዩኒቨርስቲዎችም የተመሠረቱት በቤተ ክርስቲያን መሆኑን እንረዳለን። ከዚህም አንፃር ቤተ ክርስቲያን የሁሉ ነገር አስተማሪና ጀማሪ መሆኗ የታወቀ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን:-

ሀ. ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት፣ በትንቢቱ ፍጻሜም



ለ. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረውን፣

ሐ. ሐዋርያት የተከተሉትን፣

መ. በሦስቱ ጉባኤያት የተወሰኑትን ማለት በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት እየተመሩ ፫፻፲፰ ቅዱሳን አበው በ፫፻፳፭ ዓ.ም በኒቅያ፣ ፩፻፶ ቅዱሳን አበው በ፫፻፹፩ ዓ.ም በቁስጥንጥንያ፣ ፪፻ ቅዱሳን አበው በ፬፻፴፩ ዓ.ም በኤፌሶን ያስተማሩትንና የወሰኑትን ከእነዚህም ቅዱሳን አበው ትምህርትና ውሳኔ ጋር የሚተባበሩ በየጊዜው የተነሡ ቅዱሳን አበው ያስተማሩትንና የእነርሱንም የተቀደሰ ሥርዓታቸውን አምናና ተቀብላ ታስተምራለች።

የቤተ ክርስቲያናችን የትምህርተ ሃይማኖቷ፣ የሥርዓቷ፣ የቀኖናዋ መነሻዎች እነዚህ ከዚህ በላይ የተነገሩት ናቸው።

ከዚህም ጋር በአራተኛው መቶ ዓመት በቅዱስ ፍሬምናጦስ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን የተተረጎሙትን ቅዱሳት መጻሕፍት መነሻ በማድረግ በይቀጥላልም በአምስተኛው መቶ ዓመት ተሰዐቱ ቅዱሳን ከቢዛንታይን ግዛት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ቅዱሳት መጻሕፍትን ከዕርዕና ከመሳሰሉት ጥንታውያን የሥልጣኔ ቋንቋዎች ወደ ግዕዙ ብሔራዊ ቋንቋ የተረጎሙበት፣ ገዳማዊ ሕይወት የተመሠረተበት፣ የቤተ ክርስቲያናችን የውዳሴ፣ የቅዳሴ፣ የዝማሬ ጣዕመ ዜማ ስልቶች በፈቃደ እግዚአብሔር በኢትዮጵያዊው አባት በቅዱስ ያሬድ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ የተደረሱበት የስነ ጽሑፍም ውበት የታየበት ወቅት ነበር።

ከዚህም የተነሣ ቤተ ክርስቲያናችን ከሃይማኖት በመነጨ ያስተዳደር ዘይቤ ለብዙ ዘመናት ሕዝቡን በሃይማኖት አስተባብራ ለነፃነቱ፣ ለሃይማኖቱና ለአንድነቱ እንዲታገል ብዙ ድካምንና ጥረትን አድርጋለች።

ከዚህም አሠራር የተገኘው ውጤት ሀገር የዳበረበት፣ ዳር ድንበር የተከበረበት፣ ወገን የኮራበት፣ ነፃነት የተጠበቀበት ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ህልውና ታውቆ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሀገሪቱ ሃይማኖት ከሆነበት ከአራተኛው መቶ ዓመት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያኒቱ ባሏት የታሪክ ዘመናት ሁሉ፣

የኢትዮጵያን ሕዝብ በአፍሪካ ክፍለ ዓለም የራሱ የሆነ ደፊልና ሥነ ጽሑፍ የራሱ የሆነ ፊደል ያለው የቋንቋ ባለቤት ያደረገች፣

ኢትዮጵያንም በዓለም ፊደል ካላቸው አህጉር በእኩልነት ደረጃ ያስቀመጠች፣

ጽሑፍን፣ ሥነ ጽሑፍን፣ ሥነ ጥበብን፣ ኪነ ጠበብን፣ አሐዝንና የቁጥር ሥልትን ያበረከተች፣

የዕለታት፣ የአውራህ፣ የዓመታትንና የዘመናትን አቆጣጠር ስልት በመጽሐፍ ጽፋ ያስተማረች፣ በአጠቃላይም የትምህርትና የሥነ ጥበብ ባለቤት ሆና በእምነት ላይ በተመሠረተ ትምህርትና የአስተዳዳር ዘይቤ ኅብረተሰቡን አንድ አድርጋ በሁሉም አቅጣጫ በእኩልነት ደረጃ ስታገለግል የነበረች፣ ያለችና የምትኖር ጥንታዊት፣ ሐዋርያዊት፣ ብሔራዊትና ታሪካዊት እናት ቤተ ክርስቲያን ናት።

(ይቀጥላል)

## ጥንታዊ የሹመት አሰጣጥ

በጥንታዊቷ ኢትዮጵያ የሹመት ማዕርግ አሰጣጥ ተሹዋሚው ከሚመደብበት ቦታ ጋር የተያያዘ ነበር። ከዚህ ውጭ ለአንዱ ሰው ፊታውራሪ፣ ደጃዝማች ወዘተ. ተብሎ ማዕርግ መስጠት አይቻልም ነበር። ለአብነት የጥቂቶችን እነሆ:-

ባሕረ ነጋሽ..............ለኤርትራ
ንቡረ እድ................ለአክሱም
ዋግሹም...................ለዋግ
ፊታውራሪ................ለወልቃይት
ደጃዝማች.................ለቋራ
ጃንጥራር..................ለአምባሰል
መርእድ አዝማች.........ለሸዋ
አዛዥ......................ለአገው ምድር (ጉጃም)
ወሰን አዝማች............ለአማራ ሳይንት
ራስ........................ለትግራይ

(ከኅብረ ብዕር መጽሐፍ የተወሰደ)

«...እውነት እላችኋለሁ፣ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም። እንግዲህ እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው።

እንደዚህም ያለውን አንድ ሕፃን በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል፣ በእኔም ከሚያምኑ ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር።» (ማቴ.፲፰፥፫–፮)

✣ ✣ ✣

«ፍቅር ያስታግሳል፣ ፍቅር ያስተዛዝናል፣ ፍቅር አያቀናናም፣ ፍቅር አያስመካም፣ ፍቅር አያስታብይም፣ ብቻዩን ይድላኝ አያሰኝም፣ አያበሳጭም፣ ክፉ ነገርን አያሳስብም፣ የማይገባውን አያደርግም...» (፩ቆሮ.፲፫፥፬–፮)



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ሃይማኖት



የሰው ልጅ ሰውኛውን ለመኖር ሲመጣ ባዶውን አልመጣም እሳተ ሕግ በልቡናው ተጻፍኖለት፣ የክፉና የበጐ መለያ ባህርይ በሰውነቱ ተስማምቶት...ወዘተ. ነው።

በእግዚአብሔር ምሳሌ መፈጠሩም እንደ መላእክት ህያው ሆኖ በሕገ ልቡና ተገዝቶ ሊኖር እንጂ በመጽሐፍና በጸሐፊ፣ በትምህርትና በአስተማሪ ተደግፎ ሊኖር አልነበረም። በንጹህ ባህርዩ ጽንት፣ ሁከትና ኃጢአት መንጭተው ሊአጠቁሩት አልነበረም፣ ንጹህ ባህርዩን ጠብቆ ከኖረ የግብር ጠላት የማይነሳበት ነፃ ፍጡር ነው።

በሥልጣንም የልጅነት (ልጅ የመሆን) ሥልጣን የተሰጠው፣ በገነት እንዲኖር የተፈቀደለት፣ ቅሩብ ኀበ እግዚአ· የሆነ ባለሟል ነበር። በሞት እንደ ቅጠል ሊረግፍ፣ በመሬት ጉያ ሊወተፍ አልነበረም። (ሄኖክ ፲፱፡ ፳፬) በምድረ ገነትም ሲኖር የሐልዮ፣ የነቢብና የገቢር ኃጢአት አልተገኘበትም። በንጽሐ ጠባይ ቢገኝ ኑሮ ማርጀት፣ መታመምና ሞት ሳያውቁት ሺህ ዘመን ሊመላው ግዘፉ ቀርቶ ርቀቱን ገንዘብ በማድረግ ከዓለመ ሥጋ ገነት ወደ ዓለመ ነፍስ መንግስተ ሰማይ ሊአርግ ነበር። በልቡናው የተጻፈነለትን ሕግ በመተው ለጠላቱ ስለተረታ ሁሉንም አጥቶ ሞትና መቃብር ሲቀባበሉት ኖረ። ፈጣሪውንም ሰውን በመፍጠሩ እስኪአሳዝነው ድረስ ደረሰ። (ዘፍ.፫፥፳፪፤ ዘፍ.፮፥፮–፯) ይሁን እንጅ ሰው (አዳም) በአለ አእምሮ ነውና መውደቁን አወቀ፣ አቅሙን ተረዳ፣ ተጸጸተ ጸሎቱን (ልመናውን) ወደ ፈጣሪው አቀረበ። ቸር ይቅር ባይ ፈጣሪውም ልመናውን አይቶ፣ መጸጸቱን ተረድቶ፣ ይቅር

## ሳታቋርጡ ጸልዩ

(ተሰሎ.፭፥፲፯–፲፰)

ይለው ዘንድ ወሁነ። የውሣኔውንም ፍንጭ በእየጊዜ የሚናገሩ ነቢያት ተነሱ። (ኢሳ.፯፡፲፬፤ ዘጸ.፫፡፪፤ መሳ.፮፥፴፯፤ ዳን.፪፥፴፬) ለአባቶቻችን በነቢያት አድሮ ተናገረ። (ዕብ.፩፡፩) በሰማይ በምድር ያለው ሁሉ ይታደስ ዘንድ የሚታደስበት ጊዜ ሲደርስ ልጁን በሥጋ ላከው። (ኤፌ.፩፡፲፤ ገላት.፬፥፬) የአባቶቻችን ምኞት ሁሉ ህያው ሆነ። ሰውና እግዚአብሔር፣ ሰውና መላእክት፣ ነፍስና ሥጋ፣ ሕዝብና አሕዛብ አንድ ሆኑ። ቁራኝነት ጠፋ። የሰው መስዋዕቱ፣ ጸሎቱ፣ ልመናውና በጐ ሥራው ሁሉ ወደ ፈጣሪው ደረሰ። አምነው የሚጸልዩ ጸሎት ሁሉ ሰመረ። ድውይ ፈወሰ፣ ህሙም አዳነ (ያዕ.፭፥፲፭።)

ይህ ይባል እንጂ አምነው የሚጸልዩት ጸሎት ሁሉ በእየጊዜው ግዳጅ ሲፈጽም፣ ችግርን ሲአስወግድ መኖሩ ግልጽ ነው። በጸሎቱ ጸሎተኛ በሃይማኖቱ ያፈረ ሃይማኖተኛ የለም። ነቢዩ ኤልያስ ልጅነት ባልተሰጠበት ጊዜ የነበረ አቢይ (ታላቅ) ነቢይ ነው። ይሁን እንጂ በጸለየው ጸሎትና በአቀረበው መስዋዕት አላፈረም። በሰዎቹ ክፋት አቅማቸውን ለማሳወቅ ዝናም ለዘር፣ ጠል ለመከር ከመስጠት እንዲከለከል አደረገ ሆነለትም። (፩ነገ.፲፯፥፩) አቅማቸውን ከአሳወቀ በኋላ ዝናም እንዲዘንም አደረገ። (፩ነገ.፲፰፥፵፪) ይህ ሁሉ እንዲፈጸም የሆነ በጸሎት ኃይል ነው፤ የጸሎትን ኃይል አድራጊነት ያስተምረናል፣ ጸሎት ለማኀበር፣ ለግለሰብእ...ወዘተ. ይጸለያል (ያዕ.፭፥፲፯።) በሃይማኖት ሆኖ ለወንድም የሚጸለየው ጸሎት ሁሉ እራስንም ይጠቅማል።

ጸሎት የሰውና የእግዚአብሔር መገናኛ ህቡዕ መሣሪያ ነው። (ማቴ.፮፥፯) ሰው በእግዚአብሔር ምሳሌ ስለ ተፈጠረ ከፈጣሪው ጋር መገናኘት አለበት። ጸሎት ሲባል የሰው በጐ ሥራዎች ሁሉ ጸሎት ይባላሉ። ለምሳሌ ስግደት፣ ምዕዋት፣ ትምህርት፣ ምስጋና ንስሐ:- የመሳሰሉት ሁሉ ጸሎት ይባላሉ። እነዳንኤል ከአፈ አንበሳ ሠለስቱ ደቂቅ ከእቶነ እሳት የዳኑ በጸሎት ነው። (ትንቢተ ዳንኤል ፫፥፳፬፤ ፮፥፳) በእየጊዜው ጾመ ድህነት እያልን የምንናገራቸው ጾሞች ለምሳሌ ጾመ ረቡዕና ጾመ አርብ ናቸው። እኒህም ሁለት ጾሞች በሁለቱ ሴቶች የተከናወኑ ድንቅ ተአምር ተደርጐ የተፈፀሙ ጾሞች ናቸው። (መጽሐፈ ዮዲት ፲፫፥፮፤ መጽሐፈ አስቴር ፮ና ፰ ተመልከት።) ጸሎት ከኃያል እግዚአብሔር ብርታትን ለማግኘት የምንጠይቅበት ልዩ ማመልከቻ ነው። የጸሎት ሥነ ሥርአትና ዝግጅት ይኑረው እንጂ ተፈጻሚነቱ በተሰበረ ልብ እና ትህትናን በተላበሰ ውስጣዊና ውጫዊ የተግባር ሚዛን ሲተካከል ነው። (ዮሐ.፱፥፳) በጸሎት ማንኛውም ተግባር የምንፈጽም ሲሆን በጸሎት የማይፈጸምልን ውጤት እንደሌለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነግሮናል (ሉቃ.፲፰፥፩።) ጸሎት ፍሬአማ የሚሆነው በሚከተለው መንገድ ሲቀርብ ነው። (ዕብራውያን ፲፩፥፮፤ ኤር.፳፥፫) ያለ ሃይማኖት መጸለይ ያለ ጸሎት አፈጻጸም እንደማይገኝ ብዙዎች መጻሕፍት ተባብረዋል። የጸሎታችንም ፍጻሜ ፈቃድህ ይሁን በማለት መሆን አለበት። ምክንያቱም ለእኛ ከእኛ እሱ ቀራቢ ስለሆነ ነው። (ማቴ.፮፥፲፬) ደግሞም በስልቹነት ባህርይ አይደለም። (ሉቃ.፲፩፥፰) በሕግ፣ በአምልኮት ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው አስቀድሞ ሊአምን ይገባል። በዕብራውያን መልእክት በ፲፩፥፮–፴ ቅዱስ ጳውሎስ የጠቀሳቸው ሁሉ አስገራሚ ሥራ የሠሩ በሃይማኖት እንደ ሆነ በማያሻማ ሁኔታ ያስረዳል። የጸሎትና የሃይማኖት ጥምረት ሊከሽፍ የማይችል መሣሪያ መሆኑ ማንኛውም ሰው ሊረዳ ይገባል።

የዘመናችን ትውልድ ያልሰጡትን በመሻቱ፣ የተሰጠውን እያጣ፣ ከሕግ ጥበቃ በመውጣቱ፣ ለጠላት እየተጋለጠ፣ የተሰጠውን የእድሜ ጣሪያ ሳያይ በከንቱ ከዓለም ሲሰናበት ይገኛል። ጸሎቱና እምነቱም ያልተጣጣመ በመሆኑ ለተለያዩ ችግር እጁን ሰጥቶ፣ አሳዛኝ አረንቋ ውስጥ ተዘፍቆ፣ ለችግር፣ ለርሃብ፣ ለእርዛት፣ ለድንቁርናና ለስደት ምርኮኛ ሆኖ ይገኛል። «የእሱን ነገር ለእርሱ መንገር» እንደ ተባለው በጥበበ እግዚአብሔር ሆኖ ተግሣፁን እየተቀበ መኖር ከእግዚአብሔር ቁጣና ከሰው ሰራሽ ችግር መዳን ይቻላል (መዝ.፪፥፲።) በሃይማኖት ሁነው (ጸንተው) የሚጠይቁት ሁሉ ነገ አገርን፣ ወገንን፣ ከልዩ ልዩ ችግር ያድናል መዝ.፵፱፥፲፭፤ ዮሐ.፫፥፭–፲። ለዚህ ደግሞ ሳያቋርጡ መጸለይ ይገባል (ተሰሎ.፭፥፲፯–፲፰) ✣

# እግዚአብሔር

እግዚአብሔር ሩቅ ነው፣ ጥበቡ አይታይምና፤

እግዚአብሔር ቅርብ ነው፣ ቶሎ ይሰማልና፤

እግዚአብሔር መኰንን ነው፣ ቶሎ ይፈርዳልና፤

እግዚአብሔር እንግዳ ነው፣ ቶሎ ወሬ ይሰማልና፤

እግዚአብሔር ትሑት ነው፣ ሰውን አይንቅምና፤

እግዚአብሔር መሐሪ (ርኅሩኅ) ነው፣ ይቅር ይላልና፤

እግዚአብሔር ሐኪም ነው፣ ሁሉን በጥበብ አድርጓልና፤

እግዚአብሔር ምስጉን ነው፣ ፀሐይን፣ ጨረቃን ፈጥሮአልና፤

እግዚአብሔር ክቡር ነው፣ ሰማይና ምድር የርሱ ናቸውና፤

እግዚአብሔር ባለጸጋ ነው፣ ለሁሉም ይመግባልና፤

እግዚአብሔር ረቂቅ ነው፣ አይጨበጥምና፤

እግዚአብሔር ግዙፍ ነው፣ በዓለሙ ሁሉ ሞልቷልና፤

እግዚአብሔር ብሩህ ነው፣ ጨለማ የለበትምና፤

እግዚአብሔር ኃያል ነው፣ የሚቋቋመው የለምና፤

እግዚአብሔር እሳት ነው፣ እጅግ ያስፈራልና፤

እግዚአብሔር መካር ነው፣ መጻሕፍትን ሰጥቶናልና፤

እግዚአብሔር አባት ነው፣ አሳድጎናልና፤

እግዚአብሔር ወንድም ነው፣ ሰው ሆኖዋልና፤

እግዚአብሔር ወዳጅ ነው፣ የሆዱን ነግሮናልና፤

እግዚአብሔር አገር ነው፣ እንኖርበታለንና፤

እግዚአብሔር ማርና ሱካር ነው፣ ይጣፍጣልና፤

እግዚአብሔር ገናና ነው፣ የሚያህለው የለምና፤

እግዚአብሔር ትልቅ ነው፣ ስፍራ አይበቃውምና፤

እግዚአብሔር ጥልቅ ነው፣ በዋና አይገኝምና፤

እግዚአብሔር ፋሲካ ነው፣ ለሁሉ ታርዷልና፤

እግዚአብሔር ዓመት በዓል ነው፣ ለሁሉ ደስታ ነውና፤

እግዚአብሔር ጨው ነው፣ ሁሉን ያጣፍጣልና፤

እግዚአብሔር ክረምት ነው፣ ሁሉን ያበቅላልና፤

እግዚአብሔር አይጠረጠርም፣ ሁሉን ያውቃልና፤

እግዚአብሔር አይዘነጋመ፣ በሁሉም ድካም የለበትምና፤

እግዚአብሔር አይሰጋም፣ የሚሸረው የለምና፤

እግዚአብሔር የሰው ሎሌ ነው፣ በክረምት ለማብቀል በበጋ ለማብሰል የተዘጋጀ ነውና፤

እግዚአብሔር እንግዳ አይደለም፣ ከጥንት የነበረ ነውና

ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ፓንት ለነበረ፣ አሁንም ላለ ኋላም ለሚኖር አሜን።

መጽሐፈ ጨዋታ – ሥጋዊ ወመንፈሳዊ

ከጠበ ኢትዮጵያዊ – ፲፰፻፺፮ ዓ.ም



www.ethiopianorthodox.org

# እኔም ወጣት ነበርኩ

## «ከማስተማር (ከወንበሩ) የሚለየኝ ሞት ብቻ ነው»

(መልአከ ሰላም ገብረ እግዚአብሔር ኃይሉ)

ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር

**መ**ልአከ ሰላም ገብረ እግዚአብሔር ኃይሉ የ፹፪ ዓመት አዛውንት ናቸው። የደብረ አባይ ቅዳሴ ምስክር (ተጠያቂ) የሆኑት እኚህ አባት ላለፉት ፳፰ ዓመታት መቀሌ በሚገኘው ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል በአስተዳዳሪነትና በመምህርነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ከጨቅላነታቸው ጀምረው ዕድሜያቸው በመማርና በማስተማር ነው ያሳለፉት።

ዛሬም ቢሆን ዙሪያቸውን ከአንድ መቶ በላይ በሆኑ ደቀ መዛሙርት ተከበው ነው የሚውሉት። ንግግራቸው ቁጥብ፣ ምሥጢራቸው ረቂቅ፤ ዕውቀታቸው ምጡቅ ነው። ግርማ ሞገሳቸው፣ ረድኤታቸው፣ አበባ ንብን እንደሚማርክ ያህል ሰውን ይስባል። መልአከ ሰላም ቁጥራቸው የበዛ ደቀ መዛሙርት አፍርተው ለቁም ነገር አድርሰዋል። ዛሬም እያፈሩ ይገኛሉ። መልአከ ሰላም ገብረ እግዚአብሔር ኃይሉን ያነጋገርናቸው ባለፈው ዓመት (ጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም) ነበር። ወጣቶች ከቃለ ምልልሱ ጥሩ ትምህርት ታገኛላችሁ ብለን እናምናለን? መልካም ንባብና ተሞክሮ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በመጀመሪያ የልጅነት ጊዜዎ ምን ይመስል እንደ ነበር ቢያጫውቱን?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – ተወልጄ ያደግኩት አድዋ አጠገብ ከሚገኘው መዝራእተ ክርስቶስ ከሚባለው ገዳም አካባቢ ነው። የልጅነት ጊዜዬን ያሳለፍኩት በትምህርት ቤት ነው። ትምህርት የጀመርኩት ከእናቴ ወንድም (አጎቴ) ከቄስ ገ/ሕይወት ወ/ማርያም ዘንድ ነበር። ከዛ መሪጌታ ወ/ጊዮርጊስ ከሚባሉት መምህር ዘንድ ፏጁ ትምህርቴን ቀጠልኩ። ይሁንና ትምህርት ቤቱ ከቤታችን አጠገብ ስለ ነበር ቤተሰቦቼ ሥራ አግዘን እያሉ ስለሚረብኩኝ ትምህርቴን በሚገባ ለመከታተል ብዬ ወደ ደብረ አባይ ገዳም ሄድኩኝ። አብዛኛው ትምህርቴን የተማርኩት ደብረ አባይ ገዳም ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በደብረ አባይ ገዳም ለምን ያህል ጊዜ ቆዩ?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አሥራ ሁለት ዓመታት ያህል ቆይቻለሁ። በእነዚህ ዓመታት የቃል ትምህርትን አጠናቅቄ ቅኔ እስከ መቀኘት ደርሼ ነበር። በኋላ መምህራችን የነበሩት መሪጌታ መጽሐት እኔን ተከተሉኝ ብለው ወደ ተምቤን ሄዱ። የተወሰን ተማሪዎች ግን ወደ አማራ ሀገር መሄድ ይሻላል ብለን ወደ ጐንደር ተሻገርን። ከዛ ጭልጋ አውራጃ በተለይ ደበጋ ሚካኤልና ደበጋ ማርያም ከሚባል ሥፍራ ከታዋቂው ሊቅ ከመሪጌታ አክሊሉ ዘንድ ለአምስት ዓመታት ቅኔ ከነ አገባቡ፣ ፍትሐ ነገሥትና ዳዊት ከተማርኩና ካጠናቀቅኩ በኋላ ወደ ገዳሜ (ደብረ አባይ) ተመልሼ መጣሁ።

እንደ ተመለስኩም ቅዳሴውን በሚገባ አጠናቀቅኩ። መምህራችን መምህር የኋላሸት መርሻ ይባሉ ነበር። በሁሉም የተዋጣላቸው ሊቅ ናቸው። ከቅዳሴ ሌላ የብሉይና የሐዲስ፣ የአቡሻከር መምህር ነበሩ። ቅዳሴውን ከልሼ እንዳጠናቀቅኩ በረዳትነት እያስተማርኩኝ እንደ ገና መጽሐፈ ሐዲሳትን እየተማርኩ ለሰባት ዓመታት ያህል የኔታ የኋላሸት ዘንድ ቆየሁ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከዛስ?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – አንድ ቀን ዘመዶቼን እጠይቃለሁ ብዬ ወደ ትውልድ ሀገሬ መጣሁ። ከዛ ቤተሰቦቼ ሁል ጊዜ ተራርቀን ከምንኖር እዚሁ ተወልደህ ካደግክበት ገዳም ለምን አትቀመጥም? አሉኝ። በዛው ላይ የገዳሙ መነኮሳት እዚህ ሆነህ አስተምረን ብለው ጠየቁኝ። እኔም እሺ ለአንድ ዓመት ያህል ልቆይላችሁ አልኩኝና ማስተማር ጀመርኩኝ። ሳይታሰብ ከምጠብቀው በላይ ተማሪ መጣ። በዛው ላይ የገዳሙ ማህበር ጥሩ ነበር። እኔም ያን ሁሉ ተማሪ በትኜ መሄዱ ደስ ስላላለኝ ለአሥራ ሁለት ዓመታት እዛው ሳስተምር ቆየሁ፤ በዚህን ጊዜ ካስተማርኩዋቸው መካከል ለቅስና ለዲቁና የደረሱ በጣም ብዙ ናቸው። ከመካከላቸው ለመምህርነት ደረጃ የበቁ ወንበር ዘርግተው የሚያስተምሩም አሉ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከመዝራእተ ክርስቶስ ገዳም እንዴትና ለምን ለቀቁ?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – ከገዳም ለመውጣት ፍላጐቱም ሃሳቡም አልነበረኝም። መምህሬም ቢሆኑ ከገዳም እንዳትወጣ ነበር የሚሉኝ። ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በተለያዩ ገዳማትና አድባራት የሚገኙ መምህራንና መነኮሳት ተማሪዎችን እየመረጡ ያሰባስቡ ነበር። ገና የአክሱም ንብረ እድ እያሉ የኔን ሁኔታ በዝና ሰምተው ኖሮ መምህራችንን እርሱን ይስጡኝ ከእኔ ጋር ይቀመጥ ይሉዋቸው ነበር። መምህሬ ግን ለወደፊቱ በእኔ ወንበር እኔን ተክቶ የሚቀመጠው እርሱ ስለ ሆነ አይሆንም እያሉዋቸው ቆዩ።



በኋላ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ጳጳስ ሆነው የመቀሌ መንፈሳዊ ኮሌጅን በማሠራት ላይ በነበሩበት ወቅት ፈልገው አስፈልገው አገኙኝና ወደ አክሱም አስጠሩኝ፤ የነበርኩበት ገዳም ማህበረ መነኮሳትም ሁሉም ተሰብስበው መጡና «እርሱን ከሚወስዱብን በርሱ ምትክ ሃያ መነኮሳት መርጠው ይውሰዱ» ብለው አቤት አሉ። ብፁዕነታቸው ግን አይሆንም አዲስ በሚሠራው ትምህርት ቤት ያስተምራል ብለው በአቋማቸው ጸኑ።

እኔ ግን «ብፁዕ አባታችን ይትርታ ያድርጉልኝ አይሆንም የመምህሬን ቃል እንዴት እሽራለሁ። እኔ ባለሁበት ማህበሩን ሰብስበው ከእኔ በኋላ ቅዳሴንም ሆነ መጽሐፍ በተመለከተ የምትጠይቁትና የሚያስተምራችሁ እሱ ነው አንተም ወንበሬን ይዘህ ከገዳም ሳትወጣ አስተምር ብለውኛል» አልኩዋቸው። በመጨረሻ ግን መቀሌ ድረስ አስጠርተው ታላላቅ አባቶችና ሊቃውንት ባሉበት ‹እሱ እኔ ዘንድ መጥቶ ደጅ መጥናት ሲገባው እኔ ደጅ ብጠናው፤ ብለምነው እምቢ ብሎኛል እዚህ እኔ ጋ ሆኖ እንዲያስተምር ጠይቁልኝ› አሉዋቸው። እነርሱም ከጳጳስ በላይ ማን መጥቶ ሊለምንህ ነው እሺ በል ባይሆን በኋላ በጀትህን ይዘህ ትመለሳለህ አሉኝ ከዛ ሳልወድ ከነበርኩበት ገዳም ሁለት መነኮሳትን ይዤ መጣሁ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – መቀሌ እንደ መጡ በምን ሥራ ላይ ነበር የተመደቡት?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – ቅድስት ማርያም መንበረ ጵጵስና የማህበራዊ ኑሮ ትምህርት ቤት ነበር። እዛ ነበር የማስተምረው። እዛ ለሰባት ዓመታት አስተምሬአለሁ። በዚህ ሥራ ላይ እያለሁ የደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል (ይህ መንፈሳዊ ኮሌጅ ያለበት ማለት ነው) ቤተ ክርስቲያን ግንባታ ተጀመረ። ከዛ የበላይ ተቆጣጣሪ ሁን ተብዬ በውሳኔ ወደዚህ ተላኩኝ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – አሁንም የዚህ ደብር አስተዳዳሪ ሆነው እየሠሩ ነው ያሉት፣ ለመሆኑ በአስተዳዳሪነት መሥራት የጀመሩት ከመቼ ጀምሮ ነው?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – ወደዚህ ከመጣሁ ወደ ሃያ ስምንት ዓመት ይሆነኛል። ደብሩ ደብረ ሰላም ተብሎ እኔም መልአከ ሰላም ተብዬ አለቃ ሆኜ የተሾምኩት በብፁዕ አቡነ ኤፍሬም በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም ነው። ከዛ በፊት መምህር ገብረ እግዚአብሔር እየተባልኩ ነበር የምጠራው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በአንድ ደብር ለሠላሳ ዓመታት ያህል በኃላፊነት መቆየት የተለመደ አይደለም፣ በዛው ላይ እርስዎ ከማስተማር ሥራም አልተለዩም፣ ለመሆኑ በዚህ ረዥም ጊዜ ውስጥ በሥራዎ ያጋጠምዎት ችግር የለም?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – እግዚአብሔር ይመስገን ያጋጠመኝ ከባድ ችግር የለም። ምክንያቱም በዚህ ደብር የሚያገለግሉት ካህናትም ሆኑ መነኮሳት ብዙዎቹ እኔ ያስተማርኩዋቸው ናቸው። በሥራ ሂደት መጠነኛ ችግር ቢፈጠርም እቋቋመዋለሁ። ማስተማር ላልከው አሁንም በማስተማር ላይ ነኝ። ሌላው አለቃ ከሆንኩ ምን ቸገረኝ ሊል ይችላል። እኔ ግን የቃለ እግዚአብሔር ፍቅር ስላለኝ ማስተማሩ እንደ ትሩፋት ነው የምቆጥረው፤ ወንበሩም የጠበቀ ወንበር ነው። አሁንም ቢሆን ከ፩፻ በላይ ደቀ መዛሙርት አሉኝ። በአጭሩ ከማስተማሩ ሥራ የሚለየኝ ሞት ብቻ ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በአብዛኛው ቅዳሴ እንደሚያስተምሩ ይታወቃል። ይሁንና እርስዎ በሐዲሳት፣ በቅኔና በባሕረ ሐሳብ የዳበረ ዕውቀት እንዳለዎት ነው የሚነገረው፣ ታድያ ከቅዳሴ ሌላ ምን ያስተምራሉ?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – ልክ ነው በዋናነት ቅዳሴ ነው የማስተምረው፣ መምህራን ያወጣሁትም በቅዳሴ ነው። ይሁንና አንድ ካህን ባሕረ ሃሳብም ማወቅ አለበት ብዬ ስለማምን ባሕረ ሀሳብ አስተምራቸዋለሁ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – የቅዳሴ ነገር ከተነሳ አንዳንድ ሰዎች ቅዳሴ የሰሞነኛ እንጂ የሊቃውንት ሥራ አይደለም ሲሉ ይሰማል፣ በእርግጥ ቅዳሴ የሰሞነኛ ሥራ ነው?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – (ፈገግ በማለት) እንደዚህ የሚሉት ያልተማሩ ይሆናል። ቅዳሴን የደረሱት ሊቃውንት ናቸው፣ ምሥጢርነቱ ያየን እንደ ሆን ከሁሉ የበለጠ ነው። ዜማውም ቢሆን የሊቃውንት ነው፤ ዜማውን የደረሰው እኮ ቅዱስ ያሬድ ነው። በዚህ ዓይነት ቅዱስ ያሬድ ሰሞነኛ ሊሆን ነዋ! ከመዋስዕት፣ ከዝማሬ፣ ከምዕራፍ፣ ከጾመ ድጓ አንድ ክፍል ቅዳሴ ነው። ቅዳሴን ከነጣዕሙ፣ ከነዜማው፣ ከነ ምሥጢሩ የሚያውቁት እንደዚህ አይሉም።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ጥያቄውን በሌላ መልክ ላቅርብልዎት፣ ብዙዎች ካህናት የቅዳሴን ምሥጢርና ጣዕም ቀርቶ ሁሉንም የቅዳሴ ዓይነት ለይተው አይችሉም እንዲያውም ጥንታዊውና ትክክለኛው የቅዳሴ ሥነ ሥርዓት እየተረሳ ነው፣ የሊቃውንት መሆኑ ቀርቶ የሰሞነኛ ሥራ እየሆነ መጥቷል ነው። በዚህ ላይ የእርስዎ አስተያየት ምንድነው?





www.ethiopianorthodox.org

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – ይህ መነኩሴ ነኝ፣ ቄስ ነኝ የሚል ሁሉ ለመቀደሻና ለመወደሻ ያህለ ብሎ የሚቀድሰውን ቀዳሽ አልለውም። ጠለቅ ብሎ ድርቡ፣ አንቀጹ፣ እዝሉ፣ ግዕዙ፣ የሚላላው፣ የሚጠብቀው፣ አብነቱ፣ ልኩ፣ ተቃራኒው ለይቶ የሚያውቅ የዋለበት ማለቴ ነው። በእርግጥ በዚህ በኩል አሟልተው የሚገኙ የተወሰኑ ናቸው። እንደ እኔ እንደ እኔ ግን የሚቀድስ ሰው በቅድሚያ ቅዳሴን አጠናቅቆ ሊያውቅ ይገባል። የውትድርና ትምህርት ያላወቀ ወታደር ሊሆን እንደማይችል ሁሉ መቀደስ ያለበት ቅዳሴን በሚገባ ያወቀ ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – አሁንም ከዚሁ ከቅዳሴ ሳንወጣ አንድ ጥያቄ ልጠይቅዎ፣ የደብረ አባይ ቅዳሴ ከሌላው የሚለየው በምን ነው? ይህ የቅዳሴ ዓይነትስ ለመጀመሪያ ጊዜ የት ነው የተጀመረው? አመጣጡና እድገቱን ቢገልጹልን?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – የዚህ ቅዳሴ ዓይነት ምንጭ በደብረ ታቦር አካባቢ ሶለ ልኩላ በተባለ አካባቢ እንደ ሆነ ነው የሚነገረው። ቤተ ልሔም አካባቢ ይምስለኛል። ታድያ በአንድ ወቅት በዚህ አካባቢ በሽታ ገብቶ እዛ የነበሩት ሊቃውንት አለቁ። ከእነዚህ መካከል ግን የኔታ ወልደ ኢየሱስ የተባሉ አባት በሕይወት ለመትረፍ ቻሉ። እኚህ አባት በነበሩበት ቦታ ለመቆየት ስላልቻሉ ወደ ደብረ አባይ ገዳም (ትግራይ) መጡ። እንደ ደረሱም ትንሽ ዕውቀት አለችኝና እንዳስተምር ፍቀዱልኝ ብለው ማህበሩን ይጠይቃሉ። እዛ የነበሩት ባላባቶች ግን አንቀበልም ይሉዋቸዋል። የኔታ ወልደ ኢየሱስ ደብረ አባይን ትተው ወደ አክሱም አመሩ። እዛ እንደ ደረሱም ለደብረ አባይ መነኩሳት ያቀረቡትን ጥያቄ መልሰው ለአክሱም ሊቃውንት አቀረቡ። አክሱሞችም አልተቀበሉዋቸውም። ዝም ብለው ሲቀመጡ አንድ ቀን ከደብረ አባይ አክሱም ጽዮንን ለመሳለም ከመጡ አባቶች ጋር ሲጨዋወቱ የኔታ ሁኔታውን በጥሞና አማከሩዋቸው፤ ከደብረ አባይ የመጡት አባቶችም በነገሩ ስላመኑበት የኔታ ወልደየሱስን ይዘዋቸው ወደ ደብረ ዓባይ ሄዱ።

ከዛ ሞያቸውን በሚገባ ማስተማር ጀመሩ። የሳቸው ደቀ መዛሙርትም የፊተኛውን አቃንተው ከነ ምሥጢሩ ከነንባቡ አሳምረው እንዲያውም ከሳቸው በልጠው ወጡ። ከእነዚህ መካከል የኔታ ገብረ ኪዳንና ሱራፌል ገብረ ማርያም የሚባሉ ይገኙበታል። ሱራፌል የተባሉት ትክክለኛ ስማቸው ገብረ ማርያም ነው። ከአንደበታቸው የሚፈልቀው ጣዕመ ዜማ የመላእክት ዜማ ይመስል ስለ ነበር «ሱራፌል» የሚል ቅጽል ተሰጣቸው። የእኔ መምህር የኔታ የኋላሸት የሳቸው ተማሪ ነበሩ። የኔታ የኋላሸት ዜማ፣ ዝማሬ መዋስዕት፣ አቋቋም፣ ቅኔ ብሉይና ሐዲስም እጠናቅቀው የሚያውቁ ስለ ነበር ቅዳሴውን ከነ ምሥጢሩና ጣዕሙ እያሰመሩ እያረቀቁ ነበር የሚያወጡት። የደብረ አባይ ቅዳሴ ከሌላው የሚለየው የረቀቀ ጣዕመ ዜማ ስልት ስላለው ነው። ሰው ደግሞ ጥሩ ወደ ሆነ ነው የሚሳበው። በዚህ የተነሳ ሰው ሁሉ እየወደደው እየተማረው ሲመጣ እየተስፋፋ ሄደ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – እርስዎ ጋር ለመማር የሚመጡ ደቀ መዛሙርት በቅድሚያ ማሟላት ያለባቸው ምንድነው? ወይንስ የመጣውን ሁሉ ይቀበላሉ?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – እኔ ዘንድ የሚመጡት የአቋቋም፣ የዝማሬ መዋስዕትና የዜማ መምህራን ወይም ደግሞ ሌላ ቦታ ቅዳሴ ተምረው ለማስመስከር የሚመጡ ናቸው። ስለ ሆነም ቀደም ሲል መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ዕውቀት ይዘው ስለሚመጡ ከእኔ ዘንድ ሲማሩ ሞያውን በጣም ነው የሚያረቁት።

**ፈ**ለገ ጥበብ – አሁን ከጠቀሱዋቸው ትምህርቶች ሌላ አንድ ሰው ቅዳሴ ከመማሩ በፊት ቢያውቀው የተሻለ ነው የሚሉት ትምህርት ይኖራል?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – እንደ ሰው ፍላጐት ነው። እንደ እኔ ግን ቅኔ ተምሮ ቅዳሴ ቢማር ምሥጢሩን፣ ጣዕሙን በቀላሉ አጣምሮ ይይዛል ባይ ነኝ። ቅኔ መብራት ይዞ ወደ ጨለማ ቤት እንደ መግባት ነው። ቅኔ ለቅዳሴ ብቻ ሳይሆን ቅኔ ተምሮ ወደ መጽሐፍ ሲገቡም መልካም ነው። መጽሐፍ መማር ብዙ ድካም አለበት። ሰው ግን እውቀቱን ሳይሆን ቶሎ የሚያበላውን ነው የሚመርጠው።

> ቅኔ መብራት ይዞ ወደ ጨለማ ቤት እንደ መግባት ነው። ቅኔ ለቅዳሴ ብቻ ሳይሆን ቅኔ ተምሮ ወደ መጽሐፍ ሲገቡም መልካም ነው። መጽሐፍ መማር ብዙ ድካም አለበት። ሰው ግን እውቀቱን ሳይሆን ቶሎ የሚያበላውን ነው የሚመርጠው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን በተለይ ደግሞ በከተሞች ያለው የቅዳሴ ሁኔታ እንዴት ነው የሚገመግሙት?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – በተለይ በአዲስ አበባ አብነቱን ጠብቆ አይሄድም፣ አዲስ አበባዎች ጉሮሮ ስላላቸው ዝም ብለው እንደ መጣላቸው ነው የሚያዜሙት፣ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሳሉ (በ፲፱፻፸፮–፸፯ ዓ.ም) አዲስ አበባ ተጠርቼ አሥራ አራቱም ቅዳሴ ከነይትበሃሉ በ፳፪ ካሴት ተቀርጫለሁ። ያኔ ታድያ መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ወደ መቅረጫው ክፍል እየመጡ «እንግዲህ ያለ ምልክት እንደ ፈለገው መጮህ የለመደ የአራዳ ዲያቆን ሁሉ ምን ይውጠው ይሆን?» ይሉ ነበር።

**ፈ**ለገ ጥበብ – አሁን ደግሞ መልሼ ወደ ልጅነት ጊዜዎ ልውሰድዎት፣ ልጅ እያሉ ምኞትዎ ምን ለመሆን ነበር?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – ፍላጐቴ ካህን ለመሆን ነበር። ካህን ስልህ ግን ተራ ካህን ሳይሆን ጥሩ የተማረ ካህን ሆኜ እንድቀመጥ ነበር ምኞቴ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በኋላ ታድያ ሃሳብዎን ቀይረው ለመመንኮስ እንዴት ቻሉ?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – ብዙ እያወቅኩኝ፣ መጽሐፍት ማንበብና መረዳት ስጀምር ሃሳቤ ወደ ምናኔ አዘነበለ። በተለይ ቅዱስ ጳውሎስ ሰው እንደ እኔ ራሱን ጠብቆ፣ ከሚስት ርቆ ቢኖር እመርጣለሁ ያለውን ሳገናዝብ የፊተኛው ምኞቴ እየተቀየረ መጣ። በእርግጥ ቅዱስ ጳውሎስ ያገባ ጥሩ አደረገ ያላገባም ጥሩ አደረገ ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ ከሁሉ ግን ያላገባ ይሻላል ይላል። እንግዲህ እኔም ለካ የዚህ ዓለም ነገር ከንቱና ኃላፊ ነው ብዬ ይሻላል የተባለውን መረጥኩ፤ በዛው ላይ መምህራችን የመጽሐፍ ትርጓሜ ሲያስተምሩ እኔ ነበር የማነብላቸው። በአጭሩ ብዙ እያወቅሁ በመጣሁ ቁጥር ልቤ ወደ ምናኔ ይመራኝ ጀመር።

የመነኮስኩት በ፲፰ ዓመቴ በደብረ አባይ ገዳም ነው። ማህበሩ ሁሉ ይወዱኝ ነበር፣ በተፈጥሮዬ ከሰው ጋር አልጨመርም ነበር፤ ጊዜዬን የማሳልፈው በትምህርትና በጸሎት ብቻ ነበር።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በተማሪነትዎ ቁራሽና ጥሬ ልመና በየመንደሩ በሚዞሩበት ጊዜስ ያጋጠምዎት የማይረሳ ገጠመኝ ይኖርዎት ይሆን?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – አባቴ የሞቱት እኔን ብቻ እንደ ወለዱ በልጅነት ጊዜዬ ቢሆንም ሀብት ነበረን። ስለዚህ ደብረ አባይ እያለሁ ከቤት ገንዘብ እህል እየተላከልኝ ነበር የተማርኩት፣ ችግር አልነበረብኝም። ጐንደር ሳለሁ ግን አንድ የመንፈስ ቅዱስ ወንድም ነበረኝ። እሱ ነበር ለምኖ የሚያበላኝ። በመሆኑም አንድም ቀን ሳልለምንና ከውሻ ጋር ሳልጣላ ነው ትምህርቴን የጨረስኩት።

**ፈ**ለገ ጥበብ – እስከ አሁን በርካታ ደቀ መዛሙርት እንዳፈሩ ነግረውኛል፣ እኔን ተክተው ማስተማር ይችላሉ ከሚሉዋቸው ጥቂቶቹን በስም ሊጠቅሱልን ይችላሉ?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – ብዙዎች ናቸው። ከ፲፱፻፸፭ ዓ.ም ጀምሮ ያስተማርኩዋቸው ስማቸውን በመዝገብ አስፍሬ ይገኛዋለሁ፤ እጅግ ብዙ ናቸው። ራሳቸውን ችለው በምስክርነት ሊያስተምሩ የሚችሉት ግን ሃምሳ አምስት ናቸው። ከእነዚህ መካከል ውጭ ሀገር የሄዱም አሉ። ለምሳሌ አባ ብርሃን መስቀል በኢየሩሳሌም፣ አባ ፍቅረ ማርያም በዮርዳኖስ አካባቢ፣ አዲስ አባ ደግሞ አባ ገብረ የሱስ፣ አባ ገብረ ዮሐንስ፣ አባ ፍቅረ ማርያምና ሌሎችም በየሀገረ ስብከቱ አሉ፣ ብቻ ብዙዎች ናቸው።

> አዲስ አበባዎች ጉሮሮ ስላላቸው ዝም ብለው እንደ መጣላቸው ነው የሚያዜሙት፣ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሳሉ (በ፲፱፻፸፮–፸፯ ዓ.ም) አዲስ አበባ ተጠርቼ አሥራ አራቱም ቅዳሴ ከነይትበሃሉ በ፳፪ ካሴት ተቀርጫለሁ። ያኔ ታድያ መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ወደ መቅረጫው ክፍል እየመጡ «እንግዲህ ያለ ምልክት እንደ ፈለገው መጮህ የለመደ የአራዳ ዲያቆን ሁሉ ምን ይውጠው ይሆን?» ብለው ነበር።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ስለ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የሚነግሩን ካለ?

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – ስለሳቸው ምኑ ተነግሮ ይዘለቃል? ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ፍጹም የሃይማኖት የሥራ አባት ነበሩ። ቅዳሴ ተጀምሮ እስኪያበቃ እንባቸው በጉንጫቸው ሳያቋርጥ ስለሚፈስ መሐረባቸው በውኃ የታጠበ ነበር የሚመስለው። አባታችን መንፈሳዊም ኃይለኛም ነበሩ። አንድ ሰው በርኅራኄ ከቀረባቸው የበለጠ ርኅሩኅ ሆነው ይቀበሉታል፣ በኃይል ለሚመጣባቸው ግን አይበገሩም። ብቻ እንደሳቸው የመሰለ ሰው አይገኝም።

**ፈ**ለገ ጥበብ – እግዚአብሔር ይስጥልኝ አባታችን

**መ**/ሰላም ገ/እግዚአብሔር – ተባረክ ልጄ። ✣

## ንስሐ ግቡ… በሕይወት ኑሩ

«…ንስሐ ግቡ፤ ኃጢአትም እንቅፋት እንዳይሆንባችሁ፣ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ። የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ። አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ…ስለምን ትሞታላችሁ? የምዋቹን ሞት አልፈቅድምና፣ ይላል ጌታ እግዚአብሔር ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ።»

(ትን.ሕዝ.፲፰፥፴–፴፪)

## እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ

«ዳሩ ግን የነገር ሁሉ መጨረሻ ቀርቦአል። እንግዲህ እንደ ባለ አእምሮ አስቡ፣ ትጸልዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ፤ ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና ከሁሉ በፊት እርስ በርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ።»

(፩ጴጥ.፬፥፯–፰)

## ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው

«ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ። እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መል እክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን? ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።»

(ያዕ.፪፥፳፬–፳፮)



www.ethiopianorthodox.org

# ሞትና ትንሣኤ

መ/ሰላም ዳኛቸው ካሳሁን



በዚች ምድር ላይ የምንቆይበት ጊዜ የተወሰነ ነው። በጣም አጭርም ነው። መጻሕፍትም፣ ሊቃውንትም እንደ ጥላ፣ እንደ ጢሳ ያለ ነው ብለውታል፤ በሌላም ገጽ የዚህን ዓለም የቆይታ ኑሮ የእንግድነት ጊዜ እንደ ሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል። «...እኔ ለጥቂት ጊዜ ያንተ እንግዳ ነኝ እንደ ቀድሞ አባቶቼም በስደተኛነት የምኖር ነኝ» (መዝ.፹፱፥፲፪)። ከአዳም እስከ ኖኅ በነበረው ዘመን ሰዎች ወደ አንድ ሺህ ዓመት የተጠጋ ዕድሜ እንደ ነበራቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦአል። (ዘፍ.፭፥፩–፴፪) ከዚያ በመለስ እስከ አምስት መቶ ዓመት ዕድሜ የተሰፈረላቸው አበው ለዚህ አጭር ጊዜ ቤት አንሠራም ብለው ኑሮአቸውን በዳስ፣ በሰቀላ፣ በድንኳን አሳልፈዋል። ምሥጢሩ አንድና አንድ ነው፣ ሺህ ዓመትም ተኖረ መቶ ዓመት መጨረሻው ሞት ስለ ሆነ ነው።

ሞት የተፈጠረው የመጀመሪያዎቹ ሰዎች በገነት ሳሉ የተሰጠውን ፈተና ተቋቁመው ማለፍ ተስኖአቸው በወደቁ ጊዜ ነው። በተሰጡት አለመርካት፣ ያልተሰጡትን መሻት፣ ለአደራ አለመብቃት፣ ምን ጊዜም አደጋ አለው፤ በበለስዋ ፍሬ አካባቢ በተፈጸመው ስሕተት ኃጢአት በሰው ሕይወት ሠርፆ ሞተ ሥጋ፣ ሞተ ነፍስ በወሪደ መቃብር ወሪደ ገሃነም ተፈረደ። ኃጢአት ማለት የተሰጡትን፣ የተቀበሉትን፣ እጅ የገባውን ሀብት፣ ክብር፣ ፀጋ ማጣት ማለት ነው።

በመጀመሪያዎቹ ሰዎች በደል የተፈረደው ፍርድ በሰው ዘር ሁሉ ተላለፈ፣ ከአዳም እስከ ሙሴ የነበሩ ሰዎች በሞት ጥላ ሥር ኖሩ፣ ከአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በኋላ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ የሰውን ሥጋ ለብሶ በምድር ላይ የተገለጠው በሰው ላይ የፈሰሰውን የተፈረደውን የፍርድ መርገም አጥፍቶ፣ ኃጢአትን ከሥሩ ነቅሎ፣ አስወግዶ የሞትን ሰንሰለት ፈትቶ፣ ከእግዚአብሔር የተለዩትን ከተድላ ገነት የወጡትን፣ ከፀጋ ልጅነት የራቁትን፣ ወደ ቀድሞ ነፃነታቸውና ክብራቸው ለመመለስ ነው። ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ ኮረብታ በዕለተ ዓርብ በተሰቀለ ጊዜ ኃጢአት ከሥሩ ተነቅሎ ወድቋል፣ ሞት በክርስቶስ ሞት ተሽሮአል።

በዓለማችን ስንኳን ለክፉ ሰዎች ለደጋግ ሰዎችም የሚሞት የለም። እጅግ የሚወደዱ ቢኖሩ ፍቅራቸው እስከ መቃብር ነው የሚጓዘው። የሞትን ክልል አልፎ ከመቃብር አድማስ ማዶ የሚሻገር የለም። የሁሉም ሸኝት እስከ መቃብር ነው። የአንደበት ሸንገላና ውዳሴ ከንቱ በተመላች ምድራችን «አንተ ቁምልኝ እባክህ፣ በሞቴ ልቅደምህ» እየተባለ የተዘመረላቸው፣ የውዳሴ ቅኔ የቀረበላቸው ሰዎች ነበሩ፤ የሞት መጥሪያ እየደረሳቸው በተጓዙ ጊዜ ግን የቀደመላቸው የተከተላቸውም የለም፣ ለብቻቸው እንደ መጡ ብቻቸውን አልፈዋል።

ክርስቶስ ሰውን የወደደበት ፍቅሩ ከሰው የሚለየው በዚህ ነው፣ የሚጠሉትን መውደድ ለበደሉት ራስን ካሣ አድርጎ መስጠት!

«ለክፉ ሰዎች በጭንቅስ እንኳ ይሞት ዘንድ የሚወድ አይገኝም፣ ለደጋጎች ሰዎች ይሞት ዘንድ የሚወድ ይገኝ እንደ ሆነ እንጃ! ክርስቶስ እኛ ኃጢአተኞች ስንሆን ስለ እኛ ኃጢአት ሊሞት በጊዜው ጊዜ መጣ» ብሎ አል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ (ሮሜ. ፭፥፮–፯)።

በአንድ አዳም በደል ብዙዎች ሞት እንደ ተፈረደባቸው በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ሆነ፤

«የመጀመሪያው ሰው አዳም ከምድር የተገኘ መሬታዊ ነው፣ ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ ግን ከሰማይ የመጣ ሰማያዊ ነው፣ አዳም መሬታዊ እንደ ሆነ እኛም መሬታውያን ነን፣ ክርስቶስ ሰማያዊ እንደ ሆነ እኛም ሰማያውያን ነን፤ የዚያን የመሬታዊውን መልክ እንደለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን።» (፩ቆሮ. ፲፭፥፵፯–፵፱) የትንሣኤ ምሥጢር በዚህ ይገለፃል።

በጥንተ ፍጥረት «አትንኩ ጠብቁ» የተባሉትን አክብሮ ጠብቆ በጥቂት ዘመን ትዕግሥት ፈተናውን ማለፍ ቢቻል ኖሮ ውጤቱ በየሺህ ዓመቱ እየታደሱ ከሕይወት ወደ ሕይወት መሸጋገር ነበር። የሞት መልክ ሳይታይ የልቅሶና የዋይታ ድምፅ ሳይሰማ ወደ ዘለዓለም ተድላ መግባት በተቻለ ነበር። ዕንቅፋት ያልነበረው የሕይወት መንገድ በኃጢአት ስለ ተደናቀፈ ወደ ዘለዓለም ሕይወት መድረስ የሚቻለው በሞት በኩል ታልፎ በሚገኘው ትንሣኤ ነው። በአዳማዊ ባሕርይ የምንንቀሳቀስ ሰዎች ሁላችን እንሞታለን፣ ወደ ተገኘንበት መሬት እንመለሳለን። ነገር ግን ሥጋዊ ሞት የመጨረሻ ሞት አይደለም፣ ከሕይወት ወደ ሕይወት መሸጋገሪያ ድልድይ ነው። የነፍስ ማኅደር የሆነው ሥጋችን እንደ ቀን (እንደ ሥራ) ልብስ ነው። ሥራ ሠርተን በምናልፍበት በዚህ ዓለም እሱን ለብሰን እንንቀሳቀሳለን፣ ዕድሜ የምንለው የቆይታ ጊዜ እንደ ፀሐይ ሲጠልቅ ወደ ነፍሳችን ዕረፍት ስንመለስ አውልቀን በመቃብር እናኖረዋለን። እስከ መጨረሻው የሙታን ትንሣኤ በዚያው ይቆያል። ነፍስ ግን ወደ ፈጣሪዋ ትመለሳለች።

በዚህ መልኩ ሁላችን የሞት እንቅልፍ እናንቀላፋለን፣ ነገር ግን የተኛ ሰው ፈጥኖ ከእንቅልፉ እንደሚነቃ በኋለኛው ዐዋጅ ፈጥነን እንነሳለን፣ ፈጥነን እንለወጣለን ይህም ታላቅ የሙታን ትንሣኤ ምሥጢር ነው።

«ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ፣ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና» (፩ቆሮ.፲፭፥፶፫)።

ጌታችን በታቦር ተራራ ላይ ብርሃነ መለኮቱን በገለጠበት ጊዜ ሙሴ በሞት፣ ኤልያስ በዕርገት ከዚህ ዓለም ከተለዩ ብዙ ዘመን በኋላ ሙሴ ከሞት ተነስቶ ከመቃብር ወጥቶ፣ ኤልያስ ከብሔረ ሕያዋን መጥቶ በሕይወተ ሥጋ ከነበሩ ሐዋርያት ጋር ትንሣኤና ሕይወት በሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት መገናኘታቸው የሙታን ትንሣኤ ማረጋገጫ ሌላው ትምህርት ነበር። እነሆ «በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል የታመነ ይሆን ዘንድ ከብዙ ዘመናት ጀምሮ በመሬት ውስጥ ወድቀው ሥጋቸው የፈረሰ፣ አጽማቸው የተከሰከሰ፣ እንደ ሣር እንደ ገለባ የተበተኑት ሁሉ ይነሳሉ። በመጨረሻው የሙታን ትንሣኤ በሚደረግበት ጊዜ:-

በመጀመሪያ ዐዋጅ የተበተነ ሥጋ ሁሉ ይሰበሰባል፣

በሁለተኛ ዐዋጅ አጥንት ከአጥንቱ ይሳካል ይመሳኳል፣

በሦስተኛ ዐዋጅ ሙታን ከቂጥራቸው ሳይጐድሉ አካል ሳይጐድላቸው

በአዲስ አካለ ይነሳሉ። (ቅዱ. ያዕ.ዘሥ)

ይህም አስቀድሞ በነቢይ ተነግሮአል:- «የሰው ልጅ ሆይ በእነዚህ አጽሞች ላይ ትንቢት ተናገር፣ የደረቃችሁ አጥንቶች ሆይ እግዚአብሔር የሚለውን ቃል ስሙ በላቸው። ...እነሆ እኔ መቃብራችሁን እከፍታለሁ ከመቃብራችሁ አወጣችኋለሁ፤ ነፍስ አዋሕጄ አስነሳችኋለሁ፣ መጀመሪያ ኸርማት እታታባችኋለሁ፣ ሁለተኛ ሥጋ እመርግባችኋለሁ፣ ሦስተኛ ቁርበት አለብሳችኋለሁ፣ አራተኛ ነፍስ አዋሕዳችኋለሁ፣ ወዲያው ትነሳላችሁ» ተብሎ። (ሕዝ.፴፯፥፩–፲፪)።

በነቢያት የተነገረው፣ በራእይ የተገለጠው፣ በተአምራት የታየው ሁሉ በክርስቶስ ትንሣኤ ታትሞ ተረጋግጦአል። ክርስቶስ በሞት ላንቀላፉት ሁሉ በኩር ሆኖ ተነስቶአል።

በመዋዕለ ትምህርቱ ምልክት እን ፕለን ብለው ለጠየቁት ማስረጃ አድርጎ የሰጣቸው የዮናስን ታሪክ ነበር።

«ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ኖረ እንዲሁ ወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ያድራል» የሚል ነበር (ማቴ.፲፪፥፴፰–፵)።

በክርስቶስ የስቅለት ሞት የፈረዱ ጸሐፍት ፈሪሳውያን መቃብሩ በባለ ሥልጣኖች ፊርማና ማኅተም እንዲታሸግ ንቃት፣ ትጋትና ኃይል ባላቸው ወታደሮች እንዲጠበቅ አድርገው ነበር። ነገር ግን ክርስቶስን ከመነሳት ያገደው ምንም ኃይልና ሥልጣን አልነበረም።

- በመቃብሩ ላይ ተገጥሞ የነበረው ድንጋይ ተገለባብጦ ተገኝቶአል፣
- በመቃብሩ ራስጌና ግርጌ የነበሩ ቅዱሳን መላእክት «ሕያውን ከሙታን ጋር ለምን ትፈልጉታላችሁ፣ ከዚህ የለም ተነስቶአል» ብለው መስክረዋል።
- በዚያው አካባቢ ሌሊቱን ሲመላለሱ ያደሩ ቅዱሳት አንስት (ሴቶች) በአካል አይተውታል።
- ራሱ ጌታ «እነሳለሁ» እያለ ከመሞቱ በፊት የተናገረው ተፈጽሞ ለደቀ መዛሙርቱ ተገልጦ ታይቶአል፣ ዓርባ ቀንም አብሯቸው ሰንብቶአል።
- እነ ቅዱስ ጳውሎስም ከትንሣኤው በኋላ በግልጽ ማየታቸውን አረጋግጠዋል።

የሚከተሉትን ጥቅሶች መመልከት ይቻላል።

ማቴ.፲፮፥፲፮፤ ሉቃ.፳፬፥፩–፲፪፤ ዮሐ.፳፩፥፲፬፤ ማቴ.፳፯፥፶–፶፫፤ ፲፮፥፱፤ የሐዋ.፪፥፴፩፤ ፱–፴፫፤ ፩ቆሮ.፲፭፥፫–፰።

አዎ ክርስቶስን ሞትና መቃብር ይዘው ሊያስቀሩት ስላልቻሉ ሦስት መዐልትና ሦስት ሌሊት በመቃብር አድሮ ሞትን፣ ኃጢአትን ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ተነስቶአል፤ ሞታችን በሞቱ ድል ተነስቶአል፣ እሱን በኩር አድርገን ሁላችን እንነሳለን፤ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኋላ ሞት በሰው ልጆች ላይ ኃይልና ሥልጣን የለውም፣ መቃብርም ይዞ ማስቀረት አይችልም፣ በጻድቃንና በኃጥአን የፍርድ አደባባይ የክብርና ወይም የሐሣር ትንሣኤ ለመነሳት ምርጫውና ውሳኔው የእያንዳንዳችን ስለሆነ የክብር ትንሣኤ ለመነሳትና ክርስቶስ የሚያወርሰንን የልጅነት ክብር ለማግኘት ምርጫችንን ከወዲሁ ማስተካከል ይኖርብናል። ✣



www.ethiopianorthodox.org

# እስትጉቡእ

(እስትጉቡእ - ጥርቅም፣ የተቀመመ፣ የተሰባሰበ ማለት ነው)

## አስደናቂው የዘመናችን ፍቅር

በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕ.፲፩ ቁ.፮–፰ ላይ እንዲህ ይነበባል፤ «ተኩላ ከበግ ጠቦት ጋር ይቀመጣል፤ ነብርም ከፍየል ጠቦት ጋር ይተኛል፤ ጥጃና የአንበሳ ደቦል አብረው ይሰማራሉ፤ ግልገሎቻቸውም በአንድነት ያርፋሉ፤ አንበሳም እንደ በሬ ገለባ ይበላል። የሚጠባውም ሕፃን በእባብ ጉድጓድ ላይ ይጫወታል፤ ጡት የጣለውም ሕፃን በእፍኝት ቤት ላይ እጁን ይጭናል።»

እ.ኤ.አ በ፪ ሽህ ፪ ዓ.ም በኬንያ ሳምቡሩ ፓርክ ተከስቶ የነበረው አስገራሚ ሁኔታ ብዙዎችን ከላይ የተጠቀሰው ትንቢተ ኢሳ ይያስ በአሁኑ ጊዜ መፈጸም ጀመረ ወይ? አሰኝቶአቸው ነበር። ነገሩ እንዲህ ነው። በሳምቡሩ ፓርክ አንዲት ሳላ (አጋዘን መሳይ እንስሳ) እናት ግልገልዋን ከወለደች ከጥቂት ቀናት በኋላ ትሞታለች (በሌላ አውሬ ትበላለች)። በመሆኑም ግልገልዋ ያለ እናትና ያለ አሳዳጊ ቀረች።

በዚህ ጊዜ ነበር አንዲት እናት አንበሳ የሳላ ግልገልዋ ከተኛችበት በመምጣት የማይታመን ተግባር ማከናወን የጀመረችው። ግልገልዋን በመላስና በፍቅር በመቅረብ ትንከባከባት ጀመር። ሌላው ቀርቶ ለልጆችዋ ብቻ ያለችውን ጡትዋን ሰጠቻት። ለመጀመሪያ ጊዜ የሳላ ግልገል የአንበሳን ጡት ስትጠባ ያዩ የፓርኩ ሠራተኞችና ሀገር ጎብኝዎች ያዩትን ማመን አቅቶአቸው ነበር። ወሬው መገናኛ ብዙሃን ዘንድ እንደ ደረሰ ይህንን ትንግርት ለማየት ከአውሮጳና ከተለያዩ ዓለማት ሀገር ጉብኝዎችና ጋዜጠኞች ወደ ኬንያ ይጎርፉ ጀመር።

የተባለው እውነት መሆኑን በዓይናቸው አይተው አመኑ። ድርጊቱን በፎቶና በቪዲዮ ካሜራ በመቅረጽም ትዕይንቱን በአካል መጥቶ ለማየት ላልቻለው የዓለም ሕዝብ አቋደሱ። በርካታ ሀገር ጉብኝዎች አንበሳዋና ሳላዋ ጉን ለጉን ፊትና ኋላ እየሆኑ ሲሄዱ፣ ተቃቅፈው ጥላ ሥር ሲተኙ፣ ወንዝ ወርደው ውሃ ሲጠጡ ለ፲፭ ቀናት ያህል ተከታትለው አይተዋቸዋል። ከ፲፭ ቀናት በኋላ ግን አንድ ያልታሰበ ክስተት ተፈጸመ። እንደ ተለመደው እናት አንበሳ «በማደጎነት» የምታሳድጋትን ሳላ እስከ ትላ ወንዝ ወረደች። እንደ ደረሰችም ሀገር እማን ነው ብላ ውኃ ለመጠጣት ጉንበስ አለች። በዚህ ጊዜ ነበር ሌላ አንበሳ ድንገት ከጫካ ውስጥ ዘሎ በመውጣት ግልገል ሳላዋን በመዳፉ ጨፍልቆ ገደላት።

አንበሳው ለምን ይህንን እንዳደረገ ግልጽ ባይሆንም (ከገደላት በኋላ አልበላትምና) ብዙ ኬንያውያንና የውጭ ሀገር ጎብኝዎች ግን ጥፋቱ የፓርኩ ሠራተኞች እንደ ሆነ በንዴት መናገራቸው አልቀረም። እነደ እነዚህ ሰዎች አባባል ይህ ሁሉ ከመሆኑ በፊት አንበሳዋንና ግልገል ሳላዋን ለብቻቸው ለይቶ በማስቀመጥ መጨረሻቸውን ማየት ይቻል ነበር።

የአንበሳዋንና የሳላዋን የወዳጅነት ምሥጢር በዚህ መልኩ ቢቋጭም የፓርኩ የሥነ ተፈጥሮ ባሞያ የሆኑት ሚስተር ሺንለንት ካፔን «እንግዳው አንበሳ ሳላዋን የገደላት ሌላ ተቀናቃኝ ጠላት መስሎት መሆን አለበት። ይህ ባይሆን ኖሮ ማንም አንበሳ እንደሚያደርገው ከገደላት በኋላ ግልገልዋን ይበላት ነበር።» ሲል አስተያየታቸውን ገልጸዋል።

ምንጭ (All African News Agency Bulletin No. 01/02)

## እንዲህም ተደርጓል?

ከግራኝ ወረራ በኋላ ክርስትና በምሥራቅ፣ በመካከለኛና በደቡብ ኢትዮጵያ በጣም ተዳክሞ ነበር። በተለይ በደቡብና በምዕራብ ኢትዮጵያ የግራኝን እስከፊ ጭካኔና ግድያ ተቋቁመው የቀሩ ጥቂት ክርስቲያኖች ለትምህርት ወደ ጎንደር፣ ወደ ጎጃምና እንኮበር ለመሄድ አልቻሉም ነበር። ምክንያቱም ዙርያቸው በእስላሞችና በአረማውያን በመከበባቸው የተነሳ ነው።

ይሁንና የጉራጌ ክርስቲያኖች ዙሪያቸው በሙሉ በሃይማኖት ጠላቶቻቸው ቢከበቡም በነበራቸው ጽኑና ጠንካራ የክርስትና እምነት የተነሳ ለበርካታ ዓመታት ስመ ክርስትናቸውን፤ ሀብተ ወልድ ልጅነታቸውን ጠብቀው ቆይተዋል። ምሁሮችና አክሊሎች በዚህ በኩል ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው። ጉራጌዎች እምነታቸውን በተጋድሎና በጽናት ጠብቀው ለማቆየት ከተጠቀሙባቸው ዘዴዎች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ነበሩ።

ከግራኝ ወረራ በፊት የነበሩት ካህናት ብዙዎቹ በወረራው ምክንያት በመሰዋታቸውና ቀሪዎችም በዕድሜ ምክንያት እያረጁ ሲሄዱ በእነርሱ ሥር የሚተካ አገልጋይ ያስፈልግ ነበር። ለዚህ ችግር ጉራጌዎች የፈጠሩት መላ ከቤተ ክህነት (ካህን) የሚወለደው በኩር ሁሉ የቤተ ክህነት ትምህርት እንዲማርና በድንግልና እንዲኖር የሚል ነበር። ከዛም ቄስ እገሌ እየተባለ ክህነታዊ ነገር ርቆ በየዋሻው የተደበቁትን ታቦታትን ያጥናል፤ ሕፃናትን ያጠምቃል፤ ይቀድሳል፤ ያቆርባል፤

ቄሱ ቀድሶ ካቆረበ በኋላ ለቁርባኑ ክብር ሲባል ወደ ቤቱ የሚመለሰው በፈረስ ተቀምጦ፤ ፈረስ ከሌለ በሰው ታዝሎ ነበር። ቅዳሴው በአብዛኛው የሚከናወነው እሑድ እሑድ ሲሆን ሕዝቡ በሙሉ ቅዳሜ ማታ ተሰብስቦ ቤተ ክርስቲያን ሲጸልይ ካደረ በኋላ እሑድ ጠዋት አስቀድሶ ነበር የሚመጣው።

ሌላው የጉራጌዎች ጠንካራ ክርስቲያንነት የሚያረጋግጥ አስደናቂ አሠራርም ነበር፤ ይኸውም ለቤተ ክርስቲያን የሚሆነው መገበሪያ ስንዴ የሚዘራው፣ የሚታረመው፣ የሚታጨደውና የሚወቃው በባለ ሕግ (ድንግል) ብቻ መሆኑ ነው። ሌላው ቀርቶ በሚወቃበት ጊዜ ከብት እንዳይሸናበት ተብሎ እህሉ የሚወቃው በበትር ነበር። ለዚህ ነው ከጥንት ጀምሮ መስዋዕት በጉራጌ፣ ቅዳሴ በትግሬ፣ በጎንደር ማህሌት፣ በሸዋ ሰዓታት፣ በጎጃም ጸሎት የሚባለው።

በዛ ክፉ ዘመን በጉራጌ የቄስ ልጅ ቄስ የሚሆነው እንደዚሁ አልነበረም፤ የራሱ የሆነ ሥነ ሥርዓት ነበረው። ቄሱ በዕድሜ እየገፋ ሲመጣ ከመሞቱ አስቀድሞ እርጥብ የፍየል ስልቻ ይነፋና አስሮ ያስቀምጣል። አባት ካህን ሲሞት ሕዝቡ ተሰባስቦ ወራሹን (የበኩር ልጁን) አቅርበው «እግዚአብሔር የቄስ እገሌን ክርስትናና በረከት ያሳድርብህ» በማለት ስልቻውን ፈትተው ትንፋሹን በራሱ ላይ ያፈሱበታል። ከዛ በኋላ ቄስ ይሆናል። ደስታ ተክለ ወልድ ይህንን አስመልክተው በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም በጻፉት ጽሑፍ «የማያስተምር ጳጳስ ካለበት ስፍራ ይልቅ የጉራጌ ቤተ ክህነት እጅግ የተደነቀ ነው» ብለዋል።

እነዚህን የመሰሉ ጠንካራ ክርስቲያኖች በነበሩበት ምድር፣ ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ እናቶች ጭምር የቆጮ መከተፊያቸውን በመያዝ ከነሐስን እንጃበ ጦር ጋር እየተፋለሙ መስዋዕትነት በከፈሉበት ምድር፣ የዘመኑ ፀረ ተዋሕዶ አረማሞ መናፍቃን እንዳያረክሱት የጉራጌ ወጣቶች የአባቶቻቸውን ኮቴ በመከተል የተዋሕዶ እምነታቸውን የመጠበቅ የሃይማኖት ግዴታና የአበው አፅም አደራ አለባቸው።

ምንጭ ገበታ ዋርያ የንባብ መማሪያ – ፲፱፻፷፰ ዓ.ም

ፈለገ ጥበብ



# ከወጣቱ ለወጣቱ

## የደብረ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰንበት ት/ቤት አመሠራረትና እድገት

ከዮሴፍ ከፈለኝ

በ፲፱፻፶ዎቹ መጀመሪያና ከዚያም አስቀድሞ ገዳም ሠፈር በመባል የሚታወቀው አካባቢ ይኖሩ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ወጣቶች ማህበር መሥርተው በቤተ ክርስቲያን ይሰባሰቡ እንደ ነበር አባቶች ቢናገሩም መረጃዎች እንደሚያሳዩት የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር ለመጀመርያ ጊዜ የተቋቋመው በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም በመምህር እያሱ ተፈሪ (በአሁኑ አቡነ ገብርኤል) እና በሌሎች አባቶች አማካይነት ነበር። ደርግ ሥልጣን በያዘበት በ፷ዎቹ አጋማሽ አካባቢ ኢ.ኢ.ወማ ያቋቋመበት ወቅት ስለ ነበር ሁለት የወጣቶች ማኅበራት ሊኖሩ አይገባም በማለት ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የማህበሩ ስም በፈረንጆቹ አሰያየም ሰንደይስኩል (Sunday School) (የሰንበት ት/ቤት) የሚል ስያሜ ማግኘቱን ታሪክ ያስረዳል። ይህ ሰንበት ት/ቤት ከተቋቋመ እስከ አሁን በርካታ ተግባራትን አከናውኗል አሁንም እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በዘጠኝ ሥራ አመራርና በስምንት የአገልግሎት ክፍሎች ተዋቅሮ መንፈሳዊ ጉዞውን ገፍቶበታል። ዘጠኙ አመራሮች የንዑሳኖቹ ተጠሪ በመሆን ሥራውን የሚሠሩ ሲሆን ይህ አይነቱ አካሄድ የተለመደና የረጅም ጊዜ የሰንበት ት/ቤቱ አካሄድ መሆኑ ይነገራል።

የሰንበት ት/ቤቱ ዓይነ ተዳርጐ የሚወሰደው ትምህርት ክፍሉ ሲሆን ከ፲፱፻፹፫–፲፱፻፺፬ ባሉት ፲፩ ዓመታት ከቀዳማይ (፩–፬) ራብዓይ ድረስ ባለው የትምህርት ጉዞ ወደ ፲፪ ሽህ ፩፻፹፪ ተማሪዎችን መዝግቦ ፰ ሽህ ፱፻፸ ተማሪዎችን አስመርቋል። የመምህራኑ ብቃትም አስተማማኝ ነው። ከደብሩ ወጣቶች በተጨማሪ ከቅዱስ ራጉኤል፣ ከአቃቂ ጃቲ ኪዳነ ምሕረት ከእንጦጦ ኪዳነ ምሕረት፣ ከቅዱስ እስጢፋኖስ ከቦሌ ሚካኤልና መድኃኔዓለም፣ ከቅዱስ ዑራኤልና



የሰንበት ት/ቤቱ ሊቀ/መ ወጣት ሽመልስ

ቅዱስ ዮሴፍ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ወጣቶች እየተላኩ እንዲሰለጥኑ መደረጉ ለዚህ አንጋፋ ሰንበት ት/ቤት ብቃት አንዱ ምስክር ነው። በሰንበት ት/ቤቱ ኃላፊነት የሚመሩ የተለያዩ ጉባኤያት ሲኖሩ ከእነዚህ መካከል የሮያል ኮሌጅ ተማሪዎች፣ የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ካምፓስ፣ አቃቂ አድቬንቲስት፣ የአጥቢያው የመንግሥት ሠራተኞች፣ የአንበሳ የከተማ አውቶቢስ ሠራተኞች፣ የዩኒቲ ኮሌጅ መምህራንና ሠራተኞች፣ የአርቲስቶች ጉባኤ ይገኙበታል።

በተጨማሪ የትምህርት አሰጣጥ ንድፉን የቅዱስ ዑራኤል፣ የቅዱስ ገብርኤል፣ የልደታና በዓታ ለማርያም ሰንበት ት/ቤቶች ወስደው ይጠቀሙበታል። በሰንበት ት/ቤቱ ብቃት ባላቸው መምህራን የሚሰጠውን የግዕዝ ቋንቋ ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች በየትኛውም ኮሌጅ ሲገቡ ውጤታቸው ያማረ ነው። ከዚህም በተለየ ሁኔታ በበዓላት (ቅዳሜና እሑድን ጨምሮ) ከጠዋቱ ፫–፯ ሰዓት ለአንባቢያን ክፍት የሆነ የተጠናከረ ቤተ መጻሕፍት አለው። ይህ ቤተ መጻሕፍት ሥራውን በ፲፱፻፹፫ ሲጀምር ከ፶ በላይ መጻሕፍት አልነበረውም። በኋላ ግን የተለያዩ ሰዎችን ርዳታ በማጠያየቅ እንቅስቃሴውን ማጉልበት ጀመረ።

በወቅቱ የቀጨኔ እንጦጦ አጥቢያ አስተዳዳሪ የነበሩት የአሁኑ የደ/ኃ/ቅ/ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪና የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ ክቡር መልአከ ኃይል [illegible]ት እውነቴ ኮከሃ ሃይማኖት [illegible]ንድ ቃለ አዋዲ፤ እንደዚሁም በወቅቱ የደብሩ ዓለቃ የነበሩ መልአከ ገነት ዘለዓለም እሴይ ፤ መጻሕፍት ለሰ/ት/ቤቱ ማበርከታቸው ታውቋል። የተጠረዙ (ሐመር፣ መለከት፣ ትንሣኤና ማዕዶት) መጽሔቶችን ጨምሮ በአሁኑ ሰዓት ቤተ መጻሕፍቱ ከ፫፻፹፯ በላይ መጻሕፍት አሉት። በቀን አነሰ ቢባል ከ፳–፴ ተጠቃሚዎች ይገለገሉበታል። ረቡዕና ዓርብን ጨምሮ በጾም ወቅት ከ፮:፴–፰:፴ ባለው ጊዜና በቅዳሴ ሰዓት ዝግ ይሆናል። መጻሕፍት ቤቱ በዓመት ፳፲

ፈለገ ጥበብ

ሽህ ተጠቃሚዎች እንዳሉት ታውቋል። ሰንበት ት/ቤቱ በአሁኑ ጊዜ በንዑስ ክፍሉ አማካኝነት በቪዲዮ ድምፅ ቀረጻ የልደትና ጋብቻ የመሳሰሉት አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅቱን ማጠናቀቁ የሰንበት ት/ቤቱ ሊቀ መንበር ወጣት ሽመልስ ገልጾልናል። በሌላ በኩልም ሰንበት ት/ቤቱ በውጭ አገር ካሉ አባላቶቹ ጋር እጅግ ጠንካራ የሆነ ግንኙነት አለው። ከዚህ በመነጨ መልኩ ውጪ ያሉት አባላት ኮምፒውተር፣ የጽሕፈት መሣሪያ፣ ፕሪንተር፣ ቴሌቪዥን፣ ቪዲዮ ከነዴኩ በራሳቸው ወጪ ገዝተው ለሰ/ት/ቤቱ ልከዋል። ሰንበት ት/ቤቱም በተላኩት መሣሪያዎች በመጠቀም የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅቱን አጠናቋል።

ይህ ዓይነት ግንኙነት አመራሩን ሊያስመሰግነው ይገባል። ሰንበት ት/ቤቱ በተጨማሪም የኤድስ በሽታን ወረርሽኝ ለመግታትበሚደረገው ጥረት በዓመት ሁለቴ ወይም አንዴ ታላቅ መንፈሳዊ ጉባኤ ይዘጋጃል። ከመንግሥት መሣሪያ ቤቶችና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅርበት ይሠራል፤ ከተስፋ ጉህ፣ ከበሽተኞች፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በአጋርነት ይንቀሳቀሳል። ሥራ አመራሮቹ እንደ ገለጹልን ከሌሎች አቻ ሰንበት ት/ቤቶች ጋርም ጠንካራ ግንኙነት አለው። በዓመታዊ በዓላት ላይ እንግዶችን ይጋብዛሉ አባላቱም በተራቸው ይጋበዛሉ፤ ከገጠር አብያተ ክርስቲያናት ጋር በራሪ ወረቀት በመላላክ ግንኙነት ያደርጋሉ። የሰበካ ጉባኤው ከሰንበት ት/ቤት አመራር ጋር ተባብሮ መሥራቱ አባላቱ ሥራቸውን በተቀላጠፈ መንገድ እንዲያከናውኑ ረድቶአቸዋል።

የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰንበት ት/ቤት ሊቀ መንበር ወጣት ሽመልስ በመቀጠልም «ጠይቀን የተከለከልነው፣ አዘውን እንቢ ያልንበት ጊዜ የለም። በመንፈሳዊ ሕይወት ዙሪያ በሥነ–ምግባር፣ በእምነት፣ በፍቅር፣ በመንፈሳዊና በዓለማዊ ዕውቀት ዙሪያ ከአባላቶቻችን ጋር የውይይት መድረክ መኖሩ፤ ጠንካራ መንፈሳዊ ስብዕና ያላቸው አባላትን እንድናፈራ ረድቶናል። በአሁኑ ጊዜ ፳፱ አባላትን በአገልግሎት እንዲሳተፉ ከ፴–፶ አባላት ደግሞ በተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች በመሳተፍ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት በማበርከት ላይ ናቸው» ብሏል።

በመቀጠል የካቲት ፱/፲፱፻፺፫ የተመረጠው አዲሱ ሥራ አመራር «ጠንካራ ጐናችንን አጐልብተን ደካማውን አስወግደን ለመጓዝ ጥረት እንደምናደርግ ባወጣነው ዕቅድ አኳያ ተግባብተናል።

ከዚህ አኳያ በአጭር ጊዜ:-

- ዕቅድን በተጠና መልኩ መዘርጋት
- ፈጣን ርዳታ ለአባላት ማድረግ
- ከኮሌጆች (ከድርጅቶች) ጋር ግንኙነት መፍጠር
- አባላት በአገልግሎት እንዲሳተፉ መገፋፋት
- ውጭ አገር ካሉ አባላት ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከር
- የራቁ አባላትን መመለስ የሚሉ ዕቅዶችን ስንይዝ

በረጅም ጊዜ ዕቅድ ደግሞ

- ልማት ክፍሉን ራሱን ማስቻል
- የተማሩና ጠንካራ አባላት በማሰባሰብ ማኅበሩን ማጠናከር
- ዌብሳይት መጠቀም
- የተልዕኮ ትምህርት መጀመር
- የቤተ ክርስቲያኑ ሒሳብ ክፍል ኮምፒውተራይዝድ በሆነ መልኩ ማጠናከር የሚሉትን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ላይ እንገኛለን» በማለት ገልጿል።

የገነተ–ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት በአሁኑ ጊዜ በተከታታይ እየሰጠ ባለው ትምህርት ከ፰፻ በላይ አባላትን በሥሩ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

በመጨረሻም ሥራ አመራሩንና ሰንበት ት/ቤቱን በመወከል ሊቀ መንበሩ ወጣት ሽመልስ ባስተላለፈው መልዕክት «ከሁሉ አስቀድሞ ኅብረት ይኑራችሁ ነው የምንለው፤ ሰንበት ት/ቤቱ ሌላውን አናሣ አድርጐ መመልከት የለበትም። ሥራ–አመራሩ ከአባሉ፣ አባሉ ከሥራ–አመራሩ ጋር በኅብረት ሊንቀሳቀሱ ይገባል። በሰንበት ት/ቤት መሰባሰብ በዘፈቀደ የሆነ ሳይሆን ቃለ እግዚአብሔር ለማስተማር፣ ወጣቱን ለአገር፣ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ ለማድረግ ስለ ሆነ የሚሰባሰቡበትን ዓላማ ማወቅ አለባቸው። በተጨማሪ ከስብከተ ወንጌሉ ጋር በመወያየት በሁርክ ጉባኤ ከፍተኛ ተሳትፎ ሊያደርግ ይገባል። ለቤተ ክርስቲያን እድገትም ሊኳን እንደሚገባ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን» ብሏል።

በኛ በኩል የሰንበት ት/ቤቱ አመራሮች ያሰቡትና ያቀዱት ተግባራዊ ሆኖ ያዩት ዘንድ እየተመኘን ቃለ ምልልሱን ለሰጡን ለዘጠኙ ሥራ አመራር አባላት በዝግጅት ክፍሉ ስም ምስጋናችንን እናቀርባለን። ✣




# ልትድን ትወዳለህን?

በዚህ ዓምደ ወጣቱ ትውልድ ራሱን ከዘመኑ ቀሣፊ በሽታ እንዴት መከላከልና ሌሳውን በምን መልኩ ማስተማር እንዳለበት የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ጥናታዊ ጽሑፎች፣ ቃለ መጠይቆች፣ ግጥሞች ወዘተ. ይቀርቡበታል።

## ሰዎች እንዲሠቃዩ እግዚአብሔር ይፈቅዳልን?

መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

እግዚአብሔር መሐሪና ርኅሩኅ ስለ ሆነ የሰው ልጅ በጤናማ ሕይወት እንዲኖር እንጂ በሕማምና በሥቃይ የተሞላ ሕይወትን እንዲኖር አይሻም፤ ደስታውን እንጂ መከራውንና ኀዘኑን ጭንቀቱንም አይፈቅድም።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር፡- ሰውን ከሕማምና ከሥቃይ ከኀዘንም ከሞትም ነፃ አድርጎ ፈጥሮት ነበር። ይህንም እውነት እንደሚከተለው ከብሉይ ኪዳን እንመለከታለን። «እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረም፤ የሰዎች ጥፋትም አያስደስተውም፤ ሕያው ሆኖ ይኖር ዘንድ ሰውን ፈጠረ፤ የዓለም ተፈጥሮም ለሕይወት ነበረ፤ በውስጡም የጥፋት መርዝ (በሽታ) አልነበረም።...ነገር ግን ሰዎች ራሳቸው ሞትን በእጃቸው በቃላቸውም ጠሩት፤ ወዳጅም አስመስሉት ጠፉም...» (ጥበበ ሰሎሞን ፩፡፲፫–፲፮)

የሰው ልጅ ስለ ሕይወቱ የተሰጠውን የሕይወት መመሪያና ትእዛዝ በመተላለፍ ራሱን በራሱ ለድካም ለሕማምና ለሞት ዳርጓል። በተድላ በደስታ እንዲኖርበት፣ እንዲጠብቃትና እንዲንከባከባት የተሰጠችውንም ምድር እንድትረገምና በሙንት እንድትሞላ አድርጓል።

ይሁን እንጂ ሰው፡- እግዚአብሔርን ቢረሳ እግዚአብሔር ሰውን አልረሳውም፤ ሰው ከእግዚአብሔር ሸሽቶ ለመደበቅ ቢሞክር እግዚአብሔር ፈለገው። በተሰጠው ሕሊና ሊጠቀም ባይችል የጽሑፍ ሕግን ሠራለት። ይህም የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያው ክፍል ነው። እግዚአብሔር በዚህ የብሉይ ኪዳን መጀመሪያ ክፍል የሰዎችን ጤንነት በተመለከተ በርካታ መመሪያዎችንና ማስጠንቀቂያዎችን ሰጥቷል፤ ለምሳሌ:-

፩. ከእንስሳት መካከል ንጹሕ የሆነውን ብቻ እንዲመገቡ (ዘሌ.፲፩፡፩–፵፯)

፪. ከሰው አካል የሚወጣ ማናቸውም ፈሳሽ የሚነካውን ማናቸውንም ልብስ ምንጣፍና ዕቃ በውሃ ማጠብ፤ ወይም በእሳት ማቃጠል፤ ወይም መስበር እንደሚገባ (ዘሌ.፲፫፡፵፯–፶፱)

፫. ሰፈራቸውን ሁሉ በንጽሕና መጠበቅ እንደሚያስፈልግ (ዘዳ.፳፫፡፲፬)

፬. በዝሙት ጠንቅ ከሚመጣው ከማናቸውም ደዌ እንዲጠበቁ፤ የባልና ሚስት ፍቅር እንዲጸናና ማኅበራዊ ኑሮ እንዳይበላሽ «አታመንዝር» በማለት ሕግ ሠራላቸው። አብዛኛውን ጊዜ የዝሙት ሥራ ሊስፋፋ የሚችለው ወንዶች ያለ ሚስት፣ ሴቶች ያለ ባል ሲኖሩ ስለ ሆነ ፊት ወንድና ፊት ሴት በኅብረተሰቡ መካከል መገኘት እንደ ሌለባቸው አዘዘ። (ዘዳ.፳፫፡፲፯)

ይህንም ሁሉ የሚያስፈጽሙ ካህናትና ነቢያትን ሾመላቸው።

ካህናት እንደ ነቢያት ልዩ ጥሪንና መልእክትን የማይጠብቁ የኅብረተሰቡ አገልጋዮች በመሆናቸው በየቀኑ የሕዝቡ አስተማሪዎችና አማካሪዎች፣ ጸሎትና መሥዋዕትንም ወደ እግዚአብሔር አቅራቢዎች ነበሩ፤ መቅሠፍት በሕዝቡ ላይ ሲመጣ እግዚአብሔር መቅሠፍቱን እንዲያርቅ ጾምና ምሕላን የሚያውጁ ነበሩ። ይልቁንም እንደ ጤና ባለሙያ ለበሽተኞች ምርመራ የሚያደርጉ እነርሱ ነበሩ፤ ይህንም በዘሌ.፲፫፡፲፬ ምዕራፎች እናያለን።

እነዚህ ምዕራፎች:- በተለያየ የቆዳ በሽታ የተያዙ ሰዎች በሽታውን ወደ ጤናማዎቹ እንዳያጋቡ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው፤ ካህናትም ለበሽተኞች ልዩ ክትትል እንዲያደርጉላቸው የሚያመለክቱ ናቸው። በምዕራፍ ፲፫፡፩–፶፯ በቆዳ ላይ ከሚወጡት እስከፊ በሽታዎች አንዱ ለምጽ እጅግ አስቃቂና በሽተኛውን እንደ ርኩስ የሚያስቆጥር ከኅብረተሰቡም የሚያስገልል እንደነበረ ተገልጦአል።

በብሉይ ኪዳን ዘመን በቆዳው ላይ አንድ ዓይነት በሽታ የታየበት ሰው ወደ ካህኑ ቀርቦ በሽታው ለምጽ ወይም ሌላ ደዌ መሆኑና አለመሆኑ ማስመርመር ግዴታ ነበረበት። በቆዳው ላይ የወጣው በሽታ ለምጽ መሆኑና አለመሆኑ እስኪታወቅ ከታወቀም በኋላ የሚድን ከሆነ እስኪድን ድረስ በሽተኛው ከኅብረተሰቡ ተለይቶ፣ ከሰፈር ወጥቶ፣ ይቆይ ነበር።

በለምጽ ደዌ የተያዘው ሰው ጤናማዎቹ እንዳይቀርቡት ራሱ ማስጠንቀቅ ነበረበት «ልብሱን ቀድዶ፣ ከንብንቡን ከራሱ አውርዶ፣ ከንፈሩን ጋርዶ ‹አትቅረቡኝ› እያለ ይናገራል» (ዘሌ.፲፫፡፵፭)። የለምጽ ደዌ የበሽተኛውን አካል በሙሉ ካዳረሰው ሰውየው ንጹሕ መሆኑ በአደባባይ ይነገር ለታል።




www.ethiopianorthodox.org



«ለምጹ በቁርበቱ ላይ ሰፍቶ ቢወጣ ለምጹ የታመመውን ሰው ቁርበቱን ሁሉ ከራሱ እስከ እግሩ ድረስ እንደ ሸፈነው ለካህኑ ቢመስለው ካህኑ ይመለከታል፤ ለምጹ ሥጋውን ሁሉ ቢሸፍነው የታመመውን ሰው ንጹሕ ነው ይለዋል፤ ሥጋው ሁሉ ፈጽሞ ተለውጦ ነጭ ሆኖአልና ንጹሕ ነው» (ዘሌ.፲፫፡፲፪–፲፫)

ከዚህ በላይ እግዚአብሔር ለሁሉቱም ወገኖች ማለት ለበሽተኛውና ለጤነኞች እንደሚጠነቀቅላቸው እና ያለን። በሽተኛው ፈውስ እስኪያገኝ በገለልተኛ ቦታ እንዲቆይ መደረጉ በአንድ በኩል ለበሽተኛው ልዩ ርዳታ፤ ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን ያሳያል፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሽታው የሚጋባ ከሆነ ወደ ሌሎች እንዳይተላለፍ መጠንቀቅን ያመለክታል።

በ፪ኛ ነገሥት ፭፡፯ እና በዘኁልቁ ፲፪፡፲–፲ ላይ እንደምንመለከተው ለምጽ በእግዚአብሔር ኃይልና ተአምር ካልሆነ በቀር ፈዋሽ መድኃኒት ያለው መሆኑ አልተገለጠም። ሆኖም እግዚአብሔር የማይፈውሰው ደዌ የማያሸንፈው ኃይል ሊኖር ስለማይችል የሚሳነውም አንዳች ነገር ባለመኖሩ በፈቀደ ጊዜ በሽተኞችን ይፈውሳቸዋል። ሥቃያቸውን ሁሉ ያስወግድላቸዋል። በበሽታቸው ምክንያት በኅብረተሰቡ ዘንድ መጠላታቸውን መነቀፋቸውንና መናቃቸውን ሁሉ ያስወግድላቸዋል።

በጠቅላላ ከብሉይ ኪዳን ክፍል እንደምንረዳው በለምጽም ሆነ በሌላ ደዌ ለተያዙት ሁሉ የቅርብ ጠያቂዎች፤ አጽናኞችና አማካሪዎች ካህናት ነበሩ። ሌላው ኅብረተሰብእ ሲር ቃቸው የሚቀርቧቸው ካህናት ነበሩ፤ በሽተኞችን ከጤናማዎች ለይተው ለበሽተኞች የሚጸልዩ መሥዋዕታቸውንም ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡላቸው የእግዚአብሔርንም ይቅርታ የሚያበሥሩላቸው ካህናት እንደነበሩ ግልጽ ነው። (ዘኁል.፲፮፡፵፯–፵)። ጤናማው ኅብረሰብም በማናቸውም አይነት በሽታ እንዳይለከፍ ማስጠንቀቂያ የሚሰጡ እነዚያው ካህናት ነበሩ።

እነሆ ለብሉይ ኪዳን ካህናት የተሰጠው ኃላፊነት ሁሉ የዛሬዎችን ካህናት ይመለከተናል። በክርስትና እምነት ሁሌም ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ናቸው። በሽተኞችም ጤናማዎችም ለእኛ እኩል ናቸው። በሽታቸውን እንጂ እነርሱን ልንጠላቸው አይገባም። ለኤድስ ሕሙማን አስፈላጊውን አገልግሎት መስጠት ተገቢያችን ነው። ኤድስ በማወቅም ባለማወቅም፤ በስህተትም በድፍረትም ሰዎችን ሊይዛቸው ስለሚችል ከመተቸት ከመመጻደቅ ከመሣለቅ፤ በሽተኞችን አንጓጦ ከመመልከት፤ ከሌላው ኅብረተሰብ ተለይተው ይቅርታ የማይገባቸው፤ እግዚአብሔር የረገማቸው ኃጢአተኞች እንደሆኑ አድርገን እንዳንመለከታቸው ማሰብና ይህንም ለሌሎች ማሳወቅ የካህንነታችን ዓላማ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። እርግጥ በሽተኞችን ነፃ ናችሁ፤ ወይም በሽታችሁ ይህ አይነት በሽታ ነው ለማለት አንችልም። የእኛ ድርሻ ማስጠንቀቅ፤ መምከርና ማስተማር፤ ማጽናናትም ነው።

ተላላፊ ደዌ ያለበት ሰው:- በሽተኛ መሆኑን ገልጦ መናገር እንዳለበት በዘሌዋውያን ፲፫፡፵፭ ላይ ተመልክቷል። ይህም ለባልንጀራ ፍቅርና ርኅራኄን ማድረግ ማለት ነው። በሽታው በራስ ብቻ እንዲያበቃ ሌላው በተመሳሳይ በሽታ እንዳይጠቃ ለማድረግ መጠንቀቅና ማስጠንቀቅ ታላቅ ፍቅር ነው። ከዚህም የበለጠ ፍቅር አይኖርም። በሽታውን መዋጋትና መከላከልም ማለት ይህ ነው። ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ያለባቸው ሁሉ ይህን አይነት ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። «ጉድ አያት የእኔም ጉምድ» እንዳለው ሰዉ መሆን አያስፈልግም። በቀል ማድረግ ተገቢ አይደለም። ወንዶች ሴቶችን፤ ሴቶችም ወንዶችን መበቀል ፍጹም ኢ ሰብአዊነት ስለ ሆነ «እግዚአብሔር በቀል የእኔ ነው ይላልና አትበቀሉ» የሚለውን ቃል አጥብቀን ልናስተምር ለእኛ ለካህናት ግዴታችን ነው።

በኦሪት ዘዳግም ውስጥ አስራ ኤላውያን የእግዚአብሔርን ቃል ቢሰሙ ያዘዛቸውንም ትእዛዝ ሁሉ ቢጠብቁ ሕይወታቸውንና ለሕይወታቸው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ የሚመለከት የተትረፈረፈ በረከትን እንደሚያገኙ ተነግሮአል።

በተቃራኒው ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ባይሰሙ ያዘዛቸውንም ሥርዐቱንና ትእዛዙን ባይጠብቁ ባያደርጉም ሕይወታቸውንና ለሕይወታቸው አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች ሁሉ የሚነኩ የተለያዩ መቅሠፍቶችና በሽታዎች እንደሚደርሱባቸው ተዘርዝሮ ተገልጦአል።

በዚህም ክፍል የተዘረዘሩት የበሽታ አይነቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ቸነፈር፤ ክሳት፤ ንዳድ፤ ጥብሳት፤ ትኩሳት (ቁ.፳፩–፳፪)
- ፈውስ የሌለው ቁስል፤ ዕባጭ፤ ቋቁቻ፤ ችፌ፤ ዕብደት፤ ዕውርነት (ቁጥር ፳፯–፳፰)
- ለብዙ ዘመን የሚቆይ ደዌ፤ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያልተጠቀሰ ሌላ ደዌ፤ የልብ መንቀጥቀጥ (ቁ.፶፱–፷፩)

እነዚህ በሽታዎች ሁሉ በሕዝቡ ሊመጡ የሚችሉ መሆናቸውን እግዚአብሔር እንደ ተናገረ ስንሰማ ጨካኝና ለፍጥረቱ ርኅራኄ የሌለው አምላክ እንደ ሆነ የሚሰማን እንኖር ይሆናል። ነገር ግን ድርሰ ነገሩ እንደዚህ አይደለም።

በዘዳግም ፳፰ ውስጥ የተጠቀሱት በረከቶችና መርገሞች ጤናዎችና በሽታዎች፤ ሕይወትና ሞት በሰዎች ላይ የሚከሰቱት በእግዚአብሔር ጭካኔና ምሕረት የለሽነት ሳይሆን በሕዝቡ ምርጫና ፈቃድ መሆኑ በዚሁ መጽሐፍ በምዕራፍ ፴ ውስጥ በሚገባ ተብራርቶ ተነግሮአል።

«በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን፤ በረከትንና መርገምን፤ ክፉትንና መልካምነትን አኑሬአለሁ እንግዲህ:- አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ፤ የሕይወትህና የዘመንህ ርዝመት ራሱ እግዚአብሔር ነውና እግዚአብሔርን ለመውደድ፤ ቃሉንም ለመስማት ምረጥ።» (ዘዳ.፴፡፲፩–፳)

ከዚህ ላይ ሁለት መንገዶች ብቻ እንዳሉ ይታያል። እነርሱም አንዱ የሕይወት ሁለተኛው የሞት መንገዶች ናቸው። በሁለቱም መንገዶች ለመጓዝ ምርጫው የእያንዳንዱ ሰው ነው። እግዚአብሔር እኛ ራሳችን ምርጫ እንድናደርግ ይፈልጋል። ሞትና ሕይወት በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ያሉ ቢሆንም ሰውም ስለ ሕይወቱና ስለ ሞቱ የራሱ የሆነ የኃላፊነት ድርሻ አለው። ነፃ ፈቃድ አለው።

በዘዳግም ፳፰ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ዛሬም ሞትና ሕይወት ፊታችን ለምርጫ ቀርበዋል። ከሞት ይልቅ ሕይወትን መምረጡ የእኛ ፈንታ ነው። ሕይወትንም መምረጥ የምንችለው ከዘዳግም ፳፰፡፲፱ እንደምንረዳው:- እግዚአብሔርን በመውደድ ነው፤ ቃሉን በመስማት ነው፤ ትእዛዙንም በመጠበቅ ነው።

እነሆ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ የሞት መንገድ ሆኖ በዓለም ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ተዘርግቷል። ሰዎች እያወቁም ሳያውቁም በዚህ መንገድ ይጓዛሉ።

የኤድስ ምክንያቶች ብዙዎች እንደ ሆኑ በዐዋቂዎች ቢነገርም ዋናውና አውራው ምክንያት ግን ከተፈቀደው ሕጋዊ ሩካቤ ውጭ የሚፈጸም ኢ ሕጋዊ ሩካቤ ማለት:-

- አንድ ወንድ በአንዲት ሴት፤ አንዲት ሴት በአንድ ወንድ አለመወሰን፤
- የጋብቻን ክቡርነት በማቃለል ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በልቅነት መኖር፤
- ሌላም ሕገ ወጥ የሆነ ግብር መፈጸም (ሰዶማዊ ግብር) ነው።

ሰዎች ይህን ሁሉ እንዲያደርጉ የሚገፋፋቸው ሌላ የውጭ ኃይል ሳይኖርባቸው በራሳቸው ነፃ ፈቃድና ምርጫ ያደርጉታል። ይህም ሁኔታ ሕይወትን በሞት በረከትን በመርገም መለወጥን ስለሚያመለክት የሕይወት መንገድ የሆነውን:-

- የአንድ ለአንዲት ጋብቻን
- ከማናቸውም አይነት ዝሙት ለመራቅ «አታመንዝር» የሚለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ላገቡና ላላገቡ ሁሉ ማስተማርና መምከር ማስጠንቀቅም ከካህናትና ስለ ኤድስ አደገኝነት ከፍተኛ ግንዛቤ ካላቸው ሁሉ ይጠበቃል።

በዘዳግም ፳፰ የተጠቀሱት በሽታዎች ሁሉም በሰዎች ላይ እንደ ደረሱና ሰዎቹን እንደ ጐዱ በሌላ ቦታ ተጠቅሰው አልተነገሩም፤ «በተለይ ፈውስ የሌለው ደዌና ለብዙ ዘመን፤ የሚቆይ» ደዌ በመባል የተጠቀሱት በሽታዎች ከኃጢአት ምሳሌነታቸው በቀር ተደጋግመው አልተወሱም። የሕዝቡ መንፈሳውያንና ሥጋውያን መሪዎች ከእግዚአብሔር የተላለፈውን ማስጠንቀቂያ በሚገባ ለሕዝቡ ስላስተላለፉና ሕዝቡም ስለ ተጠነቀቁና የተሰጠው የተነገራቸውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለ ፈጸሙ እንደ ሆነ ግልጥ ነው።

ዛሬም ስለ መንፈሳዊ ሕይወትና መዳን ብቻ ሳይሆን ስለ ሥጋና መንፈስ ሕይወትና መዳን የእግዚአብሔርን የሕይወት ቃል ለማስተላለፍ ኃላፊነትና አደራ የተጣለባቸው ካህናት በኤች አይ ቪ ኤድስ የተጠቁትን ለመርዳት ለመንከባከብ፤ ለማጽናናትና በየጊዜውም ለመጠየቅ፤ ያልተያዙትንም ለማስጠንቀቅ ከብሉይ ኪዳን ካህናት ምሳሌን ሊወስዱ ያስፈልጋል። ❖

### ማደሪያ

ለወፍ – ጐጆ

ለዝንጀሮ – ገደል

ለቀበሮ – ጉድጓድ

ላንበሳ – ዋሻ

ለምስጥ – ኩይሳ

ለጉንዳን – አፈር

ለበግ – ጉረኖ

ላህያ – ግርግም

ለበቅሎ – ጋጥ

ለዶሮ – ቆጥ

ለእባብ – ካብ

ለከብት – በረት

ለሰው – ቤት

ለክርስቶስ – መቅደስ

ያስፈልገዋል!

እሱ ግን በትሕትና

«ሁሉ እያለው ራሱን ባዶ አደረገ»


ዲ/ን ዘመድሁን አበበ መ/ር



www.ethiopianorthodox.org

# ከምኞት በስተጀርባ (የነገ ሰው ለመሆን)

ከመምህር ፍስሐ ካሤ



**የ**ተስተካከለ ሕይወት የሰላምና የደስታ ኑሮ ለመኖር ሁላችንም እናስ ባለን፤ እንመኛለን፤ ግን ስንቶቻችን እንሆን የተመኘነውን ያገኘንና የም ናገኝ? መልካም መመኘት በራሱ መልካም ነው። በአንፃሩ ደግሞ መጥፎ ምኞት መጥፎ ነው። በእርግጥ መል ካምም ይሁን መጥፎ ሁሉም የተመ ኘውን አያጣም፤ ስለዚህ የተመኘነ ውን የምናገኝ ከሆነ መጥፎውን ምኞት ትተን መልካሙን ምኞት እንመኝ። «ቸር ተመኝ ቸር እንድታገኝ» የሚለ ውን ሀገራዊ ስነ ልቡናዊ ምክር እዚህ ላይ ማንሳቱ ተገቢ ነው።

ምንም እንኳ መልካም ምኞት መልካም ቢሆንም በምኞት ብቻ ግን ወደ አሰብነው መድረስና የተመኘነ ውን ማግኘት አይቻለንም። በሕይወ ታችን የተሻለ ደረጃ ለመድረስና ከም ኞት የተሻለ ነገር ማድረግ አለብን። ምኞታችን ወደ ተግባር የሚለወጥበ ትን መንገድ መፈለግ፤ መረዳትና መዘጋጀት ይኖርብናል። ምኞት ከም ኞትነቱ አልፎ ተግባራዊ ሊሆን የሚች ልበትም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ፍሬ ሃሳቦች በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ገብተው በተግባር ሲገለጹ ብቻ ነው።

## ፩. ራእይ

ራእይ ብዙ ትርጉም፤ ስፋትና ጥልቀት ያለው ምሥጢር አዘል ቃል ነው። በመጽሐፈ ምሳሌ ፳፱፥፲፰ ላይ «ራእይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆ ናል» በማለት የራእይን ጠቀሜታ ያስ ረዳናል «ራእይ» የሚለው ቃል በግ ዕዙ «መምህር» ተብሎ ተተርጉ ሟል። ይህም ከዕብራይስጡ ተያይዞ እንደ መጣ ይነገራል። በብሉይ ኪዳን «ራእይ» ወይም «ረአይ» ማለት «መምህር፤ መሪ፤ መካሪ፤ አስተዳ ዳሪ» ማለት ነው ሲሉ ተርጉመውታል።

ራእይ ዘኢሳይያስ፤ ራእይ ዘሔር ምያስ፤ ራእየ ዮሐንስ የሚለውን ስን መለከት ደግሞ «ራእይ» ማለት መለ ኮታዊ መገለጥ ወይም መንፈሳዊ መገ ለጥ ማለት እንደ ሆነ እንርዳለን። ለም ሳሌ ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ ስድ ስትን ስንመለከት ነቢዩ ኢሳይያስ ከአ ያቸው መንፈሳዊ መገለጦች መሀል ሦስቱን እንመልከት።

ሀ. ልዑል እግዚአብሔርን በግርማ መለኮቱ በሰማያዊ ዙፋኑ ቅዱሳን መላእክቱ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ» እያሉ ሲያመሰግኑት አየ (ኢሳ.፮፥፲፴)

ለ. ነቢዩ እሱ ራሱን ኀጢአተኛ መሆኑን አየ ተረዳ። ነቢዩ በመንፈ ሳዊ ዓይን የረከሱ ከንፈሮቹን ኃጢአተኛነቱን ማየትና መረዳት የቻለው ወደ እግዚአብሔር ከቀረ በና እግዚአብሔርን ካየ በኋላ ነው (ኢሳ.፮፥፭)።

ሐ. ነቢዩ የሕዝቡን በደልና ኃጢአት አየ። ነቢዩ በመጀመሪያ የሌሎቹን ሰዎች ወይም የሕዝቡን በደል አላየም፤ ነገር ግን የራሱን በደል የራሱን ኃጢአት በመጀመሪያ ተረዳ፤ ራሱን በደል የሌለበት ንፁህ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደ ነበረ ሳይሆን ከንፈሮቻቸው በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል የነበረ ከንፈሮቹ የረከሱበት ሰው መሆኑን ነው።

የመንፈሳዊ ተልዕኮ ዋናው መለ ኪያ በእግዚአብሔር መጠራት፤ በእግ ዚአብሔር መመረጥ፤ ወደ እግዚአ ብሔር መቅረብ፤ እግዚአብሔርን ማየ ትና ድምፁን መስማት ነው።

በሦስተኛ ደረጃ የራእይን ትር ጉም ስንመለከት በማንኛውም ሰው ሕይወት ውስጥ ያለ የነገ ተስፋ የሩቅ ዕይታ ነው፤ ስለ ወደፊቱ ኑሮ የም ናስበው የምናሰላስለው ሐሳባዊ ውጥን ነው። በእንቅልፍ ጊዜ የሚታይ ሳይ ሆን በእውን የሚታለም ሕያው ሕልም ነው። ስለ ነገው ኑሮአችን ስለ ወደፊቱ ሕይወታችን እናስባለን እናል ማለን። ይህ በሩቅ የምናስበውና የም ናልመው ራእይ የዛሬ ዝግጅት የነገ ምርት ነው። የዛሬ ቡቃያ የነገ እሸት ነው። የዛሬ ሕልም የነገ እውን ነው።

በተስፋ የሚታይና የሚታለም የወደፊት ራእይ ባይኖር የሕይወ ታችን ትርጉም ለመረዳት ያዳግት ነበር። ሰው ያለ ራእይ ማሰብ፤ ማቀ ድና መሥራት አይችልም። በተስፋና በዓይነ ኅሊና የሚታይ የነገ ማንነታ ችንና ኑሮአችን በራእያችን ይለካል፤ እግዚአብሔር ሰውን ከብሩሕ ራእይ ከሕያው ተስፋ ጋር ነው የፈጠረው፤ እግዚአብሔር ለሰው ከሰጠው ሥጦ ታዎች መሐል አንዱና ዋናው የማ ሰብ፤ የማገናዘብና የመለየት ችሎታ ነው። እውነተኛ ራእይ ማስተዋልን ይጠይቃል፤ እውነተኛ ራእይ እርቆ፤ አስፍቶና አጥርቶ ማሰብን ይጠይ ቃል። እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈ ልገው አርቀን እንድናስብና የነገውን (የወደፊቱን) በሩቅ እንድንመለከት ነው።

ራእይ የዕለት ከዕለት መመሪያ ችንና የተስፋ መሰላላችን የነገ ዕይታ ችን ቢሆንም ሁላችንም አንድ ዓይነት ራእይ ሊኖረን አይችልም። እያንዳ ንዳችን ከእግዚአብሔር የተሰጡን ልዩ ልዩ ሀብተ ፀጋዎች ወይም መክሊቶች አሉን። የተሰጡንን መክሊቶች ለይቶ ማወቅ፤ ማባዛት፤ ማስፋትና ማሳደግ ግን የእያንዳንዳችን ድርሻ ነው።





ስለዚህ አንድን ነገር ከመጀመ ራችን በፊት በርጋታና በጥልቀት ማሰብ መመርመርና መመራመር ይኖርብናል። ምንም እንኳ ትምህርት ለሁሉም አስፈላጊ ቢሆንም ብዙ የትምህርት ዓይነቶች ስላሉ ምን ዓይነት ትምህርት ቢማር ወይም ብትማር እንደሚጠቅመው (እንደሚ ጠቅማት) አስቀድሞ የማወቁ፤ የመ ረዳቱ ጉዳይ የተማሪው (የተማሪዋ) ኃላፊነት ነው። ለምሳሌ የሕግ ትም ህርት አለ፤ የግብርና ትምህርት አለ፤ የቋንቋ፤ የታሪክ፤ የሒሳብ ትምህር ቶችና የመሳሰሉት አሉ፤ እንዲሁም በሥራው ዓለም ስንሄድ የግብርና ሥራ፤ የንግድ ሥራ፤ የትርጉምና ስነ ጽሑፍ፤ የሒሳብ ሥራ፤ አስተዳደ ራዊና የመሳሰሉት የሥራ ክፍሎች አሉ፤ ምን ዓይነት ትምህርት ቢማርና በየትኛው የሥራ ክፍል ቢሠማራ ፍሬ አማ እንደሚሆን ማወቅ፤ መረዳትና መምረጥ የሚችል ሰው በራእዩ የሚሰ ማራ ብልህና አስተዋይ ሰው ነው።

## ፪. ዓላማ

ዓላማ ከራእይ ቀጥሎ የሚመጣ ቃለ አመክንዮ ነው። ጥሩ ዓላማ በብ ሩሕ ራእይ ላይ ይመሠረታል። ዓላማ የአንድን ነገር ሐሳብ ወይም ድርጊት ይገልጻል፤ ምክንያቱን ይዘረዝራል። ያለ ምክንያት አንድ ነገር አይታሰ ብም፤ ያለ ምክንያት ድርጊት አይፈ ጸምም።

አንድ ሰው አንድን ነገር ለማድ ረግ ሲያስብ ወይም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ ሲያስብ ምክንያት ይኖረዋል፤ ታዲያ ይህ ምክንያት ነው ዓላማ የሚለው። ለምን አሰበው ለምን አደረገው ለሚለው ጥያቄ በቂ መልስ፤ የሚያድስ፤ የሚጠግን ምክን ያታዊ መልስ ከተገኘ ባለ ራእይና ዓላማ ያለው ሰው ያሰኛል። እስቲ በን ጉሥ ሳኦልና በዳዊት መሀል የነበ ረውን ሁኔታ እንደ ምሳሌ እናንሳ። ሳኦል ዳዊትን ለመግደል በዱር በገ ደሉ በየዋሻው እየፈለገ ሲሄድ እንኳን ዳዊትን ሊይዝና ሊገድል ቀርቶ ራሱ በዳዊት እጅ አልፎ ተሰጠ። ይሁን እንጂ ዳዊት ሳኦልን ሊያንገላታው ሊያዋርደውና ሊገድለው አልፈ ለገም። አብረውት በዋሻ የነበሩት ሰዎችም «እነሆ ጠላትን በእጅህ አሳ ልፌ እሰጠዋለሁ ባይንህም ደስ የሚ ያሰኝህን ታደርግበታለህ ብሎ እግዚ አብሔር የነገረህ ቀን እነሆ ዛሬ ነው» ሲሉት አልተቀበላቸውም ፩ሳሙ. ፳፬፥፩–፳፪። ራእይ ያለው ሰው፤ ዓላማ ያለው ሰው መልካም ምክርን እንጂ ክፉ ምክርን አይቀበልም።

## ፫. ግብ

ስለ ራእይ ስንናገር ምን ማድረግ እንዳለብን በሩቅ የምናስበውና የም ንመለከተው የነገው ኑሮአችን እንደ ሆነ እንዲሁም ስለ ዓላማ ስንናገር ለምናስበውና ልናደርገው ለምንፈ ልገው ነገር በቂ ምክንያት ሊኖረን እንደሚገባ፤ ለምን ያንን ወይም ይህን ማሰብና ማድረግ እንደ ፈለግን ምክን ያቱን ማወቅና መረዳት እንደሚገባን ሲሆን ግብ የሚለው ቃል ግን ከዓላማ ቀጥሎ የሚመጣ የመነሻ መድረሻ ነው። የራእይ መድረሻ የዓላማ ስኬት ነው።

በሩቅ በራእይ ያየነው ምን እንደ ሆነ አውቀናል፤ ምክንያቱንም (ዓላ ማን) ተረድተናል። ይሁን እንጂ ያንን ያየነውን ማግኘት፤ መያዝና ተፈጽሞ ማየት እንፈልጋለን፤ ወደ አሰብነውና በሩቅ ወደተመለከትነው ደርሰን ማየት እንሻለን፤ በመሆኑም ራእያችንና ዓላ ማችን ግቡን እንዲመታ ማድረግ የሚ ገባንና የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን።

ስለ ግብ ስንናገር በሀገራችን የገ ናን ጨዋታ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ የኳስ ጨዋታን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ተጫዋቾቹ ገናዋ (ሩርዋ) ወይም ኳስዋ በተፈለገው ቦታ መግባት ስትችል ግብ መቱ፤ ጎል አስ ገቡ ይባላል፤ እዚህ ላይ እስከ አሁን ያየናቸውን ሦስቱን ማለትም ራእ ይን፤ ዓላማንና ግብን በአጭሩ ከስፖር ተኞች (ከኳስ ተጫዋቾች) ጋር በማነ ፃፀር እንመልከት። የአንድ ታዋቂ ስፖርተኛ ወደ ስፖርት ዓለም ከመግ ባቱ በፊትና ስፖርተኛ ለመሆን ገና በማሰብ ላይ ሳለ ምን ነበር ራእዩ ቢባለ ወደ ስፖርት ዓለም መግባትና ስፖር ተኛ መሆን ነበር። ዓላማው ደግሞ ስፖርተኛ በመሆን ለራሱ፤ ለሀገሩና ለወገኑ የሚያገኘው ወይም የሚያስ ገኘው ዝና፤ ክብርና ጥቅም ሲሆን ግቡ ግን ራእዩንና ዓላማውን እውን ማድ ረግ ነው። ግቡ በውድድሩ ቀድሞ መገኘትና የድል ፍሬውን (የወርቅ ዋንጫቸውን) ማግኘት ነው።

ራእይ ያለ ዓላማ እንደማይቻል ሁሉ ዓላማም ያለ ግብ ሊፈጸም አይ ችልም። ራእይ ያለው ሰው ዓላማውን አይስትም፤ ራእይ ያለው ሰው ግቡን እስኪመታ በዚያው በራእዩ ፀንቶ ይጓ ዛል። ራእይ ያለው ሰው በተስፋ ይኖ ራል፤ በተስፋ ይራመዳል፤ ራእይ ያለው ሰው የሚያስበውን፤ የሚናገረ ውንና፤ የሚያደርገውን ያውቃል። ራእይ ያለው መነሻውንና መድረሻ ውን ያስተውላል፤ ራእይ ያለው ሰው በሕይወት መሰናክሎችና ውጣ ውረ ዶች አይበገርም፤ ራእይ ያለው ሰው ሁል ጊዜ ከነገ በስተጀርባ ደስታን ያስባል፤ ራእይ ያለው ሰው በጎውን እንጂ ክፉውን አያስብም፤ ክፉንም በክፉ አይቃወምም (ሮሜ.፲፪፥፲፯) ራእይ ያለው ሰው ከስህተቱ ይማራል (ይታረማል)፤ ራእይ ያለው ሰው ግቡን ለመምታት የዕቅድ መረቡን ይዘረጋል።

## ፬. እቅድ

እቅድ ለራእይ አራተኛ፤ ለዓላማ ሦስተኛ ለግብ ሁለተኛ በመሆን የሥል ጣን ደረጃውንና የሥራ ድርሻውን መያዝ ይችላል። ራእይ «ምን» የሚለ ውን ጥያቄ ያዘለ ነው፤ ስለ ወደፊቱ ምን እንደምናስብ በሩቅ ምን እንደ ምናልም እግዚአብሔር በእኛ አማካ ይነት ሊፈጽመው ያለው መልካሙ ነገር ምን እንደ ሆነ የምንረዳው በራ እይ ሲሆን ዓላማ «ለምን» የሚለውን ጥያቄ ያስከትላል። ቀደም ሲል እንዳ የነው ምክንያቱን ያስረዳል፤ አንድ ሰው አንድን ነገር ለማድረግ ቢፈልግ «ለምን» ተብሎ ሲጠየቅ መልሱን (ዓላማውን) መግለጽና መዘርዘር ይኖ ርበታል። ግብ ደግሞ «እስከ ምን ድረስ» ወይም «እስከ የት ድረስ እስከ መቼ ድረስ» የሚለውን ሐሳብ ጥያቄ ሊያስከትል ይችላል።





www.ethiopianorthodox.org

እቅድ ግን በመጨረሻ «እንዴት» የሚለውን አፈፃጸማዊ ጥያቄ ይዞ ይቀርባል፤ «እንዴት ነው ምን (ራእይ) ለምን (ዓላማ) እና እስከ ምን (ግብ)» የሚሉት ጥያቄዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት የሚለውን ሐሳብ አጠቃሎ ያቀርባል። እንዴት ነው በራእያችን መራመድ የምንችለው? እንዴት ነው ዓላማችን ሊሳካ የሚችለው? እንዴት ነው ራእያችንና ዓላማችን ግቡን ሊመታ የሚችለው? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ መገኘት ያሻቸዋል። እንዴት? ለሚለው ጥያቄ መልስ ተፈልጎ መገኘት ካልተቻለ ነገሩ ሁሉ የእምቧይ ካብ ይሆናል። ጊዜንና ጉልበትንም በከንቱ ማባከን ይሆናል።

ብዙ ሰዎች ብሩሕ ራእይ፤ ቅን ዓላማና ግብ ይኖራቸውና ዕቅድ ላይ ግን ይበላሽባቸዋል። ለምሳሌ የነቢዩ ሙሴን ሕይወት ስንመለከት በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰፊና ብሩህ ራእይ የነበረው የዓላማና የግብ ሰው ነበር። ራእዩ ዓላማውና ግቡ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ትእዛዝ መፈጸም፤ ሕዝበ እስራኤልን ከተጫኑባቸው የመከራ ቀንበር ማላቀቅና ወደ ተስፋይቱ ምድር መውሰድ ነበር። ይሁን እንጂ እቅድ ይጎድለው ነበር። እግዚአብሔር ከሰጠው መለኮታዊ ተአምርና ረድኤት ባሻገር እርሱ ሊያደርገው የሚገባውን እቅድ ወይም ዝግጅት አላደረገም ነበር። እግዚአብሔር ከእርሱ የሚጠብቀውን እቅድ ባለመዘርጋቱ ሕዝቡን ከጥዋት እስከ ማታ በፍርድ ወንበር ዙሪያ ያጉላላቸው ነበር። ራእይ ዓላማና ግብ ቢኖረውም የሥራ አፈፃጸሙ (እቅድ) ላይ ግን ለሕዝቡና ለሥራ ቅልጥፍና የተመቸ አልነበረም። ለዚህም ነው አማቱ ዮቶር ሊገስጸውና ሊመክረው የጀመረው። (ዘጸ. ፲፰፥፲፫–፲፯) ሙሴ ሕዝቡን እየመራ ወደ ምድረ ርስት ኢየሩሳሌም መውሰዱን እንጂ በየጊዜው በሕዝቡ መሀል ይከሰት ለነበረው ችግር ቀልጣፋ መፍትሔ መስጠት ያልቻለው አማቱ ዮቶር ያቀረበለትን ሐሳብና ምክር ቀደም ብሎ መገንዘብና መረዳት ባለመቻሉ ነበር።

ስለ እቅድ ስንናገር ስለ ሥራ አፈፃፀም መናገራችን ነው። አንድ ሰው አንድን ነገር ለማድረግ ራእይና ዓላማ ቢኖረውም ራእዩና ዓላማው መቼ፤ የትና እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን ማወቅና መረዳት ይኖርበታል። ሌላው ከዚህ ጋር መታየት ያለበት ራእዩና ዓላማው በተቀላጠፈና በቀና መንገድ ግቡን እንዲመታ አብረው ከጎኑ ወይም በዙሪያው የሚሰለፉ ሰዎች ያስፈልጉታል። ለሙሴ የጎደለው ይኸው ነበር። ከግብፅ ጀምሮ ቀይ ባህርን ከተሻገረም በኋላ ለሥራው የሚገቡና የሚመቹ ሰዎችን አልሾመም ነበር። እንግዲህ የሰዎችን እውቀታቸውን ብቻ ሳይሆን ሀብተ ፀጋን (ተሰጥኦን) ታማኝነትንና የአቅም ሁኔታዎችንም ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው፤ ይህ ከሆነ ራእያችንና ዓላማችን በተፈለገው መንገድ ግቡን ሊመታ ይችላል።

የግልም ሆኑ የጋራ እንቆቅልሾቻችን መፍትሔ ሊኖራቸው የሚችሉት እስከ አሁን በተከታታይ የተመለከትናቸው አራት ቃላት (ራእይ፤ ዓላማ፤ ግብና እቅድ) ደረጃ በደረጃ ሊፈጸሙ ከቻሉ ነው። ራእይ፤ ዓላማና ግብ ሊቀነስ ሊሰረዝ አይችልም እቅድ ግን በመጀመሪያ ግቡን ሊመታ ካልቻለ እንደ ገና በአዲስ መንገድ እየተሻሻለ መቅረብ የችላል። እንግዲህ የነገ ሰው ለመሆን መልካሙ የሆነውንና የሚበጀውን መመኘት ይገባል። የነገ ሰው ለመሆን ከመልካም ምኞት ወደ ብሩሕ ራእይ መሸጋገር ያስፈልጋል። የነገ ሰው ለመሆን ዓላማ ይዞ መነሣትን፤ ወደ ግብ መገሥገሥንና በእቅድ መራመድን ይጠይቃል። ❖

## ስለ መናፍቃን

☞ ጉጉት አሞራ ናት፤ ፊትዋም እንደ ድመት ነው፤ ድምጧም የከፋ ነው። መናፍቃንም መልካቸው እንደ ሰው ነው፤ ሥራቸው ግን የሰይጣን ነው።

☞ ጉንዳን በደረሰበት እንደሚቆነጥጥ መናፍ ቃንም በደረሱበት ጤና የላቸውም።

☞ እንጨትና ሣር ዝናም አብቅሏቸው አንዱ ባጥ፤ አንዱ ግዳግዳ እየሆኑ አናስገባም ይሉታል፤ መናፍቃንም የፈጠራቸው እግዚአ ብሔርን ትተው ለፍጡር ይሰግዳሉ።

☞ ዘንዶ ቢረዝም አሁን ምን ይጠቀማል፤ የሰ ይጣን ማደርያ ሆነ እንጂ፤ እግርና እጅ እንኳ የለውም። መናፍቃንስ ቢበዙ ብልሃት ሳይኖራቸው ምን ይሆናሉ።

☞ ሳማና አለብላቢት ለምለም መስለው እንዲለበልቡ፤ መናፍቃንም ሲቀርቧቸው እንደዚያ ናቸው።

መጽሐፍ ጨዋታ – ሥጋዊ ወመንፈሳዊ ከዘነበ ኢትዮጵያዊ ፲፱፻፹፮ ዓ.ም



# ሥርዓተ ቤተክርስቲያን



ሰመሆኑ ሕግ ምንድን ነው? ከየትስ መጣ? ባለቤቱስ ማን ነው? ለምንስ መጣ? በሰዎች አመለካከትና እምነት ሕግ ከተለያዩ ሰዎች (ምሁራን) እና ከተለያዩ ሰዎች (ገዥዎች) የመጣ መስሎ ይታይ ይሆናል። ነገር ግን ሕግ የመጣው ወይም የተሰጠው ከእምላክ ነው፤ ባለቤቱም ራሱ አምላክ ነው። በሕግ አምላክ መባሉ ይህንኑ ያረጋግጣል።

### ሕግ በሁለት አበይት ክፍሎች ይከፈላል

፩ኛ. ሰማያዊ (አምላካዊ) ሕግ

፪ኛ. ምድራዊ (ሰብአዊ) ሕግ ናቸው።

ሰማያዊ (አምላካዊ) ሕግ በሦስት ክፍለን ማየት እንችላለን። እነሱም:-

፩. ሕገ ልቡና

፪. ሕገ ኦሪት

፫. ሕገ ሐዲስ ናቸው።

### ሕገ ልቡና ባለሁለት አንቀጽ ነው።

፩ኛ. የሚገባህንና የተፈቀደልህን አድርግ

፪ኛ. የማይገባህንና ያልተፈቀደልህን አታድርግ፤ ኦሪት ዘፍ.፩፥፲፮–፲፰

- ሕገ ኦሪት በ፲ አናቅጽ የተከፈለ ነው፤ ኦሪት ዘጸአት ፳፥፩–፳፮፤ ዘሌዋ.፲፱
- ሕገ ሐዲስ በ፮ አናቅጽ የተከፈለ ነው፤ ማቴ.፭፥፲፯–፴፮። እንግዲህ ከላይ የጠቀስናቸው ሕግጋት በዘመነ አበው፤ በዘመነ መሳፍንትና በዘመነ ነገሥት ለመንፈሳዊም ሆነ ለሥጋዊው ዳኝነት ጉዳይ ፍትሕ ርትዕ ሲሰጥባቸው እንደ ነበር ታሪክ በሰፊው ያስረዳል።

ነገር ግን ከጊዜ በኋላ የሰዎች ሥጋዊ ፍላጎትና አመለካከት ከመንፈሳዊው የአኗኗር ሥርዓት በእጅጉ እያየለና እያፈነገጠ በመሄዱ ሥጋዊው ሕግ ከመንፈሳዊ ሕግ ተለይቶ የራሱን መንገድ አዘጋጅቶ መጓዝ ከጀመረ ዘመናትን አስቆጥሯል።

## በሕግ አምላክ!

ከመሪጌታ ምናሴ ወልደ ሐና

ምንም እንኳ ሮማውያን ከላይ ከተጠቀሱት ሕግጋት ጽንስ ሃሳቡን ቀንጭበው በመውሰድ ለአገዛዛቸው በሚያመች መንገድ የሕግን በር በመክፈት ቀዳሚዎች ቢሆኑም ሕግ በትክክል የተጀመረውና ሥራ ላይ የዋለው:-

፩ኛ. የማግና ካርታ ሠነድ (Magna carta) በ፩ ሺህ ፪፻፲፭ በእንግሊዝ

፪ኛ. በአሜሪካና ፈረንሳይ በ፲፯ኛና በ፲፰ኛው ክፍለ ዘመን ነበር። እነዚህ ሕጎች ዛሬ ድረስ በየትኛውም ሀገር ለሚወጣው ሕግ ሁሉ እንደ ዋቢ ሆነው ይጠቀሳሉ። ዛሬ በዓለም ያሉ አህጉር ወይም መንግሥታት ሁሉ የየራሳቸው ሕግ አላቸው።

የእያንዳንዱ ሀገር ሕግ እንደየ ባህሉ፤ ሃይማኖቱና እድገቱ መጠን ይለያያል። የሕግን መሠረታዊ ተፈላጊነቱና ጠቃሚነቱን አስመልክቶ ብዙ መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም ባጭሩ የሀገርን ሰላምና ሉዓላዊነትን ከውጫዊ ኃይል ጥቃት ለመከላከልና የሕዝብን መብት፤ ሀብትና ንብረት ለመጠበቅ ነው።

ዋናው የጽሑፌ ርእስ መሠረተ ሃሳብ ስለ ሥጋዊ ሕግ በሚመለከት ትንተና ለመስጠት አይደለም። ነገር ግን ሥጋዊው ሕግ ከመንፈሳዊው ሕግ በኋላ ተነስቶ እየጠነከረና እየዳበረ ሲሄድ በአንጻሩ ደግሞ መንፈሳዊው ሕግ ችላ እየተባለ ከመሄዱ የተነሳ በቤተ ክርስቲያናችን ዙሪያ የሚታዩት ግድፈቶች በተለይ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ምሁራን እርምት እንዲሰጡበትና በእጅጉ እንዲያስቡበት ለመጠቆምና ለማሳሰብ ነው።

ለምሳሌ በሥጋዊው ሕግ ድንጋጌ አንድ ሰው ሳይማር እና ሳያውቅ ለምሁሩና ለአዋቂው የተገባውን ቦታ ይዞ ቢገኝ ይጠየቅበታል፤ ይከሰስበታል በመጨረሻም ይቀጣበታል። ከሰረቀ፤ ከቀጠፈና ከዋሸም እንደዚሁ፤ ታዲያ በቤተ ክርስቲያናችን ዙሪያ ሳይማሩ ተምረናል፤ ሳያውቁ አውቀናል፤ በማለት ባልበቁበትና ባልተገባቸው ቦታ በኃላፊነት የተቀመጡ ስንት ናቸው? ቅዱስ መጽሐፍ «ኢታውትር እዴከ ለእንተ ኢኮነት እንቲአከ፤ ላንተ ላል ተፈቀደችልህ ስጦታ (ገንዘብ) ለመቀበል እጅህን አትዘርጋ» ይላል። በተለይ ደግሞ ሳይማሩ ንባብን፤ ሳያስተካከሉ ምስጢርን፤ ሳያደላድሉ ክህነልሁን፤ ልሰበክ፤ ላስተምር ማለት ሕግ መንፈሳዊ በጥብቅ ይከለክላል።

ፍትሐ ነገሥት በ፮ኛው አንቀጽ ቁጥር ፪፻፲፪ ላይ «ቀሲስ ዘኢየአምር ነገረ መጻሕፍት አምላካዊያት ሠናያት ወፈድፋደሰ አርባዕተ ወንጌላት መልካም የሆኑትን የአምላክን አንድነት፤ ሦስትነት፤ ምልአት ስፋት፤ ከሃሊነት ሕያውነትና ፈጣሪነት፤ የሚያስረዱ መጻሕፍትን ሳይማር ይልቁንም የአራቱን ወንጌላት ትርጓሜ ያላወቀ፤ ያል



www.ethiopianorthodox.org

ተማረና ያልተረዳ አንድ ስንኳ ቄስ እይሁን» በማለት ያስርዳል። በአሁኑ ወቅት ግን ሳይማሩና ሳያውቁ ቀሲስ እገሌ ቀሲስ እገሌ፣ በሚል ስያሜ እንደ ፋሽን ስም አድርገው ሲጠሩበት ተዘውትሮ ይሰማል። ለመሆኑ ቀሲስ ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በውል ይታወቃልን?

በመሠረቱ ሊቃውንት እንደሚያ ጉቱትና እንደሚተረጉሙት ከሆነ ቀሲስ ማለት «ሊቅ፣ የተማረ፣ አበ ሕዝብ፣ መገሥጸ ሕዝብ፣ መሥተስርየ ሕዝብ ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ አንድ ሰው ቄስ ከመሆኑ በፊት በሚገባ ሊማር የግድ ነው። ሌላውን ለመምራት የጎበጠውን ለማቅናት፣ የጨለመውን ለማብራት፣ የሻከረውን ለማለስለስ፣ የሄደውን ለመመለስ መንፈሳዊ ሥልጣንና ኃላፊነት አለበትና። ለዚህ ነው ዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ በመልእክቱ (፭.፩) «ጎረይ ሰብዓ ቀሲሳን ሊቃውንተ» ለማስተማር፣ ለመምራት፣ ለማስተዳደር የሚገባ ከተማሩት ከሊቃውንት ወገን ምርጥ በማለት የሚያስረዳው።

ምክንያቱም ያልተማረ፣ በበቂ ትምህርትና ተግሳጽ ኅሊናው ያልተሰበረ ሰው ደፋር፣ ተኳር ስለሚሆን ነው። ድፍረት ደግሞ ስህተትን ያስከትላል፣ ስህተት በበኩሉ የእግዚአብሔርን ቁጣ ይቀሰቅሳል። በሥጋዊ ሕግ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው ሕግ ቢተላለፍ በግሉ ይወቀሳል፣ ይከሰሳል፣ አልፎ ተርፎ ይቀጣበታል። በተቃራኒው አንድ ሰው ሕገ እግዚአብሔርን ቢጥስ ወይም ቢተላለፍ ጦሱና መዘዙ ከራሱ አልፎ ለሀገርና ለሕዝብ ይተርፋል። ለኃጢአን የወረደ መዓት ለጻድቃን ይተርፋል ነውና።

ለምሳሌ

፩ኛ. የከርሚ ልጅ አካን የእግዚአብሔርን መሐላ አፍርሶ ያልተገባውን ንብረት በመስረቁ የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ላይ በመንደዱ ከጋይ ሰዎች ጋር በተዋጉ ጊዜ እግዚአብሔር ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ስለ ሰጣቸው ብዙት ያላቸው ሰዎች እንደ ሞቱ መጽሐፈ ኢያሱ (፯፥፩–፲) ያስረዳል።

፪ኛ. ምናምንቴዎቹ የኤሊ ልጆች በደብተራ ኦሪት ውስጥ ይሠሩት በነበረው ኃጢአት እግዚአብሔር ተቆጥቶ ሕዝበ እስራኤል ከፍልስጥኤማውያን ጋር በተዋጉ ጊዜ አሳልፎ ስለ ሰጣቸው ከእስራኤል ወገን ፴ ሺህ ሰዎች እንደ ሞቱ፣ ታቦተ ጽዮንም እንደ ተማረከችና ሁለቱም የኤሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስም እንደ ሞቱ ቅዱስ መጽሐፍ «እስራኤልም ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሊዋጉ ወጡ፣ በአቤኔዜር አጠገብ ሰፈሩ፤ ፍልስጥኤማውያንም በእስራኤል ላይ ተሰለፉ፤ ሰልፉም በተመደበ ጊዜ እስራኤል በፍልስጥኤማውያን ተመቱ፤ ጦርነት በተደረገበትም ስፍራ ከእስራኤል አራት ሺህ የሚያህሉ ሰዎችን ገደሉ። ሕዝቡም ወደ ሰፈር በመጣ ጊዜ የእስራኤል ሽማግሌዎች:- ዛሬ እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን ፊት ስለ ምን መታን? በመካከላችን እንዲሄድ ከጠላቶቻችንም እጅ እንዲያድነን፣ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን ታቦት ከሴሎ እና ምጣ አሉ። የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን ታቦት ከዚያ አመጡ፣ ሁለቱም የኤሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ጋር በዚያ ነበሩ» ሲል ያስርዳናል። መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ፬፥፩–፲፰።

እንዲሁም «የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ በየራሳቸው ጽናውንወስደው እሳት አደረጉበት፣ በላዩም ዕጣን አኖሩበት፣ በእግዚአብሔርም ፊት እርሱ ያላዘዛቸው ሌላ እሳት አቀረቡ። እሳትም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ በላቸው፣ በእግዚአብሔርም ፊት ሞቱ። ሙሴም አሮንን እግዚአብሔር ወደ እኔ በሚቀርቡ እቀደሳለሁ በሕዝቡም ሁሉ እከብራለሁ ብሎ የተናገረው የህ ነው አለው፤ አሮንም ዝም አለ። ሙሴም የአሮንን አጎት የዑዝኤልን ልጆች ሚሳኤልንና ኤልጻፋንን ጠርቶ፣ ቅረቡ ወንድሞቻችሁን ከመቅደሱ ፊት አንስታችሁ ከሰፈር ወደ ውጭ ውሰዱአቸው አላቸው። እነርሱም ቀርበው አነሱአቸው፣ ሙሴም እንደ አለ በቀሚሶቻቸው ጠቅልለው ወደ ውጭ ወስደው ቀበሩአቸው» ይላል (ዘሌዋውያን ፲፥፩–፭)።

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ይህችን አነስተኛ ጽሑፍ ለመጻፍ የተነሳሳው ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እየታዩ ያሉት ከሕገ ቤተ ክርስቲያን ጋር የማይጣጣሙ አንዳንድ አሠራሮችን ለመጠቆም ስለ ፈለገ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን የሊቃውንትና የምሁራን ድሀ አይደለችም። ይሁንና የሚገባቸውን መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን እውቀት የሌላቸው ማለትም የሚጠብቀውን የሚላላውን፣ የሚቆጠረውን የሚጠቀለለውን፣ የቅርብና የሩቁን፣ አንድና ብዙውን፣ የወንድና የሴት አንቀጽን በውል ያልለዩ፣ ምሥጢሩን ያላደላደሉ፣ ለቅስና ማዕረግ ብቻ ሳይሆን ለሊቃውንት በተፈቀደው ቦታ ሲቀመጡ ይስተዋላሉ።

የዚህ ዓይነት አሠራር መንታ ጉዳት አለው። አንድም የያዙት የሊቃውንት ቦታ በመሆኑ በሊቃውንት አማካኝነት መማር የነበረባቸው ደቀ መዛሙርትና ምእመናን ሳይማሩ ይቀራሉ። በሌላ በኩል ምሁራን ሊቃውንት የሚገባቸው ቦታ ሳይሰጣቸው በመቅረቱ እውቀታቸውን፣ ችሎታቸውን ለተተኪ ትውልድ ሳያስተላልፉ፣ ቤተ ክርስቲያናቸውን በሚገባቸው መንገድ ሳያገለግሉና ለራሳቸውም ሳይጠቀሙ ያልፋሉ። ሁኔታው በዚህ መንገድ ከቀጠለ ደግሞ ምሁራን አያንሱ፣ ያልተማሩ እየነገሡ፣ ይወጡና ውጤቱ የከፋ ይሆናል። ይህ እንዳይሆን የሚመለከታቸው አካላት ትኩረት ሰጥተው እየታዩ ያሉ ስህተቶችን በወቅቱ በማረም ከትዱሳን አበው የተረከብነውን ሕገ ቤተ ክርስቲያን በሥራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ መንፈሳዊና ሀገራዊ ግዴታ አለባቸው።

አነሳስቶ ለአስጀመረን አስጀምሮ ለአስጨረሰን ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን። ✣





# ከጨለማ ያመለጡ የብርሃን ፍሬዎች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናትና ቤተሰብ ጉዳይ ድርጅት የተመሠረተበትን ፴ኛ ዓመት ባለፈው ሰኔ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም በታላቅ ድምቀት አከበሯል። ድርጅቱ ባለፉት ፴ ዓመታት ውስጥ ከሃያ ሺህ (፳ ሺህ) በላይ እጓለ ማውታ ሕፃናትን እንደ አባትና እናት በመሆን አልብሶና አጉርሶ፣ አስተምሮና አሠልጥኖ ለወግ ለማዕርግና ለቁም ነገር አድርሷል። እነዚህ ሕፃናት በድርቅና በእርስ በርስ ጦርነት ወላጆቻቸውን አጥተው፣ ወይም ደግሞ ቤተሰቦቻቸው ባጋጠማቸው ኢኮኖሚያዊ ችግር ምክንያት በሞት ጥላ ተከበው፣ በጨለማ ባሕር ተውጠው ያለ ተንከባካቢ የትም ቀርተው የነበሩ ናቸው።

የሕፃናትና ቤተሰብ ጉዳይ ድርጅት በመላ ሀገሪቱ ባቋቋማቸው የተለያዩ የሕፃናት ማሳደጊያ ማዕከላት ውስጥ አድገውና ተምረው፤ ከተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና የሙያ ማሠልጠኛዎች ከዲፕሎማ እስከ ዶክትሬት ባለው ማዕርግ ተመርቀው፤ ከራሳቸው አልፈው ሀገራቸውንና ወገናቸውን በማገልገል ላይ የሚገኙ ወጣቶች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ናቸው። ዛሬም በመላ ሀገራችን በሚገኙ ፳፫ ሕፃናት ማሳደጊያ ማዕከላት ውስጥ ከሰባት ሺህ በላይ ሕፃናት በማደግ ላይ ናቸው።

በየማዕከላቱ ሆነው በአዳሪነት ከሚያድጉ ሕፃናት ውጭ ከቅርብ ቤተሰቦቻቸውና ዘመዶቻቸው ጋር ሆነው ከኅብረተሰቡ ተቀላቅለው ከድርጅቱ በሚያገኙት ወርሃዊ ደመወዝ ትምህርታቸውንና ሥልጠናቸውን የሚከታተሉ ሕፃናትና ወጣቶች ቁጥርም ቀላል አይደለም። አንባብያን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናትና ቤተሰብ ጉዳይ ድርጅት ሥር ስለሚያድጉ ሕፃናት መጠነኛ ግንዛቤ ይኖራችሁ ዘንድ በሰበታ ቤተ ደናግል ጠባባት ገዳም ሕፃናት ማሳደጊያ ማዕከል ሥር እያደጉ ካሉት ሕፃናት መካከል ለናሙና ያህል የጥቂቶቹን ይዘንላችሁ ቀርበናል።

## እግዚአብሔር ይመስገን ያለሁበት ኑሮ በጣም ጥሩ ነው

አባይነሽ ፍስሐ ትባላለች፣ የ፲ ዓመት ሕፃንና የ፬ኛ ክፍል ተማሪ ናት። ሰበታ ቤተ ደናግል ጠበባት ገዳም ሕፃናት ማሳደጊያ ማዕከል ውስጥ ነው ያገኘናት። አባትም እናትም የላትም፣ ሁለቱም ሞተዋል። ከደቡብ ጎንደር ደብረ ታቦር አካባቢ መምጣቷንና ከሀገሯ ስትመጣ የ፫ ዓመት ሕፃን እንደ ነበረች፣ የእሷ ታናናሽ የሆኑ አንድ ወንድምና አንዲት እህት እንደ ነበሩዋትም ታስታውሳለች። በጊዜው በእሷ፣ በወንድምዋና በጨቅላ ሕፃን እህትዋ ላይ ይደርስ የነበረው ችግርም ዛሬ ድረስ ከጨቅላ አእምሮዋ አልጠፋም። ከዚህ ውጭ አገር ቤት ዘመድ ይኑራት አይኑራት፣ እህትና ወንድሟ ይኑሩ አይኑሩ የምታውቀው የለም።



«በዚህ ማሳደጊያ ማዕከል ኑሮ እንዴት ነው?» ስንላት ፈገግ እያለች «በጣም በጣም ደስ ይላል፣ እግዚአብሔር ይመስገን እዚህ በጣም ነው



የሚንከባከቡን ሁሉም ነገር የተሟላ ነው» ነበር ያለችን።

አባይነሽ ንግግርዋ፣ አስተሳሰብዋ ከዕድሜዋ በላይ ነው። በትምህርት ጎበዝ ከሚባሉት ውስጥ የምትመደብ ናት። ብቻ በስፖርትና በእርሻ የትምህርት ዓይነቶች ደከም እንደምትልና ይህ ችግር ግን የብቻዋ ሳይሆን በአጠቃላይ የሰበታ ቤተ ደናግል ሕፃናት ችግር እንደ ሆነ ነው ያጫወተችን። ምክንያቱን ስትናገርም፣ «እኛ ብዙውን ጊዜያችንን የምናሳልፈው በጥናት፣ በትምህርትና በጸሎት ነው። ውጭ ያሉት ልጆች ግን ብዙውን ጊዜያቸውን በጨዋታ ስለሚያሳልፉ በተለይ በስፖርት ይበልጡናል። በእርግጥ እኛም የጨዋታ ጊዜ አለን፣ ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜያችንን በቁም ነገር ላይ ነው የምናሳልፈው» ባይ ናት። ✣

## አትሌት መሆን እፈልጋለሁ

የሺ ዓለም ተስፋ የ፱ ዓመትና የ፫ኛ ክፍል ተማሪ ናት። ከክፍል ክፍል በመዓርግ ከሚያልፉ ተማሪዎች አንዷ ናት። ከመዋዕለ ሕፃናት ጀምራ



www.ethiopianorthodox.org



ሰበታ ቤተ ደናግል ጠበባት ገዳም ሕፃናት ማሳደጊያ ማዕከል በማደግ ላይ ትገኛለች። ገና ጨቅላ ሳለች ደብረ ታቦር ከተማ እንደ ነበረች ትገዘ ይላታል።

የሺህ ዓለም አባትና እናት ብቻ ሳይሆን ወንድም እህትም የላትም። እናትና አባቷ በሞት የተለይዋት እሷን ብቻ እንደ ወለዱ ነበር። አሁን ወደ ምታድግበት ድርጅት ያመጧት የክርስትና እናትዋ እንደ ነበሩ ከመስማትዋ በስተቀር አሁን የምታውቀው ዘመድ የላትም።

የሺህ ዓለም ያለችበት ገዳም የሚያደርግላቸው እንክብካቤ እጅግ መልካም መሆኑን ትናገራለች። ሌላው ቀርቶ በትምህርታቸው እንዲበረቱ የጥናት ፕሮግራም በማውጣትና ለመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመክፈል ማጠናከሪያ ትምህርት እንዲማሩ በማድረግ፣ ተጨማሪ መጻሕፍት በማሟላት የሚያደርገው አስተዋጽኦ ገዳሙ ለዘለቄታው ሕይወታቸው ምን ያህል እንደሚጨነቅ ያሳያል ባይ ናት።

የሺህ ዓለም ያላትን ትርፍ ሰዓት ከሷ ለሚያንሱ ሕፃናት የሚከብዳቸውን በማስረዳት፣ በመኝታ ቤታቸው ፊት ለፊት የተተከሉ አበባዎችን በመንከባከብ ታሳልፋለች። የሺዓለም ከጓደኞቿ የምትለይበት አንድ ባሕርይ አላት፣ ስፖርት ትወዳለች፣ ከስፖርት ደግሞ ሩጫን ትመርጣለች። እንደውም ወደ ፊት ምኞቷ ታዋቂ አትሌት ለመሆን ነው።



## ምኞቴ ሐኪም መሆን ነው

ኅሊና ዓመደማርያም ገና የ፫ኛ ክፍል ተማሪ ብትሆንም ምኞቷ ትልቅ አስተሳሰብዋ ጥልቅ ነው። በእድሜ በኩል አሁን ፲፪ኛ ዓመትዋን ይዛለች። ሰበታ ቤተ ደናግል ጠበባት ገዳም ሕፃናት ማሳደጊያ መች እንደ ገባች ትገዝ ባይላትም ትምህርቷን ከ1ኛ ክፍል እንደ ጀመረች ታስታውሳለች።

ኅሊና ከመዕራብ ሐረርጌ (አሰበ ተፈሪ) አካባቢ ከመምጣቷ በስተቀር የተወለደችበትን ትክክለኛ ሥፍራ አታውቅም። አባትና እናቷ የሞቱት ሦስት ልጆች ከወለዱ በኋላ ነበር። አንደኛዋ እህትዋ አብራት (መዋዕለ ሕፃናት ውስጥ) ነው ያለችው። ወንድምዋ ግን ሀገር ቤት እናት አባቷን ከሚያውቁ ሰዎች ተጠግቶ እንደሚኖር ሰምታለች።

ኅሊና እያደገችበት ያለው ገዳም በሁሉም ነገር የተሟላ መሆኑንና እርስዋም በኑሮዋ ደስተኛ እንደ ሆነች ትናገራለች። ‹የሚቸግረኝ ነገር ስለ ሌለ ትኩረቴ ለትምህርት ብቻ ነው› የምትለው ኅሊና እስከ አሁን ሦስት ጊዜ መሸለሟን ነግራናለች። ለወደፊቱም ቢሆን አሁን ካለችበት በበለጠ ትምህርቷን አሻሽላ ሐኪም ለመሆን ትፈልጋለች።

ሐኪም ለመሆን የምትፈልገው ግን እንደዚሁ አይደለም። ኅሊና ይህንን አስመልክታ ስትናገር «በአሁኑ ጊዜ ኤድስ በሀገራችን ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ መሆኑን በመምህሮቻችን ከሚደረግልን ገለፃ ለመረዳት ችያለሁ። መድኃኒት እንደሌለውም ተነግሮናል። በበኩሌ ሕክምና ለማጥናት የምፈልገው የታመሙትን ለማከም ሳይሆን እንደ ኤድስ ያሉ መድኃኒት ያልተገኘላቸውን በሽታዎች ተመራምሬ መድኃኒት ለማግኘት ነው»

በበኩላችን ያሰበችውን እግዚአብሔር ያሳካላት ከማለት የምንጨምረው የለም። ✣

## የወደፊት ዓላማዬ እንደ እኔ አባት እናት የሌላቸውን ሕፃናትን መርዳት ነው

የ፲፰ ዓመቷ ታዳጊ ወጣት እመቤት እበራ በያዝነው ፲፱፻፺፰ ዓ.ም የ፱ኛ ክፍል ትምህርቷን አጠናቅቃለች። ሰበታ ቤተ ደናግል ጠባባት ገዳም ሕፃናት ማሳደጊያ የገባችው የ፯ ዓመት ሕፃን ሆና ነው። ከዚሁ አዲስ አበባ ከጉለሌ ነው የመጣችው። አባትና እናት የላትም፣ ብቸኛ ወንድሟ አክስቱ ጋር ሲዳሞ ውስጠ ነበር የሚኖረው። ይሁንና ሲያሳድጉት የነበሩት አክስቱ አምና ስለሞቱ አሁን ያለው ከአክስትዋ ባል ጋር ነው።

እመቤት የሰበታ ቤተ ደናግል ገዳም ሙሉ ሰው ሆነው እንዲያድጉ እንደረዳቸው ነው የምትናገረው። እንደ እመቤት አባባል ምግቡ፣ መኝታው፣ ልብሱ፣ ሕክምናው የተሟላ ከመሆኑም በላይ በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ሁለንብ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። በትርፍ ሰዓታቸው የተለያዩ እጅ ሥራዎች፣ እንጀራ መጋገር፣ ወጥ መሥራት የመሳሰሉ የባልትና ሙያዎችን ይማራሉ፤ መንፈሳዊ ዕውቀታቸው እንዲዳብር በቂ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይሰጣቸዋል፤ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ሕግም ገና ሕፃን ሳሉ ጀምረው ነው የሚማሩት።



እመቤት የወደፊት ዓላማዋን አስመልክታ ስትናገር «ከእግዚአብሔር ጋር የ፲ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናን አልፋለሁ የሚል ተስፋ አለኝ። አሁንም እግዚአብሔር ፈቅዶ ራሴን ከቻልኩ የመጀመሪያ ሥራዬ የማደርገው እንደ እኔ አባትና እናት የሌላቸውን ሕፃናት መርዳት ይሆናል።» ✣

# የቅዱስ ገብርኤል ተራዳኢነት

ከመልአከ ምሕረት ብርሃኑ ተስፋዬ

የመላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ቆመው ለሰው ልጆችና በጌታችን በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ምእመናን ሁሉ ምሕረትን፣ ሰላምን፣ ሕይወትን እንዲያገኙ ለተቸገሩት ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ ችግራቸውን እንዲያስወግድላቸው የታመሙትንም ጤና እንዲያገኙ ከሚለምኑና በአማላጅነታቸውና ለተራዳኢነታቸው ከታወቁና ከከበሩ መላእክት አንዱ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል መሆኑን በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ ይገኛል። (መጽ.ሄኖ.፯ ቁ.፯–፰፤ ዳን.፰ ቁ.፲፭–፲፯፤ ሉቃ.፩ ቁ.፲፱)

የመላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል አጋዕዝተ ዓለም ሥላሴ መላእክትን ፈጥረው ተመራምረው ፈጣሪያቸውን ይወቁ ብለው በተሰወሩባቸው ጊዜ በሥልጣን ከፍ አድርገው ከፈጠሩዋቸው መላእክት አንዱ ዲያብሎስ (ሰይጣን) ወደ ላይና ወደ ታች ቢመለከት ከእርሱ በሥልጣን በመዓርግ የሚበልጥ ባለየጊዜ እኔ ፈጣሪኣችሁ ብሎ በውሸት ተናገረ፤ በዚህ ጊዜ በሰማያት ያሉት መላእክት ሁሉ በጥርጥር ውስጥ ገብተው ስለተናወጡ የሰላም መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ፈጣሪያችንን እስክናውቅ ድረስ በያለንበት እንጽና፤ እንረጋጋ ብሎ መላእክትን ያጽናና ያረጋጋ መልአክ በመሆኑ መልአክ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ተብሎ ይነገርለታል (ይጠራል)።

በዚህ ጊዜ አጋዕዝተ ዓለም ሥላሴ ፈጣሪያቸውን የሚያውቁበት የዕውቀት ብርሃን በመላእክት ላይ ስለ አፈሰሱላቸው ፈጣሪያቸውን አውቀው ቅዱስ፤ ቅዱስ፤ ቅዱስ፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያሉ አመስግነዋል። (ገድለ አዳም ገጽ ፲፫፤ ኢሳ.፮ ቁ.፫–፬) የመላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ሰማያትንና ምድርን በውስጣቸው የሚኖሩትን ሁሉ የፈጠረ አምላካችንን እግዚአብሔር አንክድም ብለው በከሃድያን ነገሥታት ፊት ቆመው በልዩ ልዩ ሥቃያት የሚሰቃዩትን ሰማዕታትን ተጋድሎቻቸው እስኪፈጸሙ ድረስ በማጽናናትና በመርዳት፤ እንዳያቃጥላቸው የነደደውን እሳት በማጥፋት፤ በማቀዝቀዝ በልዩ ልዩ ችግር ተይዘው የነበሩትን ከፈጣሪው እያማለደ ችግራቸው የተወገደላቸው ምእመናን ስፍር ቁጥር የላቸውም ብንል ማጋነን አይሆንም። የእግዚአብሔር ቸርነትና ምሕረት ለዘለዓለም ነውና (መዝ.፩፻፴፰ ቁ.፩–፳፮)

በዚሁ ጽሑፍም ሕፃኑ ቅዱስ ቂርቆስንና እናቱ ቅድስት ኢየሉጣን ከሐዲው እስክንድሮስ የተባለ መኰንን በልዩ ልዩ ሥቃይ እንዲያሰቃዩአቸው ባዘዘ ጊዜ ገድላቸውን እስኪፈጽሙ ይህንንም ለማረጋገጥ ታኅሣሥ ፲፱ና ሐምሌ ፲፱ በየዓመቱ በሚከበረው በቁልቢ የቅዱስ ገብርኤል በዓልና በሌሎችም በቅዱስ ገብርኤል ስም በተሠሩ አብያተ ክርስቲያናት ሂደን ብንመለከት ምእመናኑ በቅዱስ ገብርኤል አማላጅነት የተደረገላቸውን ተአምራት እየተናገሩ የሚያቀርቡትን ስዕለት ራሱ ምስክር ነው።

የመላእክት አለቃ ቅዱስ ገብርኤል ከላይ እንደ ተገለጸው ከፈጣሪው ታዞ በጌታችንና በአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምነው በከሐድያን ነገሥታት ፊት የሚጋደሉትን ሰማዕታት ለመርዳትና ለማጽናናት ከእግዚአብሔር የተሰጠው ተግባር ስለሆን





www.ethiopianorthodox.org

ድረስ ቅዱስ ገብርኤል ሊቀ መላእክት እንዴት እንደረዳቸውና እንዳጽናናቸው እንማራለን። ቅዱስ ቂርቆስና እናቱ ኢየሉጣ በነበሩበት ዘመን በጣኦት የሚያመልኩ እንዲዮቅልጥያኖስና እርሱን የመሳሰሉት ከሐዲያን ነገሥታት የነገሡበት ዘመን ነበር። በዚህ ዘመን የብዙ ንጹሐን ክርስቲያን ደም እንደ ጐርፍ የፈሰሰበት። ክርስቲያኖች ስለ ሃይማኖታቸው ከቦታ ወደ ቦታ የተሰደዱበት። በእሳት የተቃጠሉበት፤ በሰይፍ የተቈረጡበት፤ ወደገደል የተወረወሩበት፡ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ብለው ብዙ መከራና ሥቃይ የተቀበሉበት ዘመን ስለ ነበር ዘመኑ ሰማዕታት ተብሏል፤ ዘመኑም ከ፪፻፺፬–፫፻፲፰ ዓ.ም መሆኑን በታሪክ ተመዝግበዋል።

በዚህ ዘመን ቅዱስ ቂርቆስ ሕፃን እያለ እግዚአብሔር አምላክ ለመንፈሳዊ ሥራ መርጦታልና የሦስት ዓመት ሕፃን ሆኖ ሳለ ዳዊት በመዝሙር ፻፲፰ ቁ.፻፴ «የቃልህ ፍቺ ያበራል ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል» ብሎ በተናገረው መሠረት ቅዱስ ቂርቆስም በሕፃንነቱ በመንፈስ ቅዱስ እንደ ሐዋርያት ጥበብና ማስተዋል ኃይልም ስለተሞላ በከሐድያኑ ነገሥታት ፊት ስለ ክርስቶስ አዳኝነትና አምላክነት እየመሰከረ የሚያመልኳቸውም ጣኦታት ከንቱ መሆናቸውንና ከምንም የማያድኑ መሆናቸውን ያስተምራቸውና ይገሥጻቸው ነበር። (መዝ.፻፲፰፥፺፰–፺፱)

እናቱ ቅድስት ኢየሉጣም ይህንን መንፈስ ቅዱስ ያደረበትን ሕፃን ልጇን ስለ ሰጣት እግዚአብሔርን እያመሰገነች የልጇዋን ብርታትና አስተዋይነት እያደነቀች ትበረታ ነበር። ነገሥታቱም በማስተዋሉና በቅዱስ ገብርኤል ተራዳኢነት ከእናቱ ጋር በሚያደርሱባቸው ልዩ ልዩ ሥቃያት አለመለወጡና እናቱን እያጽናና ብዙ ሥቃያትን በመቀበሉ ያደንቁት ነበር። እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነውና (መዝ.፷፯፥፴፭)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንደነ ቅዱስ ቂርቆስ በመሰሉ ሕፃናት አድሮ ብዙ መንፈሳውያን ሥራዎችን እንደሚሠራ ሲገልጽ «ሕፃናትን ተዋቸው ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና» (ማቴ.፲፱ ቁ.፲፬) ብሎ አስተምሯል። በአህያ ላይ ተቀምጦ በሆሣዕና ዕለት ወደኢየሩሳሌም ሲገባም ልዑል አምላክ መሆኑን ተገልጾላቸው ሆሣዕና ከአርያም የወረደ መድኃኒት እያሉ እየዘመሩ የተቀበሉት ሕፃናት ነበሩ። (ማቴ.፳፩ ቁ.፱–፲)

ቅዱስ ቂርቆስም ምንም ሕፃን ቢሆን ሁሉን ለማድረግ የሚቻለው አምላክ ከቅዱስ ቂርቆስና ከእናቱ ከቅድስት ኢየሉጣ ጋር ሆኖ ከሐድያን በሚያደርሱባቸው ልዩ ልዩ ሥቃያት እንዳያዝኑና እንዳይደክሙ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ ያጽናናቸውና ይረዳቸው ነበር (መዝ.፴፫፥፯–፰)።

ሕፃኑ ቅዱስ ቂርቆስና እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ብለው ጣዖታት ከሚያመልኩ ከሐዲያን ነገሥታት ብዙ ሥቃያት ተቀብለዋል። በገድለ ቂርቆስ ተጽፎ እንደሚገኘው። እስክንድሮስ የተባለ ከሐዲ መኰንን አሥራ አራት የሾሉ ብረቶች በእሳት አግለው ሰባቱን በቅዱስ ቂርቆስ አካል ሰባቱን ደግሞ በቅድስት ኢየሉጣ ሰውነት እያጋሉ እንዲያሰቃዩአቸው አዘዘ። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ቂርቆስና ቅድስት ኢየሉጣ ደስ እያላቸው ተቀበሉት እንጂ ወደ ኋላ አላሉም። ትዕግሥታቸውን ያየ አምላክም የሚረዳቸውን ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ የብረቱን ግለት አቀዘቀዘላቸው፤ የጋሉ ብረቶችም ከአካላቸው አስወገደላቸው፤ በዚህ ጊዜ ቅዱስ ቂርቆስና ቅድስት ኢየሉጣ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ ያዳናቸውን እግዚአብሔርን አመሰገኑ። (መዝ.፺፥፲፩–፲፪)።

እንደገና መኰንኑ ሰይጣን በልቡ አድሮበታልና። በቅዱስ ቂርቆስና በቅድስት ኢየሉጣ አምላክ ማመን ሲገባው ቅዱስ ቂርቆስንና ቅድስት ኢየሉጣን የሚሰቃዩበትን የብረት ጋን አሠርቶ በብረት ጋኑ ውኃ እንዲያፈሉና ቅዱስ ቂርቆስንና እናቱ ቅድስት ኢየሉጣን በጋኑ በፈላው ውኃ እንዲያስገቧቸው አዘዘ። በዚህ ጊዜ የውኃው ፍላት ድምፁ እንደክረምት ነጐድጓድ ይሰማ ነበር፤ ቅድስት ኢየሉጣም ከውኃው ፍላት ድምፅ የተነሣ በጣም ፈራች። በዚህ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል የታጠቀ ልጅዋ ቅዱስ ቂርቆስ አይዞሽ እናቴ አትፍሪ የፈጣሪያችንን ፊት ለማየት እንበርታ፤ ገድላችንንም እንፈጽም አናንያንና አዛርያን ሚሳኤልን ያዳነ አምላክ እኛንም ያድነናል ብሎ አበረታት አጽናናት። በዚህ ጊዜ ሁል ጊዜ የሚረዳቸውን ቅዱስ ገብርኤል ሊቀ መላእክት መጥቶ የፈላውን ውኃ አቀዝቅዞላቸዋል።

ከብዙ ሥቃያት በኋላ ቅዱስ ቂርቆስ ወደ ፈጣሪው «ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ሁሉ ሥቃያት ስለ ቅዱስ ስምህ ብለን ስንቀበል መልአክህን ቅዱስ ገብርኤልን ልከህ ስለ አዳንከን እናመሰግንሃለን» ብሎ ከጸለየ በኋላ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአዕላፍ መላእክት ጋር ተገልጾ ወዳጄ ቅዱስ ቂርቆስ ስለ ስሜ ብለህ ብዙ ሕማማትንና ሥቃያትን ስለ ተቀበልክ ስለአምላክ ቂርቆስ ስለ አምላክ ኢየሉጣ ብሎ ለቤተ ክርስቲያን ዕጣን ስንዴ ያቀረበ (የሰጠ) በአንተ ስምና በእናትህ ስም ቤተ ክርስቲያን ለሠሩና ላሠሩ፤ ስለአንተና ስለ ቅድስት እናትህ ብየ ከልዩ ልዩ በሽታ አድናቸዋለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ሰጥቶታል። ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም ተብለዋልና (ማቴ.፲ ቁ.፵፪)

ስለዚህ በቅዱስ ገብርኤል ተራዳኢነትና አማላጅነት በቅዱስ ቂርቆስና በቅድስት ኢየሉጣ አማላጅነት የምናምን ምእመናን ሁሉ ከቅዱስ ገብርኤል ሊቀ መላእክትና ከቅዱስ ቂርቆስ ከቅድስት ኢየሉጣ በረከትንና ረድኤትን ለመቀበል ቤተ ክርስቲያናቸውን ወደ ታነጸበት እየሄድን በዓላቸውን እያከበርን ለተቸገሩት ነዳያንና አካላቸውን ለጐደለ ስለአምላክ ቅዱስ ገብርኤል ስለ አምላክ ቅዱስ ቂርቆስና ስለ አምላክ ቅድስት ኢየሉጣ ብለን ብንመጸውት በረከትንና ረድኤትን እናገኛለን፤ በኋላም የዘለዓለም ሕይወት ያለበትን መንግሥተ ሰማያት እንወርሳለን፤ በዘለዓለም ቤቶች እንዲቀበሉአችሁ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ ተብለዋልና (ሉቃ.፲፮፥፱–፲)

የሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ተራዳኢነት የቅዱስ ቂርቆስና የቅድስት ኢየሉጣ በረከትና ረድኤት በሁላችን ምእመናን ላይ ለዘለዓለም ይደርብን አሜን። ✣



www.ethiopianorthodox.org